ቤቴል፡ቡክስ
Bethel
(2) 405-2089

# ወቅታዊ ዘላለማዊ

## የሴሚናር ጽሑፎች ስብስብ

ንጉሤ ቡልቻ

ሐምሌ 2005 ዓ.ም

የቅጂ መብት©ንጉሤ ቡልቻ 2005 ዓ.ም መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

በ LLT (Light House of Living Truth) አሳታሚነት ታተመ።

ንጉሤ ቡልቻ

ስ.ቁ +251-911 219851

መ.ሣ.ቁ 30723 አ.አ

ኢሜይል su_ethiopia@yahoo.com

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተወሰዱት

በአብዛኛው ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም (አመት)

እና ከነባሩ (ቀ.ኃ.ሥ) ትርጉም ነው።

የሽፋን ንድፍ - በረከት ታደሰ

የገጽ ቅንብር - ሐዋርያው ጴጥሮስ

# ምስጋና

መጽሐፏ ትንሽ ብትሆንም የብዙ ደጋግ ሰዎች ቅን ትብብር አካትታለች። ከመነሻው እስከመድረሻው በአሳብም በገንዘብም ሥራውን ያስተባበረው የ LLT (Light House of Living Truth) ቡድን አባላትን፥እነዚህም፦ በጥልቅ እንድናስብ ብቻ ሳይሆን በጥልቅ እንድንፀልይም የሚያተጋን አቶ ሰሎሞን ከበደን፥ ሰላማዊ ገርነቱና ሰበን ነገር ያለው ቁጭት ያልደከመበት ፓ/ር አታላይ ዓለምን፥ ወንድማዊ ማበረታታቱና የማስተባበር ችሎታውን የማደንቀው አቶ ፈቀደ ተፈራን፥ ቃሉ ጥቂት ብትሆንም የሥራና የትብብር መንፈሱ ከፍ ያለውን ረዳት ፓ/ር ሽመልስ አድማሴን እንዲሁም ጥንቃቄዋና የእህትነት በጎ ምኞቷ የሚያግዘንን ወ/ሮ ሜሪ ላቀውን በአክብሮት አመሰግናለሁ።

እንዳበጃጅ የነገረኝን ሁሉ ከችኮላ ብዛት ባላካትትም በአርትኦትና ጠቃሚ አስተያየቶች በመስጠት ያገዘኝን ሚክያስ በላይን፥በጽሑፍ ትየባና በአይዞህታ በጸሎትና በሌሎችም መንገዶች የረዱኝን የቃለ እግዚአብሔር አንባቢዎች ማህበር ባልደረቦች ትዕግሥት ተሾመ ሁለቱ ብርሃኑዎችና ወንድሙን እንዲሁም የኮምፓሷ ሜሮን ታምራትን - በገጽ ቅንብርና በሽፋን ንድፍ ያገዙኝን ሐዋርያው ጴጥሮስን (ማዕረጉ ሳይሆን መጠሪያ ስሙ ነው) እና በረከት ታደሰ (ቤኪ)'ን ከልብ አመሰግናለሁ።

ስማቸው ያልተጠቀሱ በግራም በቀኝም ያበረታቱኝ በልዩ ልዩ መንገድ የደገፉኝን ሁሉ አመሰግናለሁ።

በየሴሚናሩ ላይ ስሯሯጥ ወረቀት እያጋበስሁ ቤት ሳጣብብና ቃላት ቅመራዬን ስሞክርባቸው የታገሡኝንና በደስታዬ ደስ የሚላቸውን ባለቤቴን ማክዳ ኀይሉንና ልጃችንን ኤፍራታ ንጉሤን በፍቅር አመሰግናለሁ።

ወቅታዊ ፋይዳ እንዲኖረኝ

ለሚያነቁኝ ፥ ለሚጸልዩልኝና
ለሚያበረታቱኝ

ለሁለቱ ውዶች - ማኪ (የኔ ባለቤት)እና
ኤፊ (ልጃችን)

ይህችን መጽሐፍ አበረክታለሁ።

# ማውጫ


ማሚሻ - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - 1

1. ወቅታዊ - ዘላለማዊ - - - - - - - - - - - - - - - - 3
2. የክርስቲያን "ሚዲያ" ሜዳ - - - - - - - - - - - - 9
3. አንጡራ ወንጌል - - - - - - - - - - - - - - - - - 22
4. ሥነ ምግባር በሦስተኛው ሺህ ዘመነ ምሕረት - - - - 28
5. የንባብ እንቅፋት - የንባብ ትጋት - - - - - - - - - - - 49
6. ኢትዮጵያ እና የተስፋ ጥበቃ - - - - - - - - - - - - - - 57
7. ካሪዝማዊ ቅርስ - - - - - - - - - - - - - - - - - 76
8. ምን ዐይነት መሪነት - - - - - - - - - - - - - - - - - - 90
9. የትርጉም ሥራና የወንጌል ተልእኮ - - - - - - - - - 104
10. ዙረት ወይስ ስምሪት? - - - - - - - - - - - - - 114
11. ወንጌላዊ ክርስትና - - - - - - - - - - - - - - - - 122
12. የሰባኪው ጥሪና ሥነምግባር - - - - - - - - - 126

# ማሟሻ

የእንጀራ ባህል ውስጥ ያደግን እኛ አብዛኞቻችን እንደምናስታውሰው ማለፊያ እንጀራ ከምጣዱ ከመውጣቱ በፊት ምጣዱ በጎመን ዘር፥ በተልባ ዘር እንደሚወለወል፥ እንደሚሟሽ ሁሉ የንባቡን ሜዳ ልጠርግላችሁ ብዬ ነው ይህንን ገጽ የምጽፈው።

እነዚህ እዚህ የተሰበሰቡ ጽሑፎች በየጊዜው አንዳንድ አሳሳቢና አነጋጋሪ ጉዳዮች ሲታዩ ጉባኤ ተጠርቶ እንመካከር፣ አሳብ አዋጡ፤ መላ አምጡ በተባሉባቸው መድረኮች ላይ የቀረቡ የውይይት ማዋዣዎች ናቸው። “ጥናቶች” የሚል ዲታ ቃል እንዳልጠቀም የከለከለኝ በመረጃ የደለቡ፥ ጓዳ ጎድጓዳውን የበረበሩ፥ የጠረቁ ሥራዎች ስላልሆኑ ነው። ታዲያ እስኪደልቡ አቆይተህ አታመጣቸውም ነበር? ብትሉኝ አልቆጣችሁም። አደልባለሁ ብዬ መኖ ስፈልግ እኔው እራሴ ዋትቼ እንዳልቀር፣ አንድም እናንተም ድልብ ሠንጋ እየጠበቃችሁ በጠኔ እንዳታልቁ ለራብ ማስታገሻ ቢሆን ብዬ ነው።

እና ራብ አስታግሱበት፤ ሠንጋውን ግን አብረን እንቀልብ። የየድርሻችንን እንሥራ። ገና ስንት መመርመር ያለበት መወያየት ያለብን ጉዳይ እንዳለ እናንተም አይጠፋችሁ።

ሌላ ነገር ደሞ - ስለ መጽሐፉ ርእስ ---

መሬት ላይ ነዋሪዎች በወቅት ፍርቅርቅ፥ በፀሐይ መውጣትና መግባት ሥርዓት ውስጥ ያለን ነን። የዛሬ ጉዳይ ያሳስበናል። ፍጥረታችን ራሱም በደቂቃ ስባሪ ውስጥ ባለ የሕይወት ንዝረት የተዋቀረ ነው። በማኅበር ስንኖርም የወል የሆኑ ሳቆችና ሲቃዎች በተቀላቀሉበት በአንድ የትውልድ ዘመን ወንዝ ውስጥ የምንንሳፈፍ ነን። ተመሳሳይ ጥያቄዎች አሉን፤ወቅታዊ መልስም እንሻለን።

እነዚህ ስብስቦች በየወቅቱ በሚነሱ ጉዳዮች ሰበብ የተጻፉ ናቸው። በየዕለቱ ውሎ - አምሽቶአችን ፣በክርስቲያን ማኅበረሰብ ቅብብሎሽ ውስጥ ያሉ የጊዜው ጉዳዮች ናቸውና ‘ወቅታዊ’ የሚለው ቃል ይወክላቸዋል። ምንም እንኳ እነዚህ አርእስተ ጉዳዮች በፀሐይ መውጣትና በፀሐይ መግባት ቅንብብ ውስጥ ያለውን ኑሮአችንን

ቢያስተነትኑም የዛሬውን ጉዳይ ሲያዩ የሚሞክሩት ቅድመ ፀሐይም፥ ድኅረ ፀሐይም ኗሪ በሆነው አምላክ ቃል፥ ያም ቃል በሰጠን ዘላለማዊ ውቅር መነጽር ነው። ስለዚህ 'የዘላለም' ዘር አላቸው። 'ወቅታዊ- ዘላለማዊ' መባላቸውም ለዚሁ ነው። ከዚህ በላይ ተናገር ብትሉኝ ማጣፊያው እንዳያጥረኝ ይኸው ይብቃኝ፤ እናንተ ግን ከፈለጋችሁ ቀጥሉ...

ከስብስቡ ውስጥ ሦስቱ "ዙረት ወይስ ስምሪት""ምን አይነት መሪነት" እንዲሁም "ወንጌላዊ ክርስትና" የተሰኙት መጣጥፎች ለመጽሔቶች የተላኩ እንጂ ለሴሚናር የቀረቡ አይደሉም። የቀሩት ሁሉ የሴሚናር ውይይት መነሻ ቢደረጉም አሁን ሲታተሙ ሲሉ ስለእናንተ አክብሮትና ጥቅም ስል ነካክቼአቸዋለሁ። ማታ የተሠራን ወጥ ጧት አሙቀነው እንደምንበላው ዐይነት።



## ወቅታዊ - ዘላለማዊ

*"ሁሉንም ነገር በጊዜው ውብ አድርጎ ሠራው፤ በሰዎችም ልብ ዘላለማዊነትን አኖረ" መጽሐፈ መክብብ*

እኛ የጊዜና የዘላለም ቅይጥ ነን። በነፍሳችን ውስጥ የሚደለቀው አታሞ ጠባቡ ግጣም ዛሬ ዛሬ እያለ ሽቅብ ሲቅጠለጠል፥ ሰፊው ግጣም ዘለ- ዓለም እያለ ይደፋል። ስለዚህ በወቅትና በዘላም መካከል ክፉኛ ተወጥረን እንኖራለን። የመኖርም ዋናው ጥበብ ይህ ውጥረት ያላግባብ እየከረረ አንገታችንን እንዳይገዘግዝ አውታሩን በሚዛን የምንዘረጋበት ጠንቃቃ አካሔድ ነው።

ክርስቲያኑ ሰው የሚያምነውና የሚያስበው ዛሬና ዘላለም (ወቅታዊነትና ዘላለማዊነት) ምንም የማይገናኙ ባላንጣዎች እንደ ሆኑ አድርጎ አይደለም። እንዲያውም እምነታችን "ዘላለም በየዕለቱ ይሠራል" የሚል ስልት ነው። የየዕለቱ ትጋት፣ የየዕለቱ ምላሽ ተጠራቅሞ ዘላለሙ ጎተራ ውስጥ ይገባል። ዛሬ የምንቀሳቀስበት ስላች የዘላለሙ አውራ ጎዳና መጋቢ ነው። እንግዲያው ክርስቲያን ወቅትን አይክዳትም፤ የሌላች ይመስል ዐይኑን ግንባር አያደርግባትም፤ ወቅትን አትኩሮ ያያታል፤ አላፊ ጠፊ ብትሆንም መጥታ እስክትሔድ ባግባቡ ያስተናግዳታል፤ ትታ ያለፈችውን ቅርስ መዝግቦ እንደ ዐቅሟና እንደ ዐይነቷ ከአላፊ ባልንጀሮቿ ቅርስ ተርታ ይደርድርላታል።

ክርስቲያኑ ሰው ወቅት አልቦ እንዳልሆነ ሁሉ በወቅት እግረ ሙቅም አልታሠረም። የወቅታዊነት አንዱ ዐበሳ ሌሎች ነገሮች ሊታዩ እስከማይችሉ ድረስ ገዝፎ ዐይን መከለሉ ነው። ብልኅ ክርስቲያን ይህን የወቅት "ልታይ ልታይ" ባይነት አባብሎና ገሥጾ ወቅቱን በዘላለሙ ዋና ውቅር ላይ ያስቀምጣል፤ ተገቢ ቦታውንና ቅርጹንም ይሰጠዋል። ይህን የሚያደርገው ለወቅትም ለዘላለምም ሲል ነው።

እግዚአብሔር የትናንት ነው፤ የዛሬና የነገም ነው። ቁጥር አልባ ነገዎችም በእጁ ናቸው። በዘላለም ሕልውና እንደሚዋኝ በጊዜ ጡቦችም ላይ ይራመዳል።

*"ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፤ እንደ መጎናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፤ አንተ ግን ያው አንተ ነህ፤ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም" (መዝ. 102፥26-27)፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬም ለዘላለምም ያው ነው" (ዕብ. 13፥8)፤ "ልክ ጊዜው ሲደርስ ክርስቶስ ስለ ኀጢአተኞች ሞቶአልና" (ሮሜ 5፥6)፤ "እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ ... ዘመኑን በሚገባ ዋጁ" (ኤፌ. 5፥15-16)።*

ክርስቲያን ወቅታዊነት በዘላለም አንጻር ዛሬን ማየት ነው፤ ዛሬን መተርጎም መቻል ነው፤ ለዛሬ ጥያቄ ዛሬ የሚደመጥ ዘላለማዊ መልስ መስጠት ነው።

## ለምን ወቅታዊነት?

ወቅታውያን መሆን የሚያሻን ወቅታውያን ለመሆን አይደለም። አለበለዚያ የፋሽን ሎሌዎች ልንሆን ነው። ወቅታዊነት ብቻውን ምስኪን ፍልስፍና ነው። ወቅታዊነት የሚያስፈልገው አስሚታ (impact) እንድናሳድር ነው። ደነዝ፣ ዱልዱም፣ የማይሰማ፣ የማይሰማ እንዳንሆን ነው። ክቡር ዓላማ ይዘን፣ የነጠረ እውነት ተሸክመን አሳፊ አግዳሚው የሌለን ያህል እንዳይመስለው ባና የደረበበት ጆሮውን ለማስከፈትም ሲባል ነው። ወቅታዊነት አንድም የዘላቂው መፍትሔ መጠቅለያ ጌጠኛ ወረቀት ነው። ወቅታዊነት የሰውን ተፈጥሮ መገንዘብ ነው። አጥንቱ ዘንድ ሰመ ድረስ በቆዳው በኩል መሔድ ማለት ነው። ደግሞም ሰውየው ቁርበትና አጥንት ደምና ሥጋ አይደለምን?



ቀደም ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች (ሰባኪዎች) ወቅታዊ ጉዳይ ያነሡበት ምሳሌ አለ። ሐዋርያው ጴጥሮስ የበዓለ ኀምሣን የብዙ ልሳናት ነገር ተያይዞም የመጣውን "ሰዎቹ ሰክረዋል" የሚል ሕዝባዊ አሜታና ስድብ የስብከቱ መነሻ ያደርገዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ በአቴናዊ ቆይታው ዛሬ ፍራሾቻቸው የቱሪስት መስህብ የሆኑትን ታላላቅ ሕንጻዎች ሳይፈርሱ በፊት አይቶአቸዋል። መሠዊያዎቹ ላይ የተጻፈበትን አንብቧል፤ የግሪክ ባለ ቅኔዎችን ዝነኛ ግጥሞች ቃኝቷል። በእነዚህም መነሻ የማይለወጠውን ወንጌል ሰብኳል። ዳንኤል ባለ ራእዩ የወቅቱንና የብዙ ወቅቶችን ጉዳዮች ዐይቷል፤ አስተንትኗል። ዮሴፍ ልባሙ ሰው የወቅቱን ከባድ ቋጠሮ በእግዚአብሔር መንፈስ ጉልበት ፈታ፤ የችግሩን አይቀሬነት መተንበይ ብቻ ሳይሆን "የመፍትሔው አካል" ሆነ።

## የወቅታዊነት ገጸና

ወቅታዊነት ቁርጠኝነትንና ጠንቃቃ አካሔድን ይጠይቃል። ይህም አካሔድ ሦስት መረጋገጫ ጡቦች ያሉት ይመስለኛል፡ -ትሥጉታዊነት፣ ተርጓሚነት እና ማተበኛነት።

### ትሥጉታዊነት

ወቅታዊው ጉዳይ ያለው እዚያ ማዶና እነዚያ ሰዎች መካከል ይመስላል። ክርስቲያኑ የዚያ ማዶውንና የእነዚያን ሰዎች ጉዳይ የዚህ ሰፈርና የእኛ ጉዳይ ማድረግ ካልቻለ ወይም በማስተዋልና በተገቢ ስሜት ካላዳመጠ ፋይዳ ያለው አስተዋጽኦ ሊያደርግ አይችልም። ለዚህ ደግሞ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሔደበት መንገድ የሚበልጥ ጎዳና የለም። ኢየሱስ መለኮት፥ ሥጋ ሆኖ በመካከላችን አደረ። ያደረው ሊናገረን ብቻ አይደለም፤ ሊሰማንም ነው። ሊያክመን ብቻ አይደለም፤ ሊታመመልንም ነው። ከትሥጉት (ሥጋ ከመሆን) የበለጠ አስሚነት ወዴት ይገኛል?! እንግዲያው የክርስቲያን ተግባቦት (communication) ውብ ንድፍ ተበጅቶለታል፤ ይህም ትሥጉታዊነት ነው። ወደ ወቅቱ፣ ወደ ሕዝቡ፣ ወደ ግለ ሰቡ ጉዳይ እንንዘለቅና እንወቅ፤ እንወቅና እንነጋገር።

ይኸው ርእሰ ጉዳይ ይዟቸው በርጋታ ያሰቡበት ዶ/ር ጆን ስቶት ይህን ይላሉ፡-

*እንደ ምን አርገን ነው በአንድ ጊዜ ሥር አጥባቂ፣ ሥር ነቀልም (conservative and radical) የምንሆነው? ማለቴ የእግዚአብሔር አስተርጓዮ (መገለጥ) እንዳይበረዝ ዘብ በመቆም ሥር ማጥበቅና ያንኑ መገለጥ በጥልቀት ተግባር ላይ እንዲውል ሥር ነቀል አካሔድ መሔድ የሚቻለው እንዴት ነው? በታሪካዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና እውነቶች የተቃኘ፣ ወዲያውም ከዘመነኛው ዓለም እውነታዎች ጋር የተዋወቀ ክርስቲያናዊ አእምሮ ማበጀት የሚቻለው እንዴት ነው? በመንታ እምቢታ መጀመር አለብን፤ በቃሉ ውስጥ እጅግ ተመስጠን ይህን ዓለም መደበቂያ ዋሻ አድርገነው እውነታን ጨርሶ እንዳይጋፈጥ፣ እንዳናመነኩሰው እምቢ ማለት አለብን። በዚህ ትይዩ ደግሞ በዓለም እጅግ ተመስጠን ከመመሳሰላችን የተነሣ ይህ ዓለም በቃሉ የፍርድ ችሎት ላይ እንዳይቀርብ መከላከልን እምቢ ማለት አለብን። ሽሽትም ተመሳስሎም (Escapism and conformity) እርስ በርስ ይጣሉ እንጂ የስሕተት አካሔዶች ናቸው። የትኞቹም የክርስቲያን መንገድ አይደሉም።*

*የዚህ መንታ እምቢታ አዎንታዊ ገጽታ መንታ ጆሮ ነው፤ ቃሉንም ዓለምንም መስማት። መስማት ለሁሉም ሰው አስቸጋሪ ነገር ነው፤ ግን ከሁሉም ይልቅ እኛ ክርስቲያኖች የበለጠ ሳንቸገር አይቀርም (ምናልባት እግዚአብሔር የተናገረውን ለማስተጋባት እንደ ተጠራን ስለምናምን ይሆናል)። አርማችን ከጆሮ ይልቅ ምላስ ነው። እግዚአብሔርንና ሰብአዊ ፍጡርን በተመሳሳይ ሁኔታና በእኩል ደረጃ እናደምጥ ማለቴ አይደለም። ቃሉን የምንሰማው ለመረዳት በመጓጓት በትሑት አክብሮት ነው፤ ዓለምን የምናደምጠው ለመረዳት በመጓጓት ቢሆንም በሒሳዊ ንቃት ነው። ዓለምን የምንሰማው የሚለንን ሁሉ ለማመንና ለመታዘዝ ሳይሆን*



*ስለሚናገረው ነገር ርኅራኄ እንዲያድርብንና ወንጌል እንዴት እንደሚዛመደው ስናጤን ጸጋ ለመቀበል በመሻት ነው።*

*በዚህ የመንታ ማዳመጥ ትጋት ብቻ ነው ወቅታዊ ክርስቲያን መሆን የሚቻለው። ያን ጊዜ ታሪካዊና ዘመናዊ የሚሉት ቅጽሎች የማይጣጣሙ መሆናቸው ይቀራል። የምናወጀውም የምሥራች እውነተኛና አዲስ ይሆናል። በትናንት ብርሃን ዛሬን እንኖራለን።" (ትርጉም የእኔ)*

እንግዲያው እኚህ ሰው እንዳመለከቱን ምድር ዓለሙን ወደ የወረደውንና ልዩት (unique) ብሥራት ይዞ የመጣውን ሥግው ጌታ ስንመስለው ነው ፋይዳ ያለው ሥራ የምንሠራው።

## ተርጓሚነት

ክርስቲያን ወቅት ተመልካች ብቻ ሳይሆን ወቅት ተርጓሚም ነው። ሕይወትን ሳይተረጉሙ መኖር እንዲያውም አይቻልም። ያዩትን የሰሙትን "እንደ ወረደ" የሚያቀርቡ ሰዎች ይኖራሉን? ክርስቲያን ለሐቅ ጠንቃቃ መሆን ያሻዋል፤ ነገር ግን ሁነቶችን በመንፈስ ዐይን በቃሉ ብርሃን ፍቺ ሊሰጣቸው ይገባል። የሰማዩን ፊት ዐይተው የአየሩን ጠባይ የሚናገሩትን ሰዎች ጌታችን ዘመኑን የማትመረምሩ ስለ ምንድን ነው? ብሎ ወቅሷል። የወቅቱ ትኩሳት ሥር የሰደደ በሽታ ምልክት ሊሆን ይችላል። በቂ ምርመራና ስያሜ መስጠት ትዕግሥትና መንፈሳዊ ልቡና ይሻል።

የሕዝብ ጭንቀት፣ የቡድን እሰጥ አገባ፣ የወጣቶች ጀግኖች ድምቀት፣ የዓለም ፖለቲካ አካሔድ፣ የኢኮኖሚ ውጥረት፣ ወዘተርፈ... ሊመረመሩና በወደቀ ዓለም ውስጥ ባለ እውነታ በሚመጣውም ዓለም ተስፋ መነፅር እየታዩ ትርጉም ሊሰጣቸው ይገባል።

የወቅቱን ሁኔታ ለማየት ወደ ዓለሙ ጥጋጥግ ሁሉ እንሩጥ እንጂ ማንም መንገደኛ "ሌባ ሌባ" እያለ የሚያሳድደውን ሰው ሳናረጋግጥ ሌባ አንልም። ትርጉሙ የራሳችን ነው። ጳውሎስ የአቴናን ጣኦታት የተረጎመበት መንገድ የአቴና ከንቱ በተረጎ መበት መሆን በግድ የለበትም።

### ማተበኛነት

የአገራችን ሰው እውነቱን ለማረጋገጥ ታማኝነቱንም ለማስመስከር ሲሻ "ለክሬ፣ ለማተቤ ብዬ እንጂ መዋሸት ምን ገዶኝ" ይላል። ማተበኛነት ለቆምንለት እውነት ጽኑ ታማኝነት ነው።

ክርስቲያን ተማሪ፣ መሪ፣ ባለሙያ ጸሐፊ፣ ነጋዴ፣ የሆነውን ሁሉ ከመሆኑ በላይ ክርስቲያን ነው። ባለ እምነት፣ ባለ መጽሐፍና ባለ ተልእኮ ነው። ወቅታዊውን ጉዳይ ለሕዝብ ጥቅም ሲያስተነትን የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲሰፋ መንገድ በመጥረግ አካሔድ ነው። የማይደራደርባቸው፣ የማያለሳልሳቸው፣ እየሸነገለ ዳር የማያስይዛቸው አዕማድ እውነቶች አሉት። ስለዚህ የወቅቱን ጉዳይ በእነዚህ እውነቶች እየገራ ቅርጽ ይሰጠዋል። "ዘመኑን ዋጁ" ስለተባለም የወቅቱን ፎልፏላ ወንዝ እያስገበረ ለእግዚአብሔር መንግሥት እርሻ ማስፋፊያ ቦይ ይቀዳል። የሚባለው ሁሉ ተብሎ ወደ አንድ ጠቅላይ እውነት፣ ወደ አንድ ልዑል አምልኮ እንዲመጣ ተግቶ ይሠራል።

ክርስቲያን ወቅታዊነት ይቻላልን? ለምን አይቻልም? ይቻላል እንጂ። ብቻ ሦስት ነገሮች መሟላት አለባቸው፦ ሕያው አምላክ ያለ እንደሆን፣ እርሱም ሕያው ቃል ያለው እንደሆን፣ ያንን ሕያው ቃል ከእውነት ጋር የሚያዛምድ ሕያው ሰው ያለ እንደሆን ወቅታዊነትም ዘላለማዊነትምይቻላል።

የዛሬ ነገር የሚገደው፣ የሚያይ የሚሰማ ሕያው አምላክማ አለ! የተጻፈው ጥንት ቢሆንም ዛሬም ስለታም ሆኖ የሚሠራ ሕያው ቃል አለ! እንግዲያው፦ ክርስቲያኑ ሰው ወቅቱንና ዘላማዊውን ቃል (ሁሉቱንም) የሚያጠና ትጉህ ሕያው ሊሆን ይጠበቅበታል። ከዚህ የተጣጣመ አስተውሎት እየተነሣ ጠቃሚና ክብራማ ተግ ባር ለመፈጸም ይንደረደራል፤ ልቡናው ሥል የማገናዘብ ዐቅም ያዳብራል፤ መንፈሱ ለላይኛው መንፈስ ንዝረት ይገብራል፤ ስለዚህ እጁ የፈውስ አሸንዳ ይሆናል።



## የክርስቲያን "ሚዲያ" ሜዳ፦

### በአብያተ ክርስቲያን መካከል ባለው ግንኙነት አንጻር

*"እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብትበላ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ።" ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ምዕመናን*

ከማስጠንቀቂያ ጥቅስ መጀመሬ የውይይታችን ፍሬ ነገር ክባድ መሆኑን፣ ወዲያውም ደግሞ ሐዋርያዊው ተግሣጽና ምክር ሁላችንን የሚመለከት መሆኑን ስለሚያሳይ ራሳችንና የአገራችንና ቤተ ክርስቲያን አካሔድ እንድንመዝን ያነቃናል ብዬ ነው።

ሐዋርያው "እንዳትጠፋፉ" ማለቱ በነገር፣ በአግቦ፣ በቂም፣ በቁርሾ፣ በቡድን፣ በጎራ ትምክህት በአንደበት ጅራፍ፣ በከንቱ ውዳሴ፣ በውንጀላ፣ በጥላቻ ከቀጠላችሁ መካተቻው የአንድ ወገን ጥፋት ብቻ ሳይሆን የሁሉም ውድመት ነው ማለቱ ነው።

እኛ ሁላችን የምንሻው መጥፋት ሳይሆን መኖርና ማደግ ነው። በየቤተ እምነታችንና በየስምሪታችን እምነታችንን አጠንክረን የእ ግዚአብሔርን መንግሥት ማስፋት ዋና ዓላማችን ከሆነ መንገዱ የንክሻና የጠብ ሳይሆን፣ የመቀራረብና የመወያየት፣ በክርስቶስ ፍቅርና እውነትም የመተናነጽ ጎዳና ነው።

በዚህ አገር ያሉ ሥላሴያውያቱ አብያተ ክርስቲያን በረዥም ዘመን

ታሪካቸው በየፊናቸው ታላላቅ በጎ አስተዋጽዖዎች እንዳደረጉ ለመገንዘብ ጥቂት ንባብና አስተውሎ መመልከት ብቻ ይበቃል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በረዥም ዘመን ታሪኳ የክርስትና ሃይማኖትን ፀረ-ክርስትና ከሆነ ወራሪ ኀይል መክታ በመቆም ለብሔራዊ ዕድገትና አንድነት ያደረገችው አስተዋጽኦ ሊዘነጋ አይገባም።

የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በአገራችን ዘመናዊ ትምህርትንና የበጎ አድራጎት ሥራን በማስፋፋት የሚያኮሩ ተግባራት ፈጽማለች።

ኢትዮጵያውያት ወንጌላውያት አብያተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ በእያንዳንዱ ሰው እጅ ገብቶ እንዲነበብ፣ እንዲጠና፣ ሰውም የሚያ ምነውን እንዲያውቅ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም።

መገናኛ ብዙኃን (ሚዲያ) ኅብረተ ሰብን ለበጎም ይሁን ለክፉ የማንሣሣታቸው ጉልበት ብርቱ እንደ ሆነ የታወቀ ነው። አስተዋይና አርቆ ዐሳቢ በሆኑ ሰዎች የሚቀርብ የሚዲያ ውጤት ክርስቲያኑንም ሆነ ሌላውን ኅብረተ ሰብ ጤናማ አስተያየት እንዲኖረውና በዕውቀት እንዲያድግ ትልቅ ሚና ሊጫወት ይችላል። በቡድናዊ ስሜት ብቻ በሚነዱ ሰዎች የሚቀርቡ ደግሞ አስሚታቸው (impact) አሉታዊ መሆኑ ግልጽ ነው።

ይህ አጭር የግምገማና የአስተያየት ጽሑፍ በሦስቱ ሥላሴያውያት አብያተ ክርስቲያን መካከል የተጀመረው መቀራረብና መነጋገር አንድ ደረጃ ከፍ እንዲል ማበረታታትና ይህንኑ መልካም ግንኙነት የማደናቀፍ አዝማሚያ ያላቸው የሚዲያ አቀራረቦች ሊቃኑ የሚችሉበትን መጠቆም እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስን ማዕከል ያደረገ የሰከነ ተግባቦት በአብያተ ክርስቲያኑ መካከል እንዲዳብር መንገድ መጥረግ ዓላማዎቹ ናቸው።

## 1. በኅትመት ሚዲያዎቻችን ውስጥ የሚታዩ አሳሳቢ አቀራረቦች

በሌሎች የሚዲያ መንገዶች የሚገኙትን ሁሉ ለማየት ዐቅሜ ባይፈቅድ በኅትመት የቀረቡትን ልዩ ልዩ ጽሑፎች ከሞላ ጎደል ለመቃኘት ሞክሬያለሁ። ከሦስቱም አብያተ ክርስቲያን አማኞች የሚጻፍ ምናልባት ሁሉም የቤተ ክርስቲያን "ኦፊሲየላዊ" ልሣናት ባይሆኑም በቤተ ክርስቲያን ያሉ አገልጋዮችና ምዕመናንን ዐሳብ



የሚያንፀባርቁ በመሆናቸው ለውይይታችን በቂ መንደርደሪያ ይሆኑናል።

ብዙ በጎ ነገር እየተጻፈ ቢሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ የሚጻፉትን አንዳንድ ጽሑፎች አጠቃላይ መልክ ስናጤን በምእመናን መካከል ጠብ የሚጭሩ፣ የራስን እምነት በትሕትና ከማስረዳት ይልቅ በሌሎች አስተምህሮና ሥርዐት ላይ ሥላቅና ትችት የሚያበዙ፣ የስሜት ትኩሳት በእጅጉ የሚያይልባቸው፣ ለክርስቲያኑ ኅብረተ ሰብ የዘለቄታ ጥቅም ከማሰብ ይልቅ የዛሬ ማታ "ድል" የሚያጓጓቸው፣ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከኀሊና እውነታ በላይ የቡድን ታማኝነት የሚያሸንፋቸው፣ ከብርሃን ይልቅ ሙቀት የሚጨምሩ ጽሑፎች ሆነው እናገኛቸዋለን። ለውይይት ቅርጽ እንድናገኝ ከዚህ በታች በተዘረዘሩ የጽሑፍ ጤና ጉድለቶች አቀራረብ በዐይነት በዐይነታቸው ሰድሬአቸዋለሁ፦ .

### 1.1 ከፍተኛ የፉክክርና የጎራ ስሜት ርችቶች

በአንዳንድ ጋዜጦቻችንና መጽሔቶቻችን ላይ የሚወጡት ዜናዎች፣ ምስክርነቶችና መጣጥፎች በጣም ጉልሕ በሆነ መንገድ "እኛ-እነሱ" በሚሉ ቀመሮች የተሞሉ ናቸው። ትኩረታቸውም የእንደኛውን ቤተ እምነት አቋም ከፍ በማድረግ "የተጻራሪውን" አኮስሶ ማሳየት ነው። ከአንዱ የእምነት ክፍል ወደ ሌላው እንዴት እንደ መጡ በምስል በተደገፈ ማስረጃና በቃለ መጠይቅ ጎላ አድርጎ በማውጣት የቀረቡ ናቸው።

የሰዎች ከቦታ ወደ ቦታ፣ ከአንድ እምነት ወደ ሌላ እምነት የመዘዋወር መብታቸው የተጠበቀ ቢሆንም፣ ይህ እውነታ ሲታተት በአብያተ ክርስቲያኑ መካከል ስላለው ግንኙነትና ለአንባቢው/ለአድማጩ ስለሚሰጠው ስሜት በርጋታ ማሰብ ይገባል እላለሁ።

እዚህ ላይ አንድ ብርቱ ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፤ "ታዲያ እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሠራውን ሥራ ከመናገር እንቆጠብ እንዴ?" የሚል። ወደ ጽሑፉ መካተቻ ለጥያቄው የሚሆን መልስ በአጭሩ ለመስጠት ይሞከራል።

### 1.2 ችኩል ጥቅለላ (Hasty Generalization)

በጽሑፎቻችንና በስብከታችን ውስጥ በተደጋጋሚ የሚታየው አንድ

ጉድለቶች ያላግባብ ለገበያ ስናለጣቸው ሰዎች አንብበው ከሚማሩት ይልቅ ተበሳጭተውና ተክዘው "እነዚህን ጋዜጤኞች ምነው ሀይ የሚል ጠፋ!" የሚሉበት ጊዜ ይበልጣል፡፡ የሌሎችንም እምነቶች አካሔድ ስንጠቅስ መቼና የት ቦታ ምን ማለት እንዳለብን ማሰብ ዘለቄታዊ ጥቅም አለው::

ጉዳዩ የነገሩ እውነትነት ወይም አጠራጣሪነት ላይ ሳይሆን በገበያ ለሚቀርብ የኅትመት ውጤት እንደዚህ ባለ መንገድ ማቅረብ የሚጠቅም ነው አይደለም? የሚል ጥያቄ ነው፡፡

## 1.6 ሚዛናዊነት ማጣት

በሁላችንም አብያተ እምነት ውስጥ የሚያሳዝን፣ የሚያሳፍር፣ የሚያጠያይቅም ነገር እንደሚገኝ ሁሉ የሚያስደስት፣ የሚያኮራና፣ "ይበል ይበል" የሚያሰኝ በጎ ዐሳብና ምግባርም ይኖራል፡፡ የሚዲያ ውጤቶችን፣ በተለይ የክርስቲያን ሚዲያ ለኅብረተ ሰቡ ሁለቱንም ገጽታ በአንድ ገበታ ላይ በማቅረብ ለምን ፍትሕ አይሠሩም? ሃይማኖታዊ ባልሆነው የውጭ አገር ሚዲያ ሰዎች የሚያዳምጡት፣ የሚያነቡት ክፋውን፣ አሰቃቂውን፣ አስደንጋጩን ነው በሚል ፈሊጥ የሚበዛውን ጊዜ ወደ ጨለማው ወገን ያጋደለ ዜና እንደሚያሰራጩ እንመለከታለን፡፡

እንደ ክርስቲያን የሚዲያ ባለሙያ በቀዳሚ ደረጃ የምስራች ነጋሪነት ጥሪያችን መሆኑን ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ እኛ ስለሌለንበት ቤተ ክርስቲያን ወይም የእምነት ተቋም ስሕተት ወይም ችግር ማንሣት ካለብን የነገሩን ርግጠኛነት አጣርተን፣ የስላቅና የዐውዳሚነትን መንፈስ ሸሽተን በቅን የማበጀት ልቡና ብናቀርበው የምንናገረውን ይበልጥ ተአማኒ ከማድረጉም በላይ መልካም ግንኙነትን ይበልጥ የሚረዳ ተግባር ነው፡፡

አንዳንድ መጽሔቶቻችንን ስመለከት ስለማይቀበሉት የእምነት ክፍል ርዕስ ጉዳይ ካነሱ ሽምጥጥ አድርገው ሁሉንም ነገር አሉታዊ በማድረግ ቢፈለግ እንኳ አንዳች በጎ ነገር እንደማይገኝበት አድርገው ሲያራክሱና ሲያጣጥሉ ይታያሉ፡፡ ልመናዬ "የሚዛን ያለህ!" የሚል ነው፡፡

## 1.7 ነጋሪት ጉሰማ (ርእስ ማስጮህ)

ለመደመጥ ሲባልና ለመነበብ ሲባል ድምፅን ማጉላት እንደሚ



ያስፈልግ ግልጽ ነው፡፡ ነገር ግን ያለ ልክ ስናጋንንና ታምቡር ስንመታ ያንዳንዶች ጆሮ ከቶውንም እንዳይሰማ፣ ከነአካቴው እንዳንደፍነው እጅግ ጥንቃቄ የሚያሻ ይመስለኛል፡፡

ከፍ ያለ ድምፅ ያላቸው አርእስት ለጊዜው አንባቢውን ቢስቡም፣ ረጋ ብሎ ሲያነበው ነገሩ የጩኸቱን ያህል ሆኖ ሳያገኘው ቢቀር ሁለተኛ የመደመጥ ዕድላችንን ያጠባል፡፡ ከዚህም ሌላ በአብያተ ክርስቲያኑ ያሉ ምዕመናን እንዳይቀራረቡ ገደሉን ይበልጥ ያሰፉታል ብዬ እፈራለሁ፡፡

## 2. የሚታዩ በጎ ለዝማሚያዎች

አንዳንድ የሚዲያ ሥራዎቻችን ከላይ የዘረዘርናቸውን የሚመስሉ አሉታዊ ገጽታዎች ቢኖሯቸውም፣ በዚያው አንጻር ደግሞ የተጀመረውን የመቀራረብና አብሮ የመሥራት ጥረት የሚያግዙ፣ ዕውቀትና ጨዋነት የተሞሉ አስደሳች ሥራዎች በየመጽሔቶቻችንና ጋዜጦቻችን ላይ ብቅ እያሉ እንደ ሆነ ተመልክተናል፡፡ አንዳንዶቹን በምሳሌነት እናቅርብ፡-

- የሌሎችን አብያተ ክርስቲያን ሥራ በአዎንታዊ ገጽ ማቅረብ እንዲናገሯም ዕድል መስጠት

"አዶናይ" የተሰኘ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ በአንድ ዕትሙ ላይ ያቀረባቸውን ሦስት አርእስት እንመልከት፡-

*"የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የደስታ መግለጫ አስተላለፉ"* በሚል የወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ እና የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን መግለጫ አውጥቷል፡፡ ቀዳሚ ያደረገውም የመካነ ኢየሱስን መግለጫ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

*"ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ብስራተ ወንጌል ሬድዮ ጣቢያን ተረከበች"* በሚል የደስታ ዜና ዝርዝር ጽፏል፡፡

*"ምዕመናቿ ተገድለውባታል፡- የኮፕት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጥሪ አቀረበች"* በሚል ደግሞ የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በእስልምና አክራሪዎች ስለተገደሉት ዘጠኝ ምዕመናን ያቀረበችውን የእርዳታ ጥሪ ያሰማናል፡፡

በአንድ ዕትም ስለ ሦስቱም አብያተ ክርስቲያን ያለውን አክብሮትና አዎንታዊ አስተሳሰብ ገልጦ እናገኘዋለን፡፡

*እግዚአብሔር በታች እንዲወለዱ አድርጋለች።*

*ባለሙሉ ፊደልና ባለሙሉ ቋንቋ ሆነን በራሳችን ቋንቋ ተናጋሪዎች መሆናችን በዚህቺው ቤተ ክርስቲያን በተሠራው ሥራ ነው። ይህም ለወንጌል መስፋፋት ይሁን ለምድራችን ሥልጣኔ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። ቤተ ክርስቲያኒቱ ለአገራችን ቋንቋ ሥልጣኔ ያደረገችው አስተዋጽኦ መቼም የማንረሳው ጉዳይ ነው።*

## ፫. ስለዚህ ምን እናድርግ፤ ዝምታ ወይስ ቱማታ?

አንዳቸውም የሚጠቅሙ ምርጫዎች ናቸው ብዬ አላስብም። በሁለቱ መካከል ያለ፣ በባሕርዩም የተለየ መልካም አማራጭ አለ፤ ይኸውም በክርስቲያን ሥነ ምግባር የተገራ ጨዋ ተግባቦት ማለት ነው።

"ምንም ጉዳይ እንዳትናገር፤ እኔም ትንፍሽ አልልም፤ እንዳንደራረስ" ማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ በዚህች አገር ላለ የክርስትና ዕድገትና የመንፈሳዊ ሕይወት ብልጽግና እጅግም የሚጠቅም መንገድ ነው ብዬ አላስብም። በፍርሀትና በጥላቻ የተሸበበ ዝምታ መካን ፍልስፍና ነው።

በተጻራሪው ደግሞ "ማንም የፈለገውን ይበል፤ የሚያለቅሱ ያልቅሱ፤ ጦር ይሰብቁም እንደ ሆነ እኔስ ከማን አንሼ?!" በሚል ክፉ ድፍረት ያሻኝን እናገራለሁ፣ እጽፋለሁ ያልን እንደ ሆነም ከንጹሕ መግባባት የተነሣ ሊወሰድ የተጀመረውን በጎ ፅንስ የማስወረድ ያህል አውዳሚ አካሄድ ነው።

እንግዲያው ምን እናድርግ? እንነጋገር። በትሕትና፣ በአክብሮት፣ በዕውቀት፣ በግልጽነት፣ በእውነት፣ በርኅራኄ፣ በመደማመጥ፤ ከዚህ ሁሉ ጋር ደግሞ በሚዛናዊነት።

ስንነጋገር ምን ዐይነት አካሄዶችን እንከተል?

*1ኛ የሌሎችን ቤተ እምነቶች እምነትና ሥርዐት ለማወቅ ጥረት እናድርግ እንተዋወቅ፡-*

የጨለማ በትር ወዳጁንም ሊፈነክት ይችላል። የወንጌላውያኑ አብያተ ክርስቲያን ምዕመናን በዚህ አገር አብረዋቸው የሚኖሩትን ብዙ፣ ሰፊና የዳበረ ባሕል ያላቸውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮና ሥርዐተ አምልኮ ለማወቅ ቅን ጥረት ቢያደርጉ የራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን ሊያበለጽግ የሚችል ብዙ መልካም ነገር በቀሰሙ ነበር።

ልክ እንደዚሁ ካቶሊካውያኑም ሆነ ኦርቶዶክሳውያኑ ወንጌላውያን ምን እንደሚያምኑና የአምልኮአቸውን ሥርዐት መነሻ አስተሳሰብ ጠጋ ብለው ቢያጤኑ ታላቅ ጥቅም በተገኘ። ባጭር ቃል ሚዲያው አንዱ የሌላውን በማወቁ ሒደት ትልቅ ድርሻ ሊያበረክት ይችላል።

*2ኛ የጋራ የሆኑ እምነቶቻችንንና ዕሴቶቻችንን እናድምቅ፡-*

ቶሎ የሚታየን ልዩነታችን እንደ ሆነ ቢታወቅም ዐይናችንን ከፍተን በርጋታ ካየን እጅግ ብዙ አንድ የሚያደርጉን ነገሮች እንዳሉ እናስተውላለን።

- በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክነት እናምን የለምን?
- በየቤተ እምነቱ በተጨማሪነት የምንቀበላቸው ወይም የምንተዋቸው መጻሕፍት ቢኖሩ እንኳ በብሉያትና በሐዲሳት ውስጥ በተካተቱት ስድሳ ስድስት መጻሕፍት የበላይ ባለ ሥልጣንነት ሁላችን እናምን የለምን?
- በኢየሱስ ክርስቶስ ወልድ አምላክነት፣ ኄትነትና አዳኝነት፣ በልደቱ፣ በጥምቀቱ፣ በስቅለቱ በሞቱ፣ በትንሣኤው በእርገቱና በዳግም ምፅአቱ እናምን የለምን?

ከዚህስ የበለጠ ምን ክርስትና አለ? እነዚህን ጉልህን እውነቶች እየተረክንና እያብራራን ብንነጋገር ገጾችስ ጊዜስ ይበቃናልን?

*3ኛ በልዩነቶቻችን ላይ በጥሞና ለመነጋገር መንገዱን እናመቻች፡-*

አንድ የሚያደርጉን አያሌ ነገሮች ቢኖሩም ልዩነቶችም አሉን።

- በቀኖናውያን መጻሕፍት ቁጥር
- በመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም

- በነገረ ድኀን (በድኅነት ትምህርት)
- በሥርዐተ አምልኮ
- ወዘተርፈ....

ልዩነቶችን ተቀብሎ በተመሳሳዩ ብቻ አብሮ መጓዝ አንድ ነገር ሆኖ እያለ፣ የዳበረ ልቡና ስናገኝ ደግሞ ልዩነቶቹን በሰከነ መንፈስ መነጋገር የማይቻልበት ምክንያት አይታየኝም። አንድ ምዕራፍ ያህል ርቀት ቢኖረን ቅን ተግባቦት ደግሞ ርቀቱን በአንድ ጋት እንኳ ቢሆን ሊቀንስልን ይችላል፤ ምናልባት እያደር ርቀታችን የምዕራፍ እርቦ ብቻ ሆኖ ቢገኝስ? ስለዚህም ያለ ወገናዊ ዝመት (bias) ልዩነቶቻችንን ለማጥናት ሚዲያውን በስዘብታ እንጠቀምበት።

*4ኛ ዜና ምስክርነት ስናቀርብ በጥንቃቄ እናድርገው፦*

እግዚአብሔር በጎ ነገር እኛ ዘንድ ሠራ፣ የሰው ሕይወት ተለወጠ፣ ፈውስ ተገኘ የሚል ወይም ይህን የመሰለ ዜና ከማቅረብ መገታት አለብን ብዬ አላስብም። ይሁን እንጂ አንድ ሰው ከሌላ የእምነት ክፍል ወደ እኛ መጥቶ ከሆነ የመጣበትን ወገን የማብጠልጠያ፣ የማናደጃ እኛ እንበልጣለን ብሎ የመፎከሪያ ድምፀት እንዳይኖረው ታላቅ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል። በዚያውም ላይ በጽሑፍም ይሁን በቪሲዲ፣ ዲቪዲ ወይም ሲዲ ለሕዝብ የሚቀርበው ምስክርነት እያንዳንዱ ቅንጣት እውነተኛነት በተቻለ መጠን ማረጋገጥ ያሻናል። ምናልባት አንዳንድ ጊዜ ያ ሰው ወይም ቡድን የመጣበትን የቀድሞ የእምነት ክፍል መጥቀስ ጨርሶ ላያስፈልግ ይችላል። የማንንም ቤተ እምነት ወይም ማኅበር ሳይጠቅሱ ሰዎች የሚያምኑነትን እውነት ለመናገር አይችሉም እንዴ?

*5ኛ የሚሰሙንና የሚያነቡን የእኛ እምነት ቤተ ሰቦች ብቻ እንዳልሆኑ ልብ እንበል፦*

ለገበያ የቀረበ ማንኛውም የኅትመትም ሆነ የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ውጤት ተደራሲው ብዙ ዐይነት ሊሆን ይችላል።

- የራሳችን ቤተ ክርስቲያን ሰዎች
- የሌሎች አብያተ ክርስቲያን አማኞች



- የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታዮች
- የመንግሥት ልዩ ልዩ አካላት
- እምነት የለሾች

ይህ ሁሉ አድማጭና አንባቢ ባለበት ሰፊ ድብልቅ አገር ውስጥ የሚባለው ሁሉ ሊያስከትል የሚችለውን ሳናጤን ሚዲያውን ያለ አስተዋይ ፍተሻ መስደድ በሳቢያው የሚመጣውን አሉታዊ ውጤት እንድንጋፈጥ ሊያስገድደን ይችላል።

የመናገርና የመጻፍ፣ ዐሳብን በነጻ የመግለጽ መብታችንን እየተጠቀምን መልእክቶቻችንን ለማስተላለፍ ዕድል ስላገኘን ቸሩ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን። የዚህንም አገር ሰላምና ነጻነት ይጠብቅልን። ይህን ታላቅ ዕድል በየትኛውም የክርስትና እምነት ክፍል ያለን የሚዲያ ሰዎች በጥንቃቄና ሰዎችን በሚጠቅም፣ ለልዑል እግዚአብሔርም ክብር በሚሆን መንገድ እንጠቀምበት።

ስብሐት ለአብ

ስብሐት ለወልድ

ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ

አንድ አምላክ

አሜን።

# አንጡራ ወንጌል

"በብዙ ዐይነትና በብዙ ጎዳና" የሚናገረው ጌታ አንድ ዋና ባሕርይ ቁርጥ ያለ መልእክት ማቅረቡ ነው። የመናገር በሽታ የለበትም፤ የራሱን ድምፅ የመስማት ጉጉት አይቀሰቅሰውም፤ ለጌጥ ለጨዋታም አይሰለፍም። መልእክቱን ያውቀዋል፤ ግቡም የሰው ልጅ ደኅንነት ነው። እግዚአብሔር በቃል ይሁን በሌላ ወደ ሰው የሚሰደውን መልእክት ባወጣ ያወጣው አይወረውረውም፤ "የምልካት ቃሌ የምሻውን ታደርጋለች እንጂ በከንቱ ወደኔ አትመለስም" ማለቱ ማነጣጠሩን፣ የማይስትም መሆኑን ያመለክታል።

እኛ ስንናገር ወይም ስንጽፍ፣ በተለይ የወንጌል መልእክት ለማስተላለፍ ስንሞክር የምንናገረውን አጥርተን እናውቃለን ወይ? ወይስ "ግብሩን እንደማያውቅ ተዋናይ" መድረክ ላይ አንጉል እንወራጫለን? "ወንጌሉን የማያውቅ ማነው? ደሞ እርሱን መናገር ምን ያስቸግርና ነው ለውይይት የሚነሣ?" የተባለ እንደ ሆነ፣ የምንለው ያልገባቸው ወይም ያደናገራቸው ሰዎች መልስ ይስጡበት እላለሁ። በየሰንበቱ ቤተ ክርስቲያን እየሄደ በስብከቱ ግራ እየተጋባ ሲብስም እየተበሳጨ የሚውለው ምዕመን መልስ ይስጥበት። ያወቅነውም እንኳ ቢሆን ይህን የተባረከ የምሥራች ቃል፣ ይህን አንድዬ ስብከታችንን አገላብጠን ማየት ያበለጽገናል እንጂ አይጎዳንም።



## ወንጌሉ ምን አይደለም?

የሥነ ምግባር ሐተታ አይደለም፤ "...ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም" በሚለው ዘይቤ "ለጤናም ለማኅበራዊ ኑሮም መቸም ይጠቅምሃል፤ ኪስህ እንዳይራቆት፣ ራስህን እንዳትታመም፣ ሰው እንዳይጠላህ ይህቺን ኪኒን ዋጣት" የሚል አስማታዊ ምክር አይደለም። የክርስቶስ ወንጌል ሰዎችን ከእኩያን አስተሳሰቦችና ድርጊቶች አላቆ ገባርያነ ሠናይ (መልካም አድራጊዎች) እንዲሆኑ ማስቻሉ እርግጥ ነው። ሌቦችን ንጹሐን ለጋሦች ያደርጋቸዋል፤ የተሳዳቢዎችን አፍ ቀድሶ ባርኮትን ያስለምዳቸዋል፤ የጨካኞችን ልብ ያለሰልሳል። ሆኖም ሌሎች ብዙ እምነቶች ተመሳሳይ ሞራላዊ ምክር ለጋሾች ናቸውና የወንጌል ልዩቱ (uniqueness) ምንድነው? ቀዳሚ ማንነቱ ከዚህ ይጠልቃል። ደግሞም በጎ ምግባር የወንጌል ሥራ ውጤት እንጂ ወንጌሉ ራሱ አይደለም።

የድንቃድንቆች ርችት ብቻ አይለም። ምን ማለቴ ነው? ሰውየው ወደ ጸሎት ቤት ሄዶ ልጁ ከቡዳ መንፈስ ብትላቀቅለት፣ ንግዱ ዐይቶ የማያውቀውን ትርፍ ቢያስገኝለት፣ ወይም በተንኮል ሲሸምቅበት የነበረው ጎረቤት ጠላቱ እግሩ ላይ ወድቆ ቢለማመጠው፣ ... የሆነለት በጎ ነገር ሁሉ መልካም ሆኖ ሳለ ብቻውን የወንጌል ቃል አይደለም። ይህ መተርጎም አለበት፤ በጠቅላላው የወንጌል መልእክት ውስጥ ተገቢ ሥፍራውን መያዝ አለበት። "ወይ ጉድ... ወይ ጉድ... ወይ የጌታ ታምር..." ብቻ ከማለት አልፎ ሙሉ የሆነ ወንጌል እንዲያቀርብ ይጠበቃል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ብርቱ ኀይል አለው፤ የዲያብሎስን መንግሥት እያፈረሰ የእግዚአብሔርን መንግሥት ያውጃል። በድንቅና በተአምር መገለጡ የሚጠበቅ፣ ሲፈለግም የሚገባው ነው። ተአምራቱ ሁሉ ግን ከሚያስተላልፉት መልእክት በላይ ሆነው ያለ ሁነኛ ፍቺ እንዳይቀሩ መጠንቀቅ ግድ ነው። ተአምር ምልክት ነው፤ መጠቆሚያ፣ ማስረጃ፣ ማሳያ፣ የክርስቶስ ስም ያለውን ብርቱ ኀይል፣ የእግዚአብሔርን ታላቅ ርኅራኄ መግለጫ ነው። እንግዲያው 'የመግለጫ ሠሌዳ ሆኖ የቆመው ለየትኛው እውነት ነው?' ብሎ መጠያየቅ ያሻል።

የቡድን ወይም የድርጅት ማስተዋወቂያ ጥሪም አይደለም። ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን (ከነ ስማቸው ወንጌላውያን) የወንጌሉን ቃል ሲዘሩ ሩጫቸው 'እዚህ ቦታ፣ እዚህ ጸሎት ቤት፣ እዚህ ስብሰባ ላይ ብትገኙ፣ ይህን ቀመር ብትሠሩ በርግጥ

ትድናላችሁ' አይበሉ። በእኛ ቋንቋ ብቻ ለሚናገሩና አብረውን ለሚውሉ ብቻ የተገለጠ አድርገን ወንጌሉን የክለባችን መተዳደሪያ ደንብ አናድርገው። የክርስቶስ ወንጌል አርቲፊሻል አጥሮችን እንደሌሉ ነው የሚቆጥራቸው። እኛም አንጡራውን ወንጌል እንፈልገው። እንግዲያው የወንጌል ቡጡ፤(ዋናው) ምንድንነው?

*ወንጌል፡- ክርስቶስ ማእከሉ ነው፤ መስቀል ስብከቱ ነው፤ እምነት ጥሪው ነው።*

## 1. ክርስቶስ ዋናው ነው (ሮሜ 1፥1-5)

የአዲስ ኪዳን መካከለኛ የተባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌሉ ዋና ትኩረት ነው። እውነት ለመናገር ብዙዎችም እንዳሉት ክርስትና ክርስቶስ ነው። ክርስቶስን ወደ ጎን የሚያደርግ ወይም እንዳላየ ለማለፍ የሚሞክር ወይም ከሌሎች እኩል ሊያስቀምጥ የሚቃጣ ወይም ለንግግር ማሳመሪያ ብቻ የሚጠቅሰው ሰው ወንጌልን አላወቀውም። ወንጌል ስለ ክርስቶስ ነው። ድሩም፣ ማጉም፣ ቋሚውም፣ ወራጅ ምሰሶውም፣ መሠረቱም ቢሆን መሲሑ ኢየሱስ ነው። ስለ ሰው ማንሣታችን ባይቀርም (በወንጌል የሚድነው ሰው ነውና) ስለ ድነት በረከቶች መዘርዘራችን ቢጠቅምም፣ የወንጌል አንጽሮት (focus) የኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛ አዳኝነትና ጌትነት ነው። ወንጌልን የምንሰብከው ሌላ አማራጭ ስለሌለ ነው።የሰው ልጅ ወዲህም ወዲያም መፈናፈኛ በሌለው ሁኔታ ላይ ወድቋል፤ ከየትም ፍልስፍና (ሃይማኖት) የተመዘዘ የመዳን ክር የለም። ክርስትና አጥላይ (exclusive) እምነት ነው። ይህ አቋሙ ሰላማዊ አብሮ መኖርን የሚጣረር ያስመስለዋል፤ ከሌሎች መሥመሮችም ጋር ሊያጋጨው ይችላል። እውነቱ ግን ይኸው ነው። መንገዶች ሁሉ ወደ ሮም ቢወስዱም፣ የሕይወት መንገድ ግን አንድ ብቻ ነው። "በእኔ በቀር" የሚለው የጌታችን ግልጽ ንግግር ደባል ለማስተናገድ አይመችም።(ዮሐ14፤6 )

ክርስቶስ የሆነው ኢየሱስ፣ ሰውም አምላክም መሆኑ፣ የእግዚአብሔር ዕቅድ ሁሉ መሰብሰቢያ መሆኑ፣ ትምህርቱና ሕይወቱ የሚጠቀሱ ናቸው። ወንጌሉን ስንሰብክ ኀጢአተኞችን ሁሉ የምንጠራው ከዚህ ሰው ጋር ርግጠኛ ግንኙነት እንዲያደርጉ ነው። ጌታም ባልንጀራም ሊሆናቸው የሚችለውን ኢየሱስን "እሺ ሁንልኝ" እንዲሉት ነው።



ሐዋርያው (የወንጌል መልእክተኛው) ጳውሎስ ግራ ቀኝ ውልፍት በማያሰኝ ሁኔታ የወንጌልን ርእስ ጉዳይና ባለቤቱን ገለጠልን፡ - *"ወንጌሉም ስለ ልጁ፣ በሥጋ ከዳዊት ዘር ስለሆነ፣ በቅድስና መንፈስ ደግሞ ከሙታን በመነሣቱ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑ በኀይል ስለ ተገለጠው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።" (ለሮሜ ሰዎች የጻፈው መልእክቱ፣ ምእራፍ 1፥3-4።)*

## 2. መስቀሉ ስብከታችን ነው (1ኛ ቆሮ. 1፥18-31)

ወንጌል ስንናገር የምናጎላው ክንዋኔ የክርስቶስን የመስቀል ሥራ ነው። መስቀሉን ያስገደደው የሰው ኀጢአት ነውና ስለ ኀጢአት መናገራችን የማይቀር ነው። አንዳንዶች "ኀጢአት" የሚለው ቃል ሲጠቀስ አይወዱም፤ በሌሎች በተለሳለሱ ቃላት ቢተካ ይመርጣሉ። ለምሳሌ፡-. የበደለኝነት ስሜት፣ ውስጣዊ ግጭት፣ ችግር ወዘተርፈ። ግን መርዝን በስሙ ጠርቶ መታከም ይበጃልና እርግጥ ፍርጥ አድርገን ሰው ኀጢአተኛ መሆኑን መንገር አለብን። ኀጢአተኛ መሆኑን እንድንናገር መጽሐፍ ያደፋፍረናል። ኀጢአት ካለ ቅጣት አለ፤ ድርጊታቸችን ሁሉ በጻድቅ እግዚአብሔር ፊት ተገልጧል።

"ደም ሳይፈስ ስርየት የለምና" ኢየሱስ ክርስቶስ ንጹሕ ደሙን በመስቀል አፈሰሰ። ቁጣም ፍቅርም በአንድ ጊዜ ተገለጠ፤ ቁጣው በልጁ በኢየሱስ ላይ አረፈ፤ ኀጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸክሟልና (1ጴጥሮስ2፤24)። ፍቅሩ ለኛ ተዘረጋ፤ ዕዳችንን ከፍሎ ከሞት እንድንድን አድርጓልና።

በሞቱ ስርየታችንን ያስገኘው ጌታ ኢየሱስ በትንሣኤው ጽድቃችንን አረጋግጧል። ንጽሕ መሥዋዕትነቱን ሙሉ ለሙሉ መቀበሉን አባቱ ልጁን ከሞት በማስነሣት መስከረ። የመስቀሉን ጎዳና የማንሄድበት አቋራጭ ወንጌል የለም፤ ወንጌልን መናገር የክርስቶስን ሞት መናገር ነው።

በስመ ወንጌል የሚነገር ስንት የገለባ ክምር በመስቀሉ ቃል መበራየት አለበት። ኢየሱስ ክርስቶስ ለኀጢተኛው ለእኔ መሞቱን በርሱ ቤዛዊ ሞት እኔ አማኙ መትረፌን የማይናገር ወንጌል ሓሳዊ ወንጌል ነው። ብርቱው ሰባኪ ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር ዐይኑን አያሽም፤ በማያወላዳ ማተበኛነት አጥብቆ ይናገራል፤ እንዲህ እያለ *"...በመካከላችሁ ሳለሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ያውም የተሰቀለውን እርሱን ብቻ እንጂ ሌላ እንዳላውቅ ወሰኝ*

*ነበርና..."፤ "...እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን" (1ቆሮ. 2፥2፤ 1፥23)።*

### 3. እምነት የወንጌል ጥሪ ነው (ሮሜ 1፥1-5፤ 3፥21-26)

የተሰቀለው ክርስቶስ ሲሰበክ እግዚአብሔር የሚያድነው የሚያምኑትን ነው። ሰው እንዲድን ከራሱ ዘንድ የሚያዋጣው ወይም የሚያደርገው ምንም ነገር የለም፤ ያምናል እንጂ። ምን ያምናል? ማንን ያምናል? በሥጋ የመጣውን ወልድ አምላክ ያምናል፤ እርሱን የሙጥኝ ይላል፤ ከሌሎች ሁሉ ላይ ሙጥኝ ታውን ያነሣል። አንድም እምነት ስንል፣ የእግዚአብሔርን ተስፋና ኪዳን የምንይዝበት መንጠቆ ነው። በሥራዬ ከነአካቴው ልድን የማልችል ተስፋ ቢስ ሰው፤ ኢየሱስ በምትኬ የሠራልኝን ጽድቅ እቀበላለሁ። ፍዳዬን ተቀብሎ ነጻ እንዳወጣኝ አረጋግጣለሁ። ያምናል ስንል ደግሞ እግዚአብሔር ስለ ልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ሁሉ ይቀበላል ማለት ነው። "የምወደው ልጄ እርሱ ነው፤ እርሱን ስሙት" ብሎ እንዳለው። ይህ አማኝ ስለ ራሱም ሆነ ስለ ሰው የተገለጠውን እውነታ ይቀበላል።

ይህ እምነት ኀጢአተኛውን ሰው ወደ ንስሓ፣ ወደ ኑዛዜ ብሎም ወደ ውሳኔ ያደርሰዋል። ወንጌልን ለሰዎች የምንሰብከው ልናዝናናቸው፣ ልናስገርማቸው ወይም ልናስበርግጋቸው አይደለም፤ እንዲያምኑ ልንጠራቸው ነው። ወንጌል የእምነትን ምላሽ በብርቱ ይጠይቃል፤ "ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ሐዋርያነትን ተቀበልን" ብሏል ሐዋርያው ጳውሎስ።

### የወንጌል ገበታ ስንዘረጋ

- ለዚህ ዘመን ሰዎች ወንጌልን ተርጓሚዎች እኛ የክርስቶስ የምስራች በርቶልናል የምንል ሰዎች ነን፤ ስለ ዚህ አሁን ላሉ ሰዎች እንዲገባ ወንጌላችንን ዐውደ ገብ (contextualize) እናድርገው። በቋንቋ ረገድ ቢሆን መሠረቱን ሳንለቅ ተደማጭ እናድርገው። መንፈስ ቅዱስ ለትውልዱ የሚሰማ ድምፅ ሊፈጥርብን ይቻለዋል። ጆሮአችን ለሰማዩም ለምድሩም ይንቃ፤ የማስታረቅ ቃል እኮ ይህንን ንቃት በብርቱ ይጠይቃልና።

- የተራክቦ ነጥብ (point of contact) ይዘን መጀመር ታላቅ ጥበብ ነው። በሐዋርያት ሥራ ከቀረቡት የወንጌል ስብከቶች ሦስቱን ሳጤን ነበር፤ ምዕራፍ 2፣ ምዕራፍ 10 እና ምዕራፍ 17። በመጀመሪያው ላይ ሐዋርያው ጴጥሮስ በኢየሩሳሌም ለበዓል የመጡ ሰዎች በሐዋርያቱ ላይ ስለተፈጠረው ዐዲስ ክስተት ከሰጡት አስተያየት ተነሥቶ ለክስተቱ ምላሽ በመስጠት አያይዞ ደግሞ ከሞት የተነሣውን ጌታ መሲሕነት በይፋ አበሠረ። በሁለተኛው ላይ መልአክ ተገልጦለት መልዕክተኞችን የላከበትን የመቶ አለቃ ጥያቄ በማስተናገድ አካሔድ የቆርኔሌዎስን ፈሪሐ እግዚአብሔር አክብሮ የጌታችንን ብቸኛ አዳኝነት ገለጠ። በሦስተኛው ሐዋርያው ጳውሎስ በሜዳ ላይ ካጋጠመው ጉዳይ ተነሥቶ እግዚአብሔር ያዘጋጀውን ልዩ ሰው አስተዋወቃቸው። መነሻ እናግኝ፤ ይኸውም ከሕይወት፣ ከታሪክ፣ ከባሕል ወዘተርፈ ሊሆን ይችላል። መድረሻውንም አስረግጠን እናስታውቅ።

- አቀራረባችን አንድ ድብልብል ኳስ ይዞ የሰው ግንባር ላይ እንደሚወረውር ባይሆን ጥሩ ነው። 'ቢቀበል ይቀበል፤ ቢገባው ይግባው፤ ባይገባው...' በሚል ስንፍና "በወንጌል ዱላ" አንማታ። በርኃታ፣ በትዕግሥት እናስተንትን፤ ሊረዱ የሚችሉበትን ቋንቋ እንጠቀም፤ ሊይዙ በሚችሉት መጠን እንግለጽ።

- የሕይወትን ውስብስብ ያላገናዘበ የችኮላ መልስ አንወርውር፤ በውትወታም ኀላፊነት ለጎደለው ውሳኔ አናጣድፍ። ለሕይወት እውነተኛ እንሁን፤ ወንጌሉ ራሱ እውነተኛ ስለ ሆነ።

*"አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፤ መከራን ተቀበል፤ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፤ አገልግሎትህን ፈጽም" ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ 2፥4-5።*

# ሥነ ምግባር በሦስተኛው ሺህ ዘመነ ምሕረት¨

ሦስተኛው ሺህ ዓመተ ምሕረት ብቷል። አዲስ ንጋት እንጠብቃለን፤ የብሔራዊ ተስፋ ራእይና የማኅበራዊ ልማት ጮራ እንዲፈነጠቅ ጉጉት አለን። በልዩ ልዩ የኑሮ ዘርፎች የሚያኮራ ኢትጵያዊነት እንዲለመልም፣ ከዓለም አቀፍ ኅብረተ ሰብ ጋርም ፍሬ ያለው መስተጋብር እንዲኖረን እንሻለን።

ይህ በጎ ምኞትና ሕልም በመጠኑ እንኳ እውን የሚሆነው የአስተሳሰባችንንና የእንቅስቃሴያችንን አካሔድ በውል የፈተሽን ጊዜና ይህ የኑሮ ዘይቤ ፍተሻ ከሚነግረን ተነሥተን "እንግዲያው ምን እናድርግ?" ብለን ተግባራዊ ጥያቄ ያነሣን ጊዜ ነው።

የአኗኗርን ዘይቤ ከሚቃኙት ብዙ ነገሮች አንዱና ዋናው የሥነ ምግባረ አስተሳሰባችን ነው። ስለሆኑ ሜዳው እጅግ ሰፊ በሆነበት በአሁኑ ዘመን ስለ ብሔራዊ ሥነ ምግባር፣ ቀድሞ ነገርስ ስለ ግለ ሰብ ሥነ ምግባር ፋይዳ ያለው ውይይት ማድረግ ይቻላል ወይ? ከእኛ ቁጥጥር ውጪ በሆኑ ብርቱ የተፈጥሮና ዓለም አቀፋዊ ግፊቶች የምንንገዋለል መሆናችን እየታወቀ እኛ ባሠመርነው ጎዳና ለመሔድ መውተርተራችን ቂሎች አያሰኘንም ወይ? ወዘተርፈ... የሚሉ ጥያቄዎች ቢደቀኑብንም የእነዚህን ጥያቄዎች ሩምታ ሳንፈራ ዐዲስ በባተው ሺህ ዓመት ለሥነ



ምግባር ዕድገትና ጤንነት የግልና የጋራ ድርሻችንን ማጤን አስፈላጊ ነው። "ሥነ ምግባር በ3ኛው ሺህ ዘመነ ምሕረት" የተሰኘው ይህ አጭር ጽሑፍ ርእሰ ጉዳዩን የመመልከቻ ሦስት ማማዎችና አንድ የተግባር መንደርደሪያ ጎዳና አካቷል።

1. የመጀመሪያው በ2ኛው ሺህ ማብቂያ ላይ ዓለም አቀፋዊ የሥነ ምግባር አስተሳሰብ ዋና ዋና ገጽታዎችን የሚዳስስ ሲሆን፣
2. ሁለተኛው ደግሞ በአገራችን አሁን የሚታየው የሥነ ምግባር ሁኔታ ምን እንደሚመስል በግርድፉ የሚቃኝ ነው፤
3. ሦስተኛው ትኩረት የሚሹ አገራዊ ሥነ ምግባራዊ ጉዳዮችን በጥቂቱ ይነካካል፤
4. አራተኛው መርሐ መር የሆነ ሥነ ምግባር ለብሔራዊ ትድግና እንዴት ሊውል እንደሚገባው አቅጣጫ የሚጠቁም መንደርደሪያ ነው።

## 1. የ2ኛው ሺህ ዘመነ ምሕረት ማብቂያ የሥነ ምግባር ርእዮተ ገጽታ

ዛሬ የደረስንበት የአስተሳሰብ ደረጃ ድንገት ከሰማይ ዱብ ያለ እንግዳ ደራሽ ሳይሆን በየዘመናቱ በተነጠፈ የፍልስፍና፣ የሃይማኖት፣ የማኅበራዊ መስተጋብር፣ የባሕል ጡቦች ላይ እየተገነባ ያደገ፣ በየወቅቱም መልኩን እየለዋወጠ የተከሰተ የጋራ ኑሮ ሕንፃ ነው። ስለሆነም እነዚህ የሥር መሠረት ንጣፎች ምን ይመስሉ ነበር? ባሁኑ ጊዜስ እየገነነ የመጣው የአስተሳሰብ ዐይነት ምንድነው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

ሥነ ምግባር የዘመኑን የፍልስፍና ፈለግ ተከትሎ ይሄዳል፤ "ከየጥሻው የሚመዘዝ" የሥነ ምግባር ዝንቅ ቢኖርም ሜዳው ላይ የነገሠው የአስተሳሰብ ኀር የአብዛኞቻችንን አመለካከት የመቅረጽ ብርቱ ጉልበት አለው። ለመሆኑ በሞራል/ሥነ ምግባር ረገድ ቀደም ባሉት ዘመናት ይታሰብ የነበሩትና አሁንስ እየታሰበ ያለው ምንድነው?

### 1.1 የሞራል (የግብረ ገብ) ተፈጥሮ

ሞራላዊነት ተፈጥሮአዊ ነው ወይስ ምክንያዊ (reasonable)?

ሁሉም ሰው ዘንድ ይገኛልን? የሞራል ዕሴቶች ወጥነት ባለው መንገድ ዓለም አቀፋዊ ናቸው ወይስ ባሕላዊ/አንጻራዊ? የግብረ ገብ ብያኔ መሠረቱ ማነው? ምንድነው?

በሃይማኖት ምሁራን ዘንድ "የበጎነትንና የእግዚአብሔርን ግንኙነት ማጤን ሃይማኖት በሥነ ምግባር ላይ ያለውን ተጽእኖ ለማመዛዘን ይረዳል።" የሚል ዐሳብ አለ። በመጽሐፍ ቅዱሳዊው አስተሳሰብ ሥነ ምግባር ከንጽረተ ዓለማችን (worldview) ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር በባሕርዩ መልካም ስለሆነ የእርሱ መልካምነት የምግባር ሁሉ መለኪያም ምንጭም ሆኖ ያገለግላል።

በግሪክ ፍልስፍና ግብረ ገባዊነት በአእምሮ ስሌት (reason) የሚደረስበት ሆኖ የሰዎችን እኩያን አስተሳሰቦችና ድርጊቶች እየተጻረሩ ሠናያት ባሕርያትን የመገንባት ጥረት ነበር። ይህም ለአፍላጦን (ፕሌቶ) "እውነኛውና ዘላለማዊው መልካም ነገር የቱ ነው?" የሚለውን ጥያቄ የአእምሮ ችሎታን ተጠቅሞ ለመረዳት መሞከር ሲሆን፣ ለአርስጣጣሊስ ደግሞ ከሰው ተፈጥሮና ችሎታ ጋር የሚጣጣሙት ሠናያት ተግባር ምን እንደ ሆኑ መመርመር ነበር።

ኢስጥኢኮች (Stoics) የተባሉት ፈላስፎች ከተጨባጭ ሁኔታዎች የመጠቀ፣ በአእምሮ ስሌት የሚገኝ ግብረ ገባዊነትን ሲያጠብቁ ኤፌቆሮሳውያን (Epicureans) የተባሉት ደግሞ አካላዊ/ቁሳዊ ደ ስታ መፈለግን ትልቅ ዋጋ ያለው ነገር አድርገው ይቈጥሩ ነበር። ያን ጊዜ የጀመሩት እነዚህ በተፈጥሮአዊና በልቡና በሚታሰበው በአእምሮአዊ ስሌትና በየዕለት ተሞክሮ መካከል የተፈጠረው ውጥረት በሞራል ፍልስፍና ውስጥ እስከ ዛሬ ድረስ ለቀጠለው ሙግት መነሻ ናቸው። አውግስጢኖስ፣ ቶማስ አኩዊነስ፣ በኋላ ደግሞ ኢማኑኤል ካንት በእነዚህ ሙግቶች ዙሪያ የእምሮን ድርሻ እያጎሉ ሲያስተምሩ ቆዩ።

## 1.2 የጉዕሣን ዘመናት ቅኝት

ዛሬ ከትናንት የተለየ ቀን ቢሆንም ከትናንት የቀጠለ ቀንም ነው። ትናንት ወደ ዛሬ ውስጥ ገብቷል፤ ስለዚህ የኋሊት መመለስ ለ ዛሬ ዕውቀት መነሻ ነው።



**1.2.1** *የጨለማው ዘመን (Dark Ages) ከ476-1000ዓ.ም.:* - ይህ የመካከለኛው ዘመን የመጀመሪያ ወቅት የጨለማ ዘመን በመባል ይታወቃል። በታሪክ ሊቃውንት ከየትኛውም የታሪክ ጊዜ አንጻር ሲተያይ ሥልጣኔና ዕድገት ያልታየበት እንዲሁም ድንቁርና የነገሠበት ዘመን ተደርጎ ይወስዳል።

**1.2.2** *የዕውቀት ዳግም ልደት (Renaissance) ዘመን ከ1350- 1600ዓ.ም.:-* ይህ ዘመን ዕውቀት የተስፋፋበት፣ ሳይንስ፣ ሥነ ጥበብ፣ ቅኔ፣ ሥነ ሕንፃ ወዘተ... በብርቱ የተንቀሳቀሰበት የሥልጣኔ ጅማሬ ተደርጎ የሚወሰድ ዘመን ነው።

**1.2.3** *ለብሩሃ ኅሊና ዘመን (Age of Enlightenment) 1700-1900ዓ.ም.:-* በአውሮጳ በዋናነት የተነሣውን የፍልስፍና ዐይነት የሚያሳይ ሲሆን፣ ይህም ዘመን አመክንዮ (Age of reason) የሚባል ነው። ሥነ ውብት፣ ሥነ ምግባርና ሌሎችም ዘርፎች በአጠቃላይ እውነትና ሐሰት፣ እኩይና ሠናይ የሚወሰነው በሰው የአእምሮ ማሰላት ኀይል ወይም በአመክንዮ ብቻ ነው የሚል አቋም አለው። ይህ ወቅት ዘመናዊም (Modern Age) ይባላል።

**1.2.4** *ድኅረ ዘመናዊነት ከ1950ዎቹ ጀምሮ እስካሁን ያለው:-* ከሌሎቹ ይልቅ በአዲሱ ሺህ ዓመት ላይ ምናልባት የበለጠ ጫና የሚያሳድረው ይህ የአስተሳሰብ ስልት ስለሆነ ዛሬ ስለምንነጋገርበት የሥነ ምግባር ርእሰ ጉዳይም አነጋጋሪ የሆኑ አቋሞች በውስጡ ስለሚገኝ በተነጻጻሪ ምንነቱን ጥቂት እንዘርዝርና እንየው።

## 1.3 *ድኅረ ዘመናዊነትና የሥነ ምግባር ለተያየ*

አሁን በምዕራቡ ዓለም እየገነነ የመጣ (እታሞ አስደልቆ ዘመቻ ባያውጅም) በፍጥነትና በለሆሳስ ወደ ሰው አስተሳሰብና አኗኗር ውስጥ እየዘለቀ ያለ አመለካከት ነው። አሁን ሉል አቀፋዊነት (ግሎባላይዜሽን) የወትሮ ቋንቋ በሆነበት፣ ምድርም በጠበበችበት ሁኔታ እዚያ የገነነ አስተሳሰብና አኗኗር ሳይመሽ እዚህ መድረሱ ስለማይቀር ምንነቱን ማወቅና ከሁኔታችን አንጻር አቋሙን ማሔስ ተገቢ ነው።

ድኅረ ዘመናዊነት ብዙ ልዩ ልዩ ፍቺ ቢሰጠውም በማያሻማ መንገድ ሁሉ የሚስማማበት የዘመናዊነት (modernism) ፍልስፍና ተቃራኒ፣ ወዲያውም የዘመናዊነት አይቀሬ መደምደሚያ መሆኑ ነው። እንግዲያው ራሱ ዘመናዊነት ምንድነው?

የዘመናዊነት (modernism) ጅማሬ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ነበረው ፈላስፋ ሬኔ ደካርት ይወስደናል። እርሱ እንዲህ አለ፡- "አስባለሁ፤ ስለዚህ አለሁ" - &I think, therefore I am"

ይህ ትወራ (theory) ሁሉን ነገር ከመጠራጠር ይጀምርና የሰውን የማሰላት ሥርዐት (አመክንዮ) ያነግሣል። እውነተኛ ዕውቀት እንዳለ የሚያምን፣ ይህም ዕውቀት በምክንያዊነት (reason) ብቻ ሊደርስበት ይቻላል ብሎ የሚያስብ አመለካከት ነው። በተጨማሪም ዓለምን በሁለት ይከፍላል፡- ተጨባጭ ቁሳዊ ዓለም እና ኢ-ተጨባጭ/ግላዊ/መንፈሳዊ ዓለም በማለት። ሲቀጥልም፦

- ዓለም ያለችው በሳቢያና በውጤት ተዋቅራ ነው፤ ለውጤቶች ሁሉ ሳቢያ አላቸው። ስለዚህ ነገሮች በፍተሻ፣ በማስረጃ ይታወቃሉ፤
- ዕውቀት በመረጃ ላይ (ደግሞ - ክፉም ባልሆነ) የተመሠረተ ነው) መሠረቱ ጥሩ ነው፤ በቴክኖሎጂና በሳይንስ ግኝቶች የኢኮኖሚ ዕድገት ማግኘት ይቻላል፤ ዓለም የተሻለች እየሆነች ትሄዳለች፤
- ሰው በመሠረቱ ጥሩ ነው፤ በምርምርና በሥነ አመክንዮ አንድ ቀን ችግሩን ሁሉ ይፈታል፤
- ማንም ግለ ሰብ ነጻ ነው፤ መብቱ ሊከበር ይገባል፤

ቀጥሎ ደግሞ ላለፉት ሁለት መቶ ዓመታት ተንሠራፍቶ የነበረውን ይህን "ዘመናዊ" አስተሳሰብ የሚጻረረው ድኅረ ዘመናይነት ዋና ዋና መልኮች ባጭሩ እንዘርዝር፡-

- ታሪክን በሚመለከት ድኅረ ዘመናይነት በሐቅና በልብ ወለድ መካከል ያለውን ልዩነት ይድጣል። ታሪክ ጸሐፊው በራሱ ከሚፈጥረው በስተቀር ምንም እውነታ የለም የሚል አቋም ይይዛል። ሪቻርድ ሰንቴራል እንደሚለው ከሆነ "ታሪክ 'እውነት' አይደለም፤ ጭጋግ በሸፈነው መነፅር የታየ፣ የባሕልና የሕዝብ ልማድ 'እንዲህ ሆኖ ቢሆን ምን አለበት' በሚል ዐጉል ምኞት የተጥበረበረ ትዕይንት ነው።"
- በሥነ ጽሑፍ ረገድ ድኅረ ዘመናዊነት ለነገሮች የሚሰጡ የትርጉሞች ብዛትን ያበረታታል፤ በየትኛውም ንግግር ወይም ቋንቋ ወይም ጽሑፍ ውስጥ ቋሚ ትርጉም የለም፤ ማንም አንባቢ "ለትክክለኛው" ትርጉም ሳይጨነቅ ገቢታው ላይ የቀረበውን ባሻው መንገድ መተርጎም ይችላል ባይ ነው።

ሌሎች ገጽታዎቹ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

### 1.3.1 ዘመናይነትን መጻረር/መነሻ ሀሳቦቹን መጠየቅ

ድኅረ ዘመናውያን እንዲህ ይላሉ፡- "ዘመናዊነት የሰፈረው ተስፋ አልተፈጸምም፤ ይልቁን አዳዲስ ጣጣ ይዞብን መጣ፤ ዕቡይ ሆኖ ለጥያቄዎቻችን መልስ የያዘ ያህል ፎከረ። አሁን ግን ስናየው እኛ ምንም አናውቅም፤ ትርጉምም የለም። ይህም ቀዋሚ መልክ ነው።"

በንጽጽር ሲታይ፡-

| ዘመናዊነት | ድኅረ ዘመዊነት |
|---|---|
| • ተስፋ ፈንጣቂ የሕይወት ርእይ | • ሕይወት ዕብደት ነው የሚል ነው |
| • ሕይወት ባለ ዓላማ ናት | • ሕይወት ቀልድ ጨዋታ ናት |
| • ንድፍ/ቢጋራ አለ | • ሁሉም ዕድል ብቻ ነው |
| • የሥልጣን ተዋረድ ይከበር | • ፀረ ሥልጣን አቋም |

### 1.3.2 እውነትን መካድ ወይም እውነት የለም ማለት

ምንም ዐይነት ርግጠኝነት የለም፤ ያለ ነገር ቢኖር እንኳ "እንደ እኔ አመለካከት" የሚል ብቻ ነው። የሁሉም ነገር ተርጓሚው አንተ ስለሆንክ እንደ ሁኔታው በየጊዜው የሚለዋወጥ አስተያየት ሊኖር ይችላል። ሁሉ ነገር ሒደት ነው። መጽሐፍ ቅዱስን እውነት ነው ብዬ ብቀበል እንኳ አተረጓጎሜ እንደ አመለካከቴ ነው።

ድኅረ ዘመናዊነት እምነትን ምንም መልሕቅ የሌለው "እውነት አልባ" ጉዞ ስለሚያደርገው አደገኛ አስተሳሰብ ነው፡፡ ፍልስፍናው "የቱም ክልክል አይደለም፤ ከሠራልህ በየትኛውም በኩል መሔድ ትችላለህ" የሚል ነው፡፡

## 1.3.3 ሥልጣን ተጣራጣሪነት - ገፊነት

ድኅረ ዘመናውያን እውነት አንጻራዊ ነች ብለው ስለሚያስቡ እኔ ይዣታለሁ ብሎ የሚለውን ሁሉ ይጠራጠራሉ፡፡ እንዲህ ዐይነት እውነት ስለሌለ ይህ እውነት አለኝ ብሎ የሚለው ሰው ሁሉ መጨቆኛ መሣሪያ እንዲሆንለት ሥልጣንን ይጠቀማል ሲሉ ይሞግታሉ፡፡

እንደ ድኅረ ዘመናዊው ሰው አስተሳሰብ ዓለምንና አወቃቀሯን እንዲሁም አካሔዷን የምናይበት አንድ ጠቅላይ ታሪክ (meta narrative) የለም፤ ያሉት እዚህም እዚያም የተቀነበቡ ብጥስጥስ፣ ቁርጥራጭ ታሪኮች ናቸው፡፡ ጠቅላይ ታሪክ አለ ከተባለ ሌሎችን ሁሉ ይጨቁናል፡፡ ስለዚህ ወጥ የሆነ አመለካከትም ሆነ የሰዎች ሁሉ ታሪክ የለም፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በየባሕሉ ልዩ ልዩ አመለካከትና አኗኗር መኖሩን ቢያውቅም፣ የሰው ልጆች ሁሉ መነሻ ታሪክና ጠቅላይ አካሔድ እንዳለ፣ ስለዚህም ሁሉንም የሚመለከት ብያኔ እንዳለ ያስተምረናል፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንረዳው ወጥ የሆነ የሰው ልጅ ታሪክ አለ፡፡ ይህም ታሪክ መሥመራዊ ነው፤ መነሻም መድረሻም አለው፡፡ይህም ብቻ ሳይሆን ይህ መስመራዊ ጉዞ አንድ ጠቅላይ ታሪክ መሆኑን አስረግጦ ያስቀምጥልናል፡፤ ባጭሩ ለማሳየት እነዚህ ቃላት ይጠቅማሉ፡፡

ፍጥረት/creation

ውድቀት/fall

ቤዝዎት/redemption

ትፍጽምት/consummation ሊባል ይችላል ፡፡

ድኅረ ዘመናዊነት ይህንን ጠቅላይ ታሪክ የአንድ ሰፈር አመለካከት እንጂ ሁሉንም የሚተረጉም ለሁሉ እውነት የሆነ ታሪክ አይደለም ይላል፡፡ በመሠረቱ ሁሉን በአንድ ውቅር የሚያሳይ ምንም እውነት የለም የየጎራው ታሪክ (ተረት) ብቻ ነው ያለው ይላል፡፡



## 1.3.4 ተንሳፋፊ ማንነት

በድኅረ ዘመናዊነት አስተሳሰብ ልክ እውነት እንደሌለ ሁሉ ቀዋሚ ማንነትም የለም፡፡ ማንነቴ ኅብረተ ሰብና ዙሪያ ገባው የፈጠረልኝ ውቅር ነው፡፡ እኔ በየጊዜው ይቀያየራል፤ ዛሬ እንዲህ ነኝ፤ ነገ ሌላ ነኝ፤ አላውቀውም፡፡ ይሁን እንጂ፣ የማንነት (identity) ፍለጋው፣ ጭንቀቱ አለ፤ የትኛውንም ለዘለቄታው ለመቀበል ግን ወኔውም ፈቃዱም የለም፡፡ ስለዚህ ራስን ለተወሰነ ማንነት የመስጠት ፈቃድ (commitment) ጊዜያዊ ነው፡፡

## 1.3.5 ሥነ ምግባራዊ ብዥታ/አንጻራዊነት

ቋሚ ሥነ ምግባራዊ ብይን ስለሌለ የሚያዋጣህንና አንተን የሚጠቅምህን ፈልግ የሚለው ዋና የድኅረ ዘመናዊው ፍልስፍና ስብከት ነው፡፡

- ራስህን ውደድ፤ ዋናው ጉዳይ ራስህን ማስደሰት ነው፤ ሌሎች ሰዎች ዋና አይደሉም፤
- ቋሚ ሞራላዊ ሕግ ስለሌለ ያንተን አስተሳሰብ በሌሎች ላይ አትጫን፤ እንዳሰኛቸው ይሁኑ፤
- ሥልጡንነት የሁሉንም የሞራል አቋም ሳትቃወም እያሸጋሸግህ መኖር ነው (Tolerance - highest virtue) ይላሉ፡፡

ለድኅረ ዘበናውያን "ሠናይ" የሚባል ዕሴት ኅብረተ ሰብ ሲሻው የፈጠረውና የሰየመው፣ ሲሻውም ሊቀይረው የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ ሮርቲ የተባለው ድኅረ ዘመናዊ እንዲህ ይላል፡- "እኛ በውስጣችን ከጨመርነው ሌላ በጥልቅ ማንነታችን ውስጥ ምንም ነገር የለም፤ መለኪያውን የፈጠርነው እኛው ነን፡፡ የልክነት መስፈሪያ እኛው ካወጣነው በስተቀር አንዳችም የለም፡፡" በሌላ አነጋገር፣ ወደፊት የሚመጣው ትውልድ ፋሺዝም ያስፈልገናል ብሎ ቢል የምንቃወምበት ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡ እንዲያውም ጥሩ/ሠናይ ምግባር ማለት በሥልጣን ያሉቱ ይሁን ያሉት ነገር ብቻ ነው፡፡

በዚሁ መሥመር ውስጥ የሚገኘው ፉኮ(Foucalt) የተባለው የድኅረ ዘመናይነት አቀንቃኝ ነገሩን እጅግ አክርሮ ሄዶ የመጨረሻው መልካም ነገር ግለ ሰቡ ራሱን ለማስደሰት የሚኖረው ነጻነት

እንደ ሆነ ከቆጠረ በኋላ፣ ፍርሃቱን እንዲህ ሲል ይገልጻል፡ -"ኅብረተ ሰብ ማለት አንድ ግለ ሰብ የራሱን ፍላጎት የመግለጽና የመጠቀም አካሔዱን የሚያጨናግፍ ሤራ ነው።" ለምሳሌ አስገድዶ መድፈር ወንጀል መሆኑ ያሳስበዋል። ለእርሱ ሕግ ማለት ጭቆና እንደ ማለት ነው።

## 1.3.6 ድኅረ ዘመናዊው ሰውስካከት ዕቃ ሰምኅኢነት ያደለበታል

"መኖሬን የማውቀው ስለምሸምት ነው" ("I buy therefore I am") መፈክሩ ነው፤ ገበያ ሰገድ ነው። ከዚህም ሁሉ ጋር ይህ የኑሮ ዘዬ ሚዲያ አበድ (media-mad) እና አወሰቦ አበድ (sex-mad) አካሔድ ይዟል። ድኅረ ዘበናዊው ዓለም የአሳቡን ጥሬ ዕቃ የሚሸምተው ከሚዲያው (መገናኛ ብዙሃን)ነው፤ ቀቅሎ የሚያበስለውም እዚያው ላይ ነው። ስለዚህ ከምንጊዜውም ይልቅ ሚዲያ ጉልበታም ሆኗል። ራስ ማዕከሉ የሆነው ድኅረ ዘበናዊ ሰው ለፈንጠዝያና ለግላዊ ምቾት የሚሰጠው ዋጋ ትልቅ ከመሆኑ የተነሣ (Sex) ዋና የመዝናኛ ስፖርቱ ነው፤ አውስቦንን ከጋብቻ ዘላቂ ግንኙነት ጋር ለማጣመር አይገደድም። የአሁኑና የጊዜውን ደስታ ባሻው ዓይነትና መንገድ ማግኘት የኑሮ ዘዬው ሆኗል።

## 1.4 የግብረ ገባዊ አንጻራዊነት አደጋ (ይህ ክፍል በአብዛኛው የተወሰደው አቶ ተስፋዬ ሮበሌ ከጻፉት ‹‹የስነምግባር መርሖ›› ከተሰኘው መጽሐፍ ነው::)

በድኅረ ዘመናዊነት ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ግብረ ገባዊ/ሥነ ምግባርዊ አንጻራዊነት ዋና አመለካከት "ግብረ ገባዊ እውነታዎች እንደ ምግብ ጣዕም በግለ ሰቦች ኅሊናዊ ብያኔ ይወሰናሉ እንጂ፣ ምንም መስፈሪያ የለውም" የሚል ነው። ይህ በአሁኑ ዘመን የገነነ አስተሳሰብ የራሱ አደጋዎች አሉት። አራቱን እንጥቀስ፡-

### 1.4.1 አንጻራዊነት እርስ በርሱ የሚቃረን አስተሳሰብ ነው

አንጻራዊነት የቆመባቸው መሠረቶች 'ፍጹማዊ እውነት የለም፤ ፍጽማዊ የሆነ ፋይዳም የለም' የሚሉ ሲሆን፣ የምናነሣው ጥያቄ ፍጹማዊ የሆነ እውነት ከሌለ "ፍጹማዊ እውነት የለም" የሚለው አባባል ራሱ ፍጹማዊ አይደለም ማለት ነው። በዚያው መልክ ስለ ሥነ ምግባርም ማንሣት ይቻላል። በልዩ ልዩ ማኅበረ ሰቦች መካከል የግብረ ገብ መለኪያ ተለያይቶ መታየቱ (እንዳንዶ በጥልቅ ሲጠና ሥረ መሠረቱ ያው ሆኖ ቢገኝም) ልክኛ የሞራል መለኪያ የለም ለማለት የሚያስገድድ አይደለም። ነገሮች አንጻራዊ ናቸው የሚለው ነጻ አካሔድ ይምሰል እንጂ፣ በባሕል ስም የሚመጣውን ማንኛውንም አቋም እንድንቀበል እየመራንና እየወሰነልን ነው። ይህን ካላደረግልን "ጨቋኞች"፣ "ጠባቦች" በሚል ስያሜ ሊሰጡብን ነው።

### 1.4.2 ፍጹማዊ የሆነ ግብረ ገባዊ መስፈርት ከሌለ ግብረ ገባዊ መግባባት ሊኖር አይችልም

ፍጽማዊ የሆነ ገብረ ገባዊ መስፈርት ከሌለ ግብረ ገባዊ ውይይቶች ትርጉም አይኖራቸውም። አንድ ሰው ከማሆይ ቴሬሳ ይልቅ ሂትለር "ጥሩ ሰው" ነበር ማለት ይችላል። ሰዎች ሊሠሯቸው ከሚችሏቸው ነገሮች ሁሉ ግድያ "ጥሩ ነገር ነው" የሚል ሰው "ትክክል" ነው ማለት ይቻላል። የባሪያ ንግድም ሆነ አስገድዶ መድፈር ጥሩ እንዲሁም ሲደፋፈር የሚገባው ነገር ነው ማለት ነው። የታረዘን ማልበስ፣ የተራበን ማብላት፣ የታመመን ማስታመም ወንጀል ሊሆን ይችላል ማለት ነው። ሰብአዊነታችን የተቀበለው የግብረ ገባዊነት መስፈርት ግን እነዚህ ነገሮች ሁሉ ትክክል እንዳልሆኑ የሚገልጽ ነው። እንግዲህ በዚህ ሙግት መሠረት ከላይ ያየነውም ሁሉ ፍጽም ስሕተት ነው ማለት እንችላለን። እነዚህ ነገሮች ስሕተት ከሆኑ ደግሞ፣ አንጻራዊነት ስሕተት ነው ወደሚል ድምዳሜ ያመጣናል።

### 1.4.3 አንጻራዊነት እኩይ ምግባርን አይኰንንም

ግለዊ ሥነ ምግባራዊ አንጻራዊነት (ethical subjectivism) የግለ ሰቦችን እኩይ ባሕርይ አይኰንንም። እኩይ የሚባል ግብረ ገብ አለ የሚል እምነት ስለሌለው፣ ግብረ ገብ ኅሊናዊ ከሆነ (በሰዎች ፍላጎት ወይም &ጣዕም& የሚወሰን ጉዳይ ከሆነ) ሰዎች የቱንም ያህል ጸያፍ ሥራ ቢሠሩ ምግባራችሁ ስሕተት ነው የሚል ዐቅም የለውም (ቢያደርገው እንኳ እየገለጸ ያለው ስሜት፣ ጣዕም ወይም ግለ ሰቡ ያሻው ነገር እንጂ መሆን ያለበት ነገር አይደለም)። በሌላ አባባል "ተሳስተሃል" ማለት አይቻልም።

### 1.4.4 አንጻራዊነት የሰዎችን ሥነ ምግባር ማሻሻል አይችልም

ይህ አቋም ባሕርይን በማነጽ በጎ ሥነ ምግባርን ከመፈለግ እንድንዘናጋና ባሻኝ ልሩጥ የማለትን ግዴለሽነት ያበረታታል። ለበጎ ያለንን ጥረት ያፍናል፤ ያዳክማል።

በአንጻራዊነት ዕሳቦት ግብረ ገባዊ መሻሻል ወይም ተሐድሶ በፍጹም የሚታሰብ ነገር አይደለም። አንጻራውያን ምግባራቸውን ሊለውጡ ይችሉ ይሆናል፤ ነገር ግን ሊያሻሽሉ፣ የተሻለም ሰው ሊሆኑ አይችሉም።

"መሻሻል" የሚለው ፅንሰ ሐሳብ ትርጉም ሊኖረው የሚችለው ነባራዊ የሆነ መስፈርት ሲኖር ብቻ ነው። የተሻለ መንገድ ከሌለ መሻሻል የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም። ግብረ ገብ ይለውጣል እንጂ አይሻሻልም ብሎ ያስባል። ግብረ ገብ የመሻሻሉ ጉዳይ እውነት ከሆነ፣ አንጻራዊነት ስሕተት ነው።

## 1.5 የባህርይ ልማት ግንባታ

የባሕርይ ልማት ግንባታ ላይ ማትኩር የበለጠ ዋጋ አለው። ግብረ ገባዊነት በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የመስጠት ሒደት ሳይሆን፣ በዋናነት የሠናያት ባሕርያት ግንባታ ነው። የሰው ልጆች ሁልጊዜም ለነገሮች የሰጡት ምላሽ ከማንነታቸው ወይም ከባሕርያቸው የሚመነጭ ነውና። ስለዚህ በአንድ ወገን በጎ ሥነ ምግባርን የሚያበረታቱ ፖሊሲዎችና ደንቦች እንዲረቀቁ መተጋገዝ የሚያስፈልግ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ግለ ሰቦችና ማኅበረ ሰቦች መልካም ባሕርያት እንዲያዳብሩ በባሕርይ ቀረጻ ላይ ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው።

## 1.6 ተጠቂ - ተጠያቂ

በሞራላዊ አንጻራዊነት ግብረ ገብ የሚፈጠረው አንድ የሰዎች ቡድን አባላት በውስጠ ታዋቂነት ወይም አውጥተው አውርደው በተረዱት መንገድ፣ እርስ በርስ ባላቸው ግንኙነት ላይ ስምምነት ሲደርሱ ነው። ስለዚህ ግለ ሰቡ ለየትኛውም ፍጹማዊ ሞራል የመገዛት ኀላፊነት የለበትም፤ ፍጹማዊ ከተባለው ከየትኛውም መስፈርት የወረደ ቢሆንም፣ የወረደበት/የሳተበት አካሔድ የሚተረጎመው እርሱን ያስጠይቀዋል በሚል ሳይሆን፣ ለችግር



ተጋልጦ ተጠቂ ሆኗል በሚል ብቻ ነው።

ኮፖን የተባሉት ፈላስፋ ይህን ሲተቹ እንደዚህ ብለዋል፡- "ድኅረ ዘመናዩ ኅብረተ ሰብ ከፍጹማዊ ሞራል እምነት የሚያደርገው ሽሽት አንዱ ጉልህ ምልክት፣ እኩያን ተግባራትን 'ሥነ ልቡናዊ ችግሮች ናቸው'፤ 'የጥቃት ምልክቶች ናቸው' በሚል የቃላት እንቶ ፈንቶ መሸንገሉ ነው።" ይህ አካሔድ በቀኑ መጨረሻ ምንም ዐይነት "ክፉ" ተግባር ቢፈጸም (ክፉ ያለ እንደ ሆነ) ማንም ተጠያቂ ሊሆን እንዳይችል ጥርጊያ የሚሰጥ ነው። በዚህ መንገድ ከተሔደ በኅብረተ ሰብ ላይ እንያዣበበ ያለውን አደጋ ጆርጅ ዊል የተባሉት ሰው ልብ ብለውታል፦ "እኩይ ምግባር እንደሌለ የሚሸፍጥ ኅብረተ ሰብ በቅጣትም መኖር አለመኖር ላይ ይሸፍጣል፤ ይህ ኅብረተ ሰብ ዕድሜ ልኩን በሥጋት ቢኖር የሚያስገርም አይሆንም።"

ሰዎችን ለጥፋታቸው ተጠያቂ ሳይሆኑ ተጠቂ ብቻ እንደሆኑ ስንቆጥር ማክበራችን ሳይሆን፣ ሰብአዊነትን ማዋረዳችን ነው። ሰው የሞራል ዳኝነት ከሌለውና ተጠያቂነት የማይሰማው ከሆነ ክብር የሌለው ዕቃ መሆኑ ነው። እዚህ ላይ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የተጻፈ የአንዲት ሴት ታሪክና የኢየሱስ ክርስቶስ የሥነ ምግባር አተያይ ሚዛን ይሰጠናል ብዬ ዐስባለሁ።

በምንዝር የተያዘች ሴት እያካለቡ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ለፍርድ ያቀረቧት በዘመኑ የነበሩ የተከበሩ ሃይማኖት መሪዎች ናቸው። "በሙሴ ሥርዐት ይህች ሴት በድንጋይ ተወግራት ትሙት ተብሏል፤ አንት ምን ብይን ትሰጣለህ?" ለሚለው የተንኮል ጥያቄአቸው ክርስቶስ የሰጠው መልስ "ከእናንተ መካከል ኀጢአት የሌለበት ሰው የመጀመሪያውን ድንጋይ አንሥቶ ይወገራት" የሚል ራስ መርማሪ፣ ግብዝነት አጋላጭ ጠንካራ መልስ ነበር። በውስጣቸው በተፈጠረው የሞራል ሞገድ እያፈሩና እየተበሰጩ ሲሔዱ አመንዝራ የተባለችይቱን ሴት "እኔም አልፈርድብሽም፤ ደግመሽ ግን ኀጢአት አትሥሪ" ማለቱ ከግብረ ገብ መሥፈርት ለወደቁ ሰዎች መሰጠት ያለበትን ርኅራኄ፣ ወዲያውም እኩይ ተግባርን በስሙ ጠርቶ የማውገዝ ክምጫጫ አቋም የሚያሳይ ሚዛናዊ አካሔድ ነው።

# 2 እኛ ያለንበት የሥነ ምግባር ሁኔታ

አሁን በአገራችን የሚታየውን የሥነ ምግባር ሁኔታ ጠቅላላ

ዳሰሳ ለማድረግ ቀላል ተግባር አይሆንም። በሰፊው የተደረጉ ጥናቶችና መረጃዎች በሌሉበት መስክ ልንል የምንችለው ጥቂትና አብዛኛውን ላይ ላዩን ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ፣ ወደፊት ለምናልመው የመልካም ሥነ ምግባር ግንባታ መንደርደሪያ ሜዳ ለማበጀት ሲባል ግርድፍ ቅኝትም ቢሆን መከናወን አለበት።

### 1.1 የትውልድና የአመለካከቶች ክፍተት

የትውልድ ክፍተት በሁሉም ኅብረተ ሰብ ውስጥ በየጊዜው የሚከሰት በሽታ ነው። በእኛ ኅብረተ ሰብ ከቴክኖሎጂ ውጤቶች መስፋፋትና ከመገናኛ ብዙኃን ጉልበት የተነሣ በወጣቱና በቀደመው ትውልድ የአኗኗር ዘዬ፣ በተለይም በሥነ ምግባር አስተያየት በኩል እየጨመረ የሚሄድ ክፍተት/ገደል እንዳለ መቃኘት ይቻላል። ነውር ተደርገው ሲቆጠሩ የነበሩ ባሕርያትና ተግባራት "ሁሉም የሚያደርገው" ተራ ነገር በሚል ወቅታዊ ነፋስ ሲንገዋለሉ አሮጌውና አዲሱ ግጭት ውስጥ ይገባሉ። ይህ ክፍተት አንዳንድ ጊዜ እያየለ ሄዶ ሁለቱ ትውልድ እርስ በርስ መደማመጥ እንዳይችል ደንቃራ ሲሆንም ይታያል።

### 2.2 የግላዊነት በሽታ መዛመት

ከፍተኛ የፉክክርና የእሽቅድምድም ሁኔታ ላይ ስለወደቅን ኑሮን በማሸነፍ ሩጫ አንዳንዶች ተድጠው፣ ተደፍጥጠው ቢቀሩም እስ ከዚህ ቁብ የማይሰጥበት ጊዜ እየሆነ ያለ ይመስላል። ለማኅበራዊ መስተጋብርና ለጋራ ማንነት ያለው ትርጉም እየኮሰሰ ስለሔደ እሷ ከሞቱች ሠርዶም ባይበቅል ግድ እንደሌላት እንስሳ የማሰብ አዝማሚያ ይቃኛል።

### 1.3 የኑሮ ጫናን ያባበበ የሙስና መበራከት

የየግለ ሰቡ ኑሮ በጠባብ የኢኮኖሚ ገመድ ላይ እየተውተረተሩ የመሄድ ርምጃ ስለሚመስል አዳልጦ እንዳይወድቅ የተገኘውን ሐረግ ሁሉ መጧጠጥ የዕለት ዕለት ክስተት ነው። "ይሞታል እንጂ!" በሚል ዜማ ያየለበት የሙስና ዳንኪራ ኅብረተ ሰባችንን ወዲያ ወዲህ እያላጋው እንዳለ መካድ አይቻልም። በሐሰት የትምህርት መረጃ ሥራ ከመቀጠር አንስቶ ከባድ የሕዝብና የመንግሥት ንብረት ዝርፊያ የሚበራከትበት ሁኔታ ለሁላችን ግልጽ ነው። ከዚህ ይልቅ የሚያሳስበው ደግሞ እንደዚህ ዐይነት ድርጊቶች በሚፈጸሙበት አካባቢ ያለው ተመልካች "እባክህ



ተወው፣ ካልተያዘ ይብላ፣ ቢያልፍለት እኔ ምናገባኝ" የሚል ለሞራል እውነታዎች ግዴለሽነት የሚሳይ አመለካከት ነው።

### 1.4 የሚዲያ/መገናኛ ብዙኃን ልቅነት - ዳኛ አልባ ሸንጎ

ኅብረተ ሰብ ለማልማት ሊውሉ ከሚችሉ ጠንካራ ኀይሎች መካከል አንዱ ሚዲያ እንደ ሆነ ይታወቃል። በሁነኛ የሥነ ምግባር መርኀ ላይ ካልተመሠረተ ደግሞ ምናልባት ከሁሉ ይልቅ ዐውዳሚ መሣሪያ ሊሆን የሚችለው ሚዲያ/መገናኛ ብዙኃን ሳይሆን አይቀርም። አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የጽሑፍም ሆነ የኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ኅብረተ ሰብን ለበጎ ሥነ ምግባር ለማነጽ ከክፉ የሞራል ነፋሶች ለመጠበቅ ይሁነኝ ተብሎ የሚሠራበት አካሔድ አለው ወይ የሚል ጥያቄ ማንሣት ተገቢ ነው። ሁሉንም በጭፍን ማጥላላት የሰነፍ ሥራ ስለሚሆን እንደዚህ ያለ ፍርደ ገምድልነት ሳናሳይ ልብ ብለን የተመለከትን እንደሆን ጋዜጣው ቴሌቪዥንና ሬዲዮ እርስ በርሱ የሚጣላ ጉራማይሌ የሥነ ምግባር የትዕይንት ገበታ እያቀረቡልን በሌላ ወገን ለልቅነት የሚዳርጉ ብዙ ሥራዎች ይቀርባሉ። በሌሎች መስኮች ምናልባት በወጣ መመዘኛ የሚለኩ ፕሮግራሞች ኖረው ቢሆንም የሞራል ሁኔታ ላይ ግን ግልጽ መለኪያ ስለመኖሩ እጅጉን የሚያጠያይቅ ዳኛ አልባ ሸንጎ መስሏል።

### 1.5 የማንነት ስጦት - ሥር አልባነት

"እኔ ይህ ነኝ" ብሎ በእግሩ ያልቆመ ግለ ሰብም ይሁን ማኅበረ ሰብ ዋና ፈተናው ያለፈ ያገደመ አመለካከት የሚጎትተው ለምንም ነገር ታማኝ ያልሆነ ዘዋሪነት ነው። ባለፉት ጥቂት ዐሠርት ዓመታት ካሳለፍነው የፖለቲካ ነውጥና የማኅበራዊ ኑሮ ቀውስ ጋር ተይይዞ እንዲሆም ከቤተ ሰብ ተቋም መዛባትና ከኢኮኖሚያዊ ስደት ጋር ተነባብሮ፣ የአሁኑ ሰው ማንነቱን አንጥሮ "እንዲህ ነኝ" ለማለት ዐቅም እያነሰው መጥቷል። ከዚህ የተነሣ ሥር አልባነት ወይም ቅጂያዊነት እየተበራከተ ይታያል። በሥነ ምግባር ገበያ የሚሸመተውን ባለብዙ ቀለም እንጀራ እየበላ የየሰዉ መልክ እጅግ ተለዋዋጭ ሆነ።

## 3. ሥነ ምግባራዊ ትኩረት የሚሹ አገራዊ ጉዳዮች

*(በዚህ ክፍል የቀረበው የተወሰደው ፕሮፌሰር አታላይ ዓለም፣ አቶ ንጉሤ ቡልቻ እና ዶ/ር ሄኖክ ገ/ሕይወት ከጻፉት 'አንተ ግን ከተሰኘ መጽሐፍ ነው።)*

በኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ በ3ኛው ሺህ ዓመተ ምሕረት ላይ የሁላችንን ሥነ ምግባራዊ ትኩረትና ጥረት የሚሹ ብዙ ብርቱ ጉዳዮች (ethical issues) አሉ። ከእነዚህ መካከል፦

- ሥነ ምኅዳራዊ ሚዛን (አካባቢ ጥበቃ)
- ሥራና ሙዐለ ንዋይ
- ጾታዊ ሥነ ምግባርና ቤተ ሰብ
- አልኮልና አደንዛዥ ዕፅ (substance abuse) የተሰኙት ሊጠቀሱ ይገባል እላለሁ።

ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱን ዐሳቦች ብቻ እናንሣ።

3.1 ሥራ፦ ሥራ የዐዋቂ ዕድሜያችንን ሲሦ ይይዛል፤ በማኅበረ ሰብ ውስጥ ያለንን የማንነት ሚዛን ያስተጋባል። የባሕርያችን መስተዋት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የፍጥረት ዐሰም መጋረጃ ሲገለጥ እግዚአብሔር በሰማይ ዙፋን ላይ በመላእክት ከበባ ተደላድሎ ተቀምጦ አይታይም፤ ይልቁን ዓለማትንና በውስጣቸው ያሉትን ሲፈጥር፣ ሲያበጅ ሲያሳምር፣ ሲመራ፣ በታላቅ ትጋት ውስጥ ሆኖ እናየዋለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠው አምላክ ብርቱ ሠራተኛ ነው። የመጀመሪያው መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ ይህን አምላክ የሚያስተዋውቀን ባሕርያቱን በመዘርዘር ሳይሆን ሥራውን በማሳየት ነው። የተግባር መግለጫ የሆኑትን የግሥ ሡራዊት ያሰልፍልናል። ፈጠረ፣ አለ፣ አየ፣ ለየ፣ ጠራ፣ አደረገ፣ አኖረ፣ ባረከ የሚሉት ቃላት ባናት ባናት እየተደራረቡ ከሠላሳ ጊዜ በላይ ተጽፈዋል። ልዑል አምላክ ሥራውን በዓላማ፣ በዕቅድ፣ በትጋት በሥርዐት፣ በጥበብና በደስታ ሲያከናውን ይታያል።

ሰው ለምን ይሠራል? ወይም ሰው መሥራት ያለበት ከሆነ ለምን ዓላማ መሥራት አለበት? የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ጥያቄ ነው። የሰው ልጅ ባለ ዓላማ ፍጡር ከመሆኑ የተነሣ አጥጋቢ የመንቀሳቀሻ ምክንያት ካገኘ ነፍሱ ትለመልማለች፤ ግብና መድረሻ ካጣች ነፍሱ ትስለመለማች። ርካታው ይጠፋል፤ ፍላጎቱ ይቀዘቅዛል። የፍላጎት ማሟላት (የእንጀራ ጉዳይ) አንዱ ዓላማ ቢሆንም፣ ለኅብረተ ሰብ ጥቅም እንዲሆን፣ ለሌላቸው ማካፈል እንዲቻል እንዲሁም ስብዕናችንን ለማልማት፣ እርካታም ለማግኘት ሥራ ሁነኛ መንገድ ነው።



ሰው ባለብዙ ዕምቅ ችሎታ ፍጡር ነው። ኀይል የተቋጠረው ጡንቻው ውስጥ ብቻ ሳይሆን የአእምሮው ክሮች ላይም ነው። ብዙ ክሂሎች የተከማቹበት የሰው ልጅ ያንን ሁሉ ዐቅምና ጥበብ መተንፈሻ፣ መንቀሳቀሻ ማውጫ፣ መግለጫ ይፈልጋል፤ ታፍኖ ሊሞት አይወድም። ሥራ ጤነኛ መተናፈሻው ነው። የሰው ጉልበት ጊዜውና ዕውቀቱ ጠቃሚ ነገር ላይ እንዲውል የሚያስችለው ጥሩ መንደርደሪያ በይ ሥራ ይባላል። የሰው አካልና አእምሮ በጎ ሥራ ላይ ካልዋለ ክፉው ይጣባዋል። መዶሻ ካላስጨበጥነው ጩቤ ይይዛል። ለሰው ልማት እንዲያስብ በር ካልከፈትንለት ለሰው ጥፋት ማሰብ ይጀምራል። ይህን ሳስብ ነው ወጣቶችን በልዩ ልዩ ሙያ ማሠልጠን፣ የሥራ ዕድልን ማዘጋጀትና ሥራ ፈጠራን ማስተማር አስፈላጊነቱ ገዝፎ የሚታየኝ።

ስለ ሥራ ሥነ ምግባር ሊነገር የሚችል ብዙ ነገር ቢኖርም፣ በተለይ ሕዝባዊ አገልግሎት ስለ መሆኑ ጥቂት ማንሣት እወዳለሁ።

የሥራ ትርጉም ራሱ ከአገልግሎት ጋር የተያያዘ በመሆኑ በማናቸውም የሥራ መስክ ላይ በምንሠማራበት ጊዜ የምናከናውነው ተግባር ይብዛም ይነስም ለሕዝብ ጥቅም የሚውል መሆኑን ማጤን አለብኝ። ጫማ መጥረግም ይሁን ቁስል መጥረግ፣ የትምህርት ቤት ቲማቲም መትከልም ይሁን በመደብር ቲማቲም መሸጥ፣ የተበላሸ መኪና መጠገንም ይሁን የቆመ መኪና መጠበቅ ሁሉም ለሕዝብ ጥቅም የሚውል ሥራ ነው።

የምሠራው ሥራ ለእኔ መተዳደሪያ የሚሆን ገቢ ቢያስገኝም፣ አሻግሬ ማየት ያለብኝ ሌሎችን ባግባቡ እየጠቀምሁ ነው ወይስ እየጎዳሁ? እኔ ብዙ ጥቅም እንዳገኝ እነሱን አጉላላሁ ወይስ ሚዛናዊ መጠቀም አስባለሁ? የሚሉትን መፈተሻዎች ነው። በኅብረተ ሰብ ውስብስብ ኢኮኖሚ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ የአንዱ ጉዳት ለሌላው ጥቅም የሆነ የሚመስልበት ሁኔታ አለ። ዕቃና ባለሙያ ሲጠፉ ዕቃውና ሙያው ያላቸው ሰዎች የበለጠ የሚፈለጉበት አጋጣሚዎች ይፈጠራሉ። ያን ጊዜ እንደ ሠራተኛ ወይም ነጋዴ ሊኖረን የሚገባ አመለካከት በጥንቃቄ የተያዘ ሊሆን ያስፈልጋል።

"በድብቅ እህል የሚያከማቸውን ሕዝብ ይረግመዋል፤ አውጥቶ የሚሸጥ ግን በረከት ይጎናጸፋል።" (ምሳሌ 11:26)

## 3.2 የአደንዛዥ ዕፆች ችግር

በብዙ አገሮች አልኮልና አደንዛዥ ዕፆች እያስከተሉ ያለው ችግር በተደጋጋሚ ሲወሳ የሚሰማ ነው። በአገራችን በኢትዮጵያም የአልኮል ጉዳይ እያደገ የመጣ ችግር መሆኑን የሚጠቁሙ ጥናቶችና ሪፖርቶች አሉ። በገጠርና በከተማ በተደረጉ ሁለት ጥናቶች እንደታየው ከ2.7 እስከ 3.7% የሚሆነው የአገራችን ሕዝብ ጤንነትን በሚጎዳ መጠን አልኮል የሚጠጣ መሆኑ ታውቋል። ይህም በአኀዝ ሲተመን ከ2 እስከ 2.6 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ለዚህ ችግር የተጋለጠ መሆኑን ያሳያል። ይህንን ከትራፊክ አደጋ ዘገባዎች ጋር ያገናዝቡት።

ትምባሆም እንደዚሁ ዋነኛ የጤና ጠንቅ ነው። በአገራችን በተለይም በወጣቱ ኅብረተ ሰብ መኻል ብዙ ትምባሆ ተጠቃሚዎች አሉ:: በእነርሱና በአከባቢያቸው የሚኖሩ ሰዎች ላይ የጤና ጉዳት ቢደርስም፣ ይሄንኑ በጥንቃቄ የዘገበ ስለሌለ ምን ያህል እንደ ሆነ አይታወቅም። በሌሎች አገሮች አገሮች የትምባሆ የጤና ጠንቅነት በደንብ ተዘግቦ መንግሥታትና ሕዝቡም ከፍተኛ የሆነ ፀረ ትምባሆ ዘመቻ እያካሄዱ ናቸው። በአገራችን በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ትምባሆ ይጠቀማሉ። በትምባሆ ውስጥ የሚገኘው ሱስ የሚያሲዘው ኬሚካል "ኒኮቲን" ይባላል። ኒኮቲን በአንጎል ውስጥ አንዳንድ ለውጦችን በማምጣት አንጎል በኒኮቲን ላይ ጥገኛ እንዲሆን ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ በትምባሆ አምራች ድርጅቶች በኩል የሚካሄደው ቅስቀሳ ብዙዎች ማጨስ እንዲለምዱ ያደርጋል። ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ትምባሆ የሚጠቀሙ ከሆነ ልጆችም ይለምዳሉ። ከአልኮልና ከትምባሆ ሌላ በአገራችን በሚሊዩን የሚቆጠሩ ወንዶች ሴቶች፣ ወጣቶች አዋቂዎች ጫት ይቅማሉ። ጫት ማብቀልም ሆነ መቃም በአገራችን ከተጀመረ በሺህ የሚቆጠር ዓመታት ሲያስቆጥር፣ በአሁኑ ጊዜ ከተጀመረበት ከምሥራቁ የአገሪቱ ክፍል ወደ ሌላው በመስፋፋት በሁሉም የኢትዮጵያ ክልል ከተሞች በሰፊው እየበቀለና እየተቃመም ነው። ምንም እንኳን በአንዳንድ ባለ ሥልጣናትም ሆነ በሃይማኖት መሪዎች ቢወገዝም፣ ስርጭቱንም ለመቀነስ ሙከራ ቢደረግም ጫት መቃም የበለጠ እየተስፋፋ ነው። የሌሎች ዕፆች አደገኛነትም ምንም ንግግር/ማብራሪያ ሳይሻ ሁላችን የምንገነዘበው ዋና ችግር ነው።



## 4 ጠርጥ ጠር ሥነ ምግባርና ብሔራዊ ትድግና

በሥነ ምግባር አመለካከት ሒደት ዙሪያ ገባውን እየቃኘን፣ በአገራችንም ያለውን የሞራል ሁኔታ ከሞላ ጎደል ለመረዳት እዚህና እዚያ እየተዛለልን የተራመድነው ርምጃ ሁሉ ማካተቻው "እንግዲያው ምን እናድርግ?" የሚል ነው። ብዙ ልናስበውና ልንመካከርበት የሚያሻ አስተያየት ቢኖርም አራት መንደርደሪያ ጡቦች ላስቀምጥ፡-

### 4.1 የማንነት ግንባታ

ማንነቱን አስረግጦ የማያውቅ ግለ ሰብም ይሁን የሕዝብ ማኅበር ሁነኛ ዓላማ ሊኖረው አይችልም፤ የአስተሳሰብም ሆነ የምግባር መለኪያ፣ ማነጻጸሪያ አያገኝም፤ ስለዚህ ደመ ነፍሳዊ ፍላጎቶቹ ያሳደሩበትን ብቻ ለማድረግ የሚነዳ አስፈሪ ፍጡር ይሆናል። ባለረዥም ዘመን ታሪክ የሆነችው ይህች አገር እየበቀለ ያለው ትውልዷ ሳይሸማቀቅና ግራ ሳይጋባ ብሔራዊ ማንነቱን በርጋታ የሚያጤንበት ዕድል መስጠት ያስፈልጋል። የትናቱንና የዛሬውን ልናያያይዝለት ይገባል፤ በቤተ ሰብ በትምህርት ቤት፣ በመገናኛ ብዙኃን በሌሎችም የማሳደጊያ መደቦች ላይ የማንነት ግንባታ "ሥራዬ" ተብሎ ሊያዝ ያስፈልገዋል። የሌሎች ሕዝቦችን ማንነት እያከበሩ፣ የራስን ማንነትም እያጠናከሩ መሔድ ፊታችን የተደቀነ ተግባር ነው።

### 4.2 የባሕርይ ግንባታ

ስለ ሥነ ምግባር ስነጋገር ሰዎች ምን ዐይነት ባሕርያት ያሳያሉ የሚለው ትኩረት የሥነ ሰብ ጥናት ባለሙያዎች ተግባር ሲሆን፣ እኛ ግን ከዚህ ፈቀቅ ብለን ሠናያት ባሕርያት እንዴት ሊገነቡ ይችላሉ ማለት ይጠበቅብናል። ለእንደዚህ ዐይነቱ ርምጃ አንዱ መንገድ በየሥነ ምግባሩ ጉዳይ (issue) ላይ በጎ ወይም ሠናይ ባሕርይ የምንለው ምንድነው የሚለውን በጥንቃቄ መመርመር ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ይህ ዐይነት ባሕርይ እንዴት እንደሚሠርጽ ስልት አውጥቶ፣ በተለይ በወጣቶች ላይ፣ ከእነርሱም ጋር መሥራት ነው።

### 4.3 ቤተሰብን ማጠንከር

የብርቱ አገራዊ ፍቅርና ሕዝብ አገልጋይነት መሠረት መልካም

ቤተ ሰብ መሆኑ ብዙ የሚያከራክር አይደለም። በተናጋ ቤተ ሰብ ውስጥ የሚያድጉ ወይም በቤተ ሰብ ሕይወት መናጋት የሚበታተኑ ወጣቶች የሚበዙበት ሁኔታ ማኅበራዊ ሥነ ምግባራችን ለምልሞ መልካም ፍሬ ያፈራል ማለት ያልዘሩትን ለማጨድ እንደ መከጀል ነው። ስለዚህ መንግሥታዊ የሆኑም ያልሆኑም ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማትና ሌላው ኅብረተ ሰብ ሁሉ በልዩ ልዩ ቀውስ እየተላጋ ላለው ለዚህ መሠረታዊ ተቋም ከፍተኛ የማዳን ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል።

## 4.4 መገናኛ ብዙኃንን በሥነ ምግባር ዕድገት መቃኘት

የሕዝባችን ቁጥር እየጨመረ ሲመጣ፣ የወትሮው አፍ ለአፍ ግንኙነት እየላላ ሚዲያ ዋና እየሆነ መምጣቱ አይቀርም። አሁንም በፍጥነት ኅብረተ ሰባችን ወደዚሁ እየዘለቀ ነው። በመጻሕፍት፣ በፊልምና ቴአትር፣ በቴሌቪዥን፣ በሬዲዮና በኢንተርኔት ለሕዝባችን እየቀረበ ያለውን የሥነ ጽሑፍና የሌሎች ሚዲያ አገልግሎት በርጋታ መመርመር የሚያስፈልግ እንደ ሆነ አጥብቄ አምናለሁ። ሚዲያ የአስተሳሰብና የኑሮ ዘዬ ገበታ እንደ መሆኑ ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሁሉ በዚህ ገበታ ላይ ስለሚቀርበው አልሚ ወይም አጥፊ ምግብ ሁነኛ ፍተሻ ማድረግ፣ በጎውን ማበረታታት፣ በጎ ያልሆነውን ማቃናት በአጠቃላይም ለተሻለ ብሔራዊ ሥነ ልቡና ግንባታ የሚሠሩ አዳዲስ ሥራዎችን ማነቃቃት ይጠበቅባቸዋል። የሚዲያ ባለሙያዎች ከፍተኛ ኃላፊነትና ባለ ዐደራነት አለባቸው። በተለይ ከውጪ አገር የሚመጡ ጤነኛ የቤተ ሰብ ሕይወትን የሚሸረሽሩ፣ ወደ ዘማዊነት፣ ግብረ ሰዶማዊነትና ወንጀለኛነት የሚገፉፉ ልዩ ልዩ የሚዲያ ውጤቶች የባሰ ጉዳት ሳያመጡ ኅብረተ ሰባችንን የምንጠብቅበትን መንገድ ማሰብ ተገቢ ነው።

## 4.5 የተግባራዊ መፍትሔዎች ማጠቃለያ

1.1.1 ከጅማሬ እስከ ከፍተኛ ባሉ የመንግሥትም ሆነ የግል የትምህርት ተቋሞች የሞራል ትምህርት በተገቢው ሥርዐት የሚቀርብበት መንገድ ሊመቻች ያስፈልጋል፤ መምህራኑንም በተከታታይ ሥልጠናዎች ማገዝ ፍሬያማ ያደርጋል። በዚህ ረገድ ከእምነት ተቋሞችና ከማኅበራዊ አገልግሎት ቡድኖች ጋር ግንኙነት ቢደረግ የበለጠ ውጤት ሊገኝ ይችላል።



1.1.2 በመገናኛ ብዙኃን መልካም ሥነ ምግባር ማስተማሪያ መወያያ መድረኮች በበቂ ሁኔታ እንዲዘጋጅ ማነሣሣት ያስፈልጋል። በሚዲያ በሚቀርቡ ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች የሚተላለፉትን የሥነ ምግባር አስተሳሰቦች የሚፈትሽ ግልጽ ፖሊስ ማስቀመጥ ጠቃሚ ነው።

1.1.3 ለወጣቱ የሥነ ምግባር መበላሸት ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ የአደንዛዥ ዕፅ፣ የመጠጥና የዳንኪራ ቤቶች መበራከት ላይ ቁጥጥር ማድረግ መብትን እንደመጣስ ተርጎ መወሰድ የለበትም፤ ይልቁን ጤናማ ኅብረተ ሰብ የመገንባት አንድ ገጽታ ተርጎ መቆጠር ይገባዋል። በእነዚህ ቦታዎች ምትክ ለወጣቱ መዋያና መዝናኛ ጠቃሚ ቦታዎች እንዲበራከቱ የሚያበረታታ ርምጃ ከከተማ አስተዳደሮችና ከባለ ሀብቶች ይጠበቃል።

1.1.4 በአትሌቲክስ፣ በአካዴሚክስና በሥነ ጥበብ ለሚደረጉ ጉልኅን አስተዋጽኦዎች ዕውቅናና ሽልማት እንደሚዘጋጁ ሁሉ ለመልካም ሥነ ምግባርና አርኣያነት ለተሞላ በጎ ሥራ ሽልማቶችና በዓላት ማዘጋጀት፣ ከጥፋተኛነት ወደ ኅብረተ ሰብ ጠቃሚነት የተመለሱ ሰዎችን ግለ ታሪክ እያቀረቡ አዲሱን ትውልድ ማበረታታት ያስፈልጋል።

1.1.5 በጋብቻ በቤተ ሰብ ዕድገት፣ በልጆችና በወጣቶች ልማት ላይ የሚሠሩ ተቋማትን ማበራከትና የጀመሩትንም ማበረታታት እጅግ አስፈላጊና ወቅታዊ ጥሪ ነው።

በመጪው ዘመን ለበጎ ሥነ ምግባር የታጠቅን እንድንሆን ሰማያዊ ረድኤቱን እግዚአብሔር ይላክልን!

ዋቢ መጻሕፍት


1. Campbell etal, *"New Dictionary of Chrisitian Apologetics.* IVP 2006
2. Copan Paul, *"True For you But Not Me"* Bethany House Publishers,Minneapolis, 1998
3. Dokery, David S. ed. *The Challenge of Post Modernism: An Evangelical Engagement,* Baker,Michigan, 1995
4. Johnston, Graham, *PrcachingTo A Postmodern World.* IVP, 2001
5. *መጽሐፍ ቅዱስ -ነባሩ ትርጉም*
6. ተስፋዬ ሮበሌ ፡ የሥነምግባር መርሖ። ተስፋ ዐቃብያን ክርስትና ማኅበር አዲስ አበባ 1996 ዓ.ም
7. *ዶ/ር አታላይ ዓለም እና ሌሎች ‹‹አንተ ግን ››ኤ.አ.ኢ*
8. ተስፋዬ ሮበሌ፡ ድኅረ ዘመናዊነት -ጥናታዊ ጽሑፍ




# የንባብ እንቅፋት - የንባብ ትጋት

*"... ስትመጣ ... በርኖሱንና መጻሕፍቱን ይልቁንም በብራና የተጻፉትን አምጣልኝ" ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ*

እንድናነብ ሰዎችም እንዲያነቡ የምንፈልግ ሰዎች ለጉዳዩ ሁነኛ ትኩረት ሰጥተን መወያየታችን አስፈላጊ ነው። እንደ ክርስቲያን ከንባብ ጋር ያለን ግንኙነት ሕያውና ጠቃሚ መሆኑ አያጠያይቅም። የአምላካችን ቃል በፊደል ገበታ ቀርቧልና ንባብ ለክርስቲያን እንግዳና ሩቅ ሊሆን አየገባም።

ውይይታችንን በሦስት ክፍለን እንነጋገር። የንባብ ታሪክ ብጤ፣ አሁን ያለው የንባብ ሁኔታ እና ንባብን ለማትጋት የሚሉ ንዑሳን አርእስት መንጠላጠያ ደረጃዎቻችን ይሁኑ።

## የንባብ ታሪካችን

> *ካኹን ቀደም ንጉሥና ጳጳስ ስለ ሕዝብ በየወረዳው ያቆሙት ታላላቅ ጉባዔ ለፋፊ የተማሪ ቤት ከሌለ ዘንድ ካባትና ከእናት ቤት ኮብልሎ፣ አገር ላገር ዞሮ በልመና እንጀራ የሚማሩት ትምህርት እንደ ቅምሻና እንደ ጉርሻ የማያጠግብ ስለኾነ በሽመታና በዲገታ በራቻና በሽት ይመስላል። ከዚህ ምሳሌ የተነሣ ጥፈትና ትምህርት እየቅል ኹኖ ጥፈት አዋቆች ከሰዋሰው ትምህርት የራቁ መጽሐፍ አዋቆችም*

*ጥፈት የማያውቁ ስለኾኑ የትምህርቱ አቢጋዝ ጳጳሱም አካቶ ፈጽሞ የግዕዝን መልክዓ ፊደል የማያውቅ ባዕድ የውጭ አገር ሊቅ ስለ ሆነ በዚህ ምክንያት የግዕዝ አዝመራ የትምህርቱ ሰብል ... ተሰቅሞ ታጭዶ ምርቱና ግርዱ ተንጣሎ ገና አልታፈሰም አልተዛቀም።" (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ)*

ይህ አገር በታሪክ ማስታወሻ ስርጥ ስርጡን ሳይሆን አዛንቶ የሚያስኬድ የፊደልና የንባብ ጎዳና አለው። ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ስንትና ስንት ዓመታት ሲጻፍ ሲነበብም ቆይቷል። የክርስትና መግባትም የጽሕፈትን፣ የትርጉምን፣ የማስተማርን ሥራ ባያሌው ከፍቶታል። በብዙ መቶ ዓመታት መካከል የተጻፉትን የኢትዮጵያ ጥንታውያን ጽሑፎች ከመቶ ዘጠናው ነገረ ሃይማኖት፣ በተለይ ደግሞ የክርስትና ትምህርትና ከዚሁ ጋር የተያያዙ ጽሑፎች ነበሩ። ያን ጊዜ የነበረው የኅብረተ ሰብ እድገት ደረጃ ሰበብ ሆኖ ምናልባት የምሁራኑም አስተሳሰብ አቅጣጫ ሰበብ ሆኖ ይጻፍ የነበረው ሁሉ በተወሰኑ ምሁራን አንባብያን መካከል የሚሰራጭ፣ እንዲያውም በገዳማትና በአድባራት የሚቀመጥ፣ ከተራው ሕዝብ የራቀ የመጠቀ ነበረ። ቆይቶ ቆይቶ ተነባቢ ጽሑፍነቱ ሳይሆን ታሪካዊ ዕቃነቱ የጎላ ሆነ።

ስለዚህ በቤተ ክህነቱ ዙሪያ ያሉትም ከላይ አለቃ ኪዳነ ወልድ እንዳሉት "መጽሐፍ ዐዋቆች ... ጥፈት የማያውቁ" ሆነው ተከታታይ ባሕላችን የቃል፣ የንግግር የድጋም፣ እንጂ የጽሑፍ የንባብ መሆኑ ጎልቶ አይታይም።

የንባብ ታሪካችንን ለማስተንተን ዕውቀቱና ጊዜው ያላቸው ሰዎች እንዲሰማሩበት ትቼ እኔ አሁን የሚያሳስበኝና የሚያነጋግረኝን ጉዳይ ብቻ በግርድፉ ልነካካ። ይህም ጉዳይ "ብዙና ጥልቅ አንባቢዎችን እንዴት እናፍራ?" የሚል ነው።

## አሁን ያለው የንባብ ሁኔታ

በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዙሪያ ያለውን የንባብ ትጋትና እድገት አጠቃላይ አመለካከት ስንቃኝ በአንድ ፊት የሚያስደስት የሚያበረታታ ሆኖ የሚታይ ሲሆን፣ ከተገባው አንጻር ደግሞ ገና በእንፉቅቅ የሚሄድ፣ ጉልበቱ ያልጠና ልጅ



ነው። 'የሚያበረታታው ምንድነው?' ቢባል፣ በተለይ ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ ኦርጂናል ጽሑፎች እየተጻፉ መሆናቸው፣ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የአገር ውስጥ መጽሔቶችና ጋዜጦች በአንባቢው እጅ መግባታቸው፣ ዋጋቸው የሚያስፈራራ መጻሕፍትን እንኳ አብያተ ክርስቲያንና ግለ ሰቦች እየገዙ መጠቀማቸው ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ሲታይ የሚያነቡትና የሚጽፉት ሰዎች ከጠቅላላው ፊደል አንባቢ የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ቁጥር ጋር ሲተያይ በጣም ትንሽ ሆኖ እናገኘዋለን። አሁን በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ለምናየው ግልብነትና ጥራዝ ነጠቅነት አንዱ መነሻ በቂና ጥልቅ ንባብ አለመደረጉ ይመስለኛል።

ፊደል ማንበብ የማይችለውን ትተን «የተማረ ማይሙን» ጉዳይ ብቻ ብናጤን 'ለምንድነው የማያነበው?' የሚለውን ጥያቄ ለመጠየቅ እንገደዳለን። ምክንያቶቹ ብዙ ናቸው ከእነዚህ መካከል፦

- የትመጣችን በዚህ የንባብ ትጋት አላሳደገንም። አብዛኞቻችን ቤተ ሰብ፣ ትምህርት ቤት፣ ኅብረተ ሰብ መጽሐፍ እያነበብን እንድናድግ እጅግም የሚያበረታታ አልነበረም፤ ግድ ካልሆነብን በስተቀር ወረቀት ማገላበጥ የወትሮና የደስታ ሥራ አልነበረም። መጻሕፍት ለተወሰኑ ተመራማሪዎች የተሰጠ ከነፍስ ውቅራቸው ጋር የተያያዘ እንጂ ለሁሉ ሰው የሚሆን ጉዳይ እንደ ሆነ አይታሰብም። የንባብ ነገር ካህናቱ እንጂ ጨዋውን ሰው የሚመለከተው አልነበረም። በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም ሰባኪውና ወንጌላዊው ከየቦታው በጥራዝ ነጠቅ የዘረፈውን ያሰማል እንጂ፣ ማመሳከርም መጠያየቅም አልተበረታታም። ስለዚህ ድንገት ተነሥተን አንባቢዎች ልንሆን አንችልም።
- በቋንቋችን የተዘጋጁ በቂ መንፈሳዊ መጻሕፍት የሉንም፤ ያሉት ጥቂቶችም በአጻጻፍ ስልትም ሆነ በፍሬ ዐሳብ ክምችት የሚያጓጉን ሆነው አልተገኙም፤ ያለንበትን ሁኔታ በበቂ ያነጣጠሩና ደልዳላ መልስ የሚሰጡን አልሆኑም።

- ለማንበብ የሚጋብዙ ቁሳዊ ምቾቶች የሉንም መጽሐፍ መግዣ ገንዘብ፣ ጥሩ የማንበቢያ ሥፍራ፣ ከዕለት ውጣ ውረድ የሚተርፍ በቂ ጊዜ ወዘተርፈ... የለም። በተለይ በከተሞች ያለው ኑሮ ጫጫታ የበዛበት ማኅበራዊ ግንኙነቶች ስፊ ሥፍራ የያዙበት አስባታሊ ሕይወት ሆኗል።

- ከተሞቻችን አሁን ምዕራባዊ ልማዶች እየለወጡዋቸው መጥተዋል። ከእነዚህም አንዱ ከፊደል ንባብ ይልቅ ወደ ተንቀሳቃሽ ሥዕልና ድምፅ የሚሄድ አዝማሚያ ነው። ከሳቢነትና ከቀላልነት የተነሣ በኢንተርኔት የሚቀርበው፣ ቪዲዮ ፊልሞችና ሲዲዎች እንዲሁም ካሴቶች እየተመረጡ በጥሞና ሆኖ መጻሕፍትን የማንበቢያ ዘመን ያረጀ እያስመሰለ ነው።

- ምናልባት ከመጻሕፍት ንባብ የሚገኙትን ጥቅሞች በውል ካለመረዳት የተነሣ ችል ማለት ደግሞ ሌላ ምክንያት ነው።

እነዚህን የሚመሳሰሉ ሌሎችም ምክንያቶች ሊነሡ ይችላሉ።

## በትጋት እንዲነበብ

ለምንድነው አንባቢ እንዲበዛ የምንፈልገው? መጻሕፍትስ የምናበራክት ምን መተኪያ የሌለው ጥቅም ተገኝቶበት ነው? እንደ ፈረንጆቹ አባባል የዚህ ዘመን ሰው ድኀረ ንባብ ሆኖ እንደ ሆነ ሌሎች የመረጃና የዐሳብ መለዋወጫ መሥመሮች እያየሉና የድሮውን እየተኩ ከመጡ ከፊደል ጋር መታሸታችን ምን ፋይዳ ይሞላል?

በዐይንና በጆሮ በኩል መረጃ የሚያቀብሉን፣ የሚያዝናኑንና ስሜታችንን የሚቀሰቅሱ ዘመናዊ መገናኛዎች በፊናቸው የሚጠቅሙት እንዳለ ሆኖ ጽሑፍ ራሱን የቻለ ጠቀሜታ አለው። የንባብ አንዱ ዋና ጥቅም በአንባቢው የማሰብ፣ የማሰላሰል፣ የማስተናገድ፣ የማዋሓድ፣ የመረዳት ፍጥነት ቁጥጥር ውስጥ ሊውል መቻሉ ነው።

ሁለተኛ በዐሳብ ስክነትና ጥልልታ፣ በስብስብነት በኩል ከሌሎች የላቀ መዛሪያ መሆኑ ነው።

ሦስተኛ ከሌሎቹ ይልቅ ለስርጭትም ሆነ ለአያያዝ የተመቸና



ወጪው ቀላል መሆኑ ነው።

አራተኛ የሚያስተናግደው እርእስትና የሚያካትታቸው ባለ አእምሮ ሰዎች ቁጥር በጣም ከፍ ያለ መሆኑ ተዝቆ የማያልቅ የባሕር ሀብት ክምችት ያደርገዋል። እንግዲያው ከአሁኑ የተሻለ ንባብ እንዲገኝ ጥረት ልናደርግ ይገባል። የጥረቱን አግጣጫ ለማሰብ ልቡናችንን የሚያነቃቁ አንዳንድ ነጥቦች ልሰንዝር።

## ፩ኛ የንባብ ልምድን ማጠናከር/ማስተማር

ብዙ ሰዎች ማንበብ ያውቃሉ እንጂ አያነቡም። እንደ መብላት፣ እንደ መጠጣት፣ እንደ ማውራት፣ እንደ መተኛት፣ ጥርስም እንደ መቦረሽ ማንበብ ሊለመድ ይችላል፤ ይህን ለማስለመድ ሦስት ቤቶች ሊነሡ ይችላሉ።

- ቤተ ሰብ፦ ትዳር ሳይመሠረትና ልጅ ሳይወለድ በፊት ለልጆቹ መጻሕፍት እየገዛ ስለሚያስቀምጥ ሰው ሰምቻለሁ፤ ለመልመድ የተመቸ ጊዜ የልጅነት ጊዜ መሆኑ አያጠያይቅም። ክርስቲያን ቤተ ሰቦች ልጆቻቸውን ንባብ እንዲለምዱና እንዲወዱ በግድ ሳይሆን በጉጉት እንዲያነቡ ለማበረታታት ማሰቢያው ጊዜ አሁን ነው። ለዕቅማቸው የሚመጥነውን በማቅረብ፣ በመለዋወጥ፣ ያነበቡትን በመጠየቅና አብሮ በማንበብ ወዘተርፈ ... ሊታገዙ ይገባል።

- ቤተ ክርስቲያን፦ ሰባክያንና መምህራን ራሳቸው አንባቢዎች ከሆኑ ለዐሳባቸው ማዳበሪያ የትኛው ጽሑፍ እንደረዳቸው ቢናገሩ፣ አድማጮቻቸውን እንዲያነቡ ቢመክሩ፣ ሐኪም ልዩ ልዩ መድኃኒት እንደሚያዝ የንባብ ጥቆማ ቢያደርጉ ብዙዎች ከየት ልጀምር? ምን ላንብብ? ለምን ላንብብ? የሚሉ ጥያቄዎቻቸው በጥቂቱ መልስ ስጡ ማለት ነው።

- ቤተ ትምህርት፦ ሁሉም ትምህርት ቤቶች፣ በተለይ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች በክፍል ውስጥ ከሚሰጠው የቃል ትምህርት በተጨማሪ ተማሪዎች በገዛ ንባባቸው መሠረት ጥናት እንዲያደርጉ ሊያበረታቱዋቸው ያስፈልጋል። ትም

ህርት ቤቶች የንባብ መናኸሪያ፣ የዐሳብ ገበያ ሊሆኑ ይገባል።

## 2ኛ ተገቢና ተነባቢ ጽሑፎች ማቅረብ

አሁን አዘውትረው የማያነቡ ሰዎች ልቡናቸውን ጠቅ የሚያደርግ፣ ነፍሳቸውን የሚመግብ፣ ስሜታቸውን የሚያነቃ ጽሑፍ ካገኙ ለማንበብ ይገፋፋሉ። ለዚህ ጽሑፍ ዝግጅት ከመጻሕፍት ሻጮችና ከአንባቢዎች ጋር ያደረግሁት ጥቂት ቃለ መጠይቅ እንደሚያመለክተው ሰዎች የንባብ ዐይነት መራጮች ናቸው። ያሉበትን ሁኔታ ያገናዘበና ለንባብ ምላሳቸው ጣም የተስማማ ነገር ሲያገኙ በትጋት እንደሚያነቡ ታይቷል።

"ምን ዐይነት ጽሑፎች ይበልጥ ይነበባሉ?" ለሚለው ጥያቄ ያገኘኋቸውን መልሶች ሳሰባስብ እንደዚህ ዐይነት ዝርዝር ይሠራል፡-

*እውነተኛ ታሪኮች፡-* የክርስቲያን ውጣ ውረድን፣ የእምነት አለማመን ትግሉን፣ የአገልግሎት ፈተናን፣ የእግዚአብሔር ማዳን ምስክርነቶችን ወዘተርፈ... የሚተርኩ መጻሕፍት በጣም ከሚወደዱት መካከል የመጀመሪያዎቹ ናቸው። የክርስቲያን መሪዎች ሕይወት ልክ እንደ መፍሐፍ ቅዱስ ጀግናች ውድቀቱ ሳይደበቅ፣ ትግሉ ሳይለሳለስ፣ የእግዚአብሔር ተአምራት ሳይቀነስ ቢጻፍ አንባቢው ብዙ ነው።

*ለነጋገሪ የሥነ መለኮት ጭብጦች፡-* ብዙ የቤተ ክርስቲያን ሒያጅና ከዚህም ውጭ ያለ ሰው ነገረ መለኮትና የመንፈሳዊ ሕይወት አካሄድ ላይ ጥያቄው በገፍ ነው። በጥናት የተደገፈ፣ የበሰለ ትንታኔ ካገኘ በጉጉት ያነባል። ትምህርተ ሥላሴ፣ የእምነት ባሕርይ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታና አገልግሎት፣ የቤተ ክርስቲያን ሥልጣንና ማንነት፣ የጨለማው ዓለም ተግዳሮትና የክርስቲያን ጦርነት ጆሮ የሚያነቁ አርእስት ናቸው።

*ጋብቻና ለውስበን የሚመለከቱ ምክሮች፡-* በየትኛውም ዕድሜ ያሉ ሰዎች ጋብቻን የሚመለከት ተግባራዊ ምክርና የሰዎች ሕይወት ልምምድ ማንበብ ይወዳሉ።

*ለዳዲስ ንቅስቃሴዎችን የሚያስተነትኑ፡-* ጊዜ ተርጓሚ፣ ትንቢት አገናዛቢ፣ ጽሑፎች ለምሳሌ ስለ አዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ፣



ስለድኅረ ዘመናዊነት የሚያስተነትኑ ሥራዎች ሌሎቹ ተፈላጊ መጻሕፍት ናቸው።

*"እንዴት እንደሚሠራ" የሚጠቁሙ መጻሕፍት፡-* ይህ ዐይነቱ ጽሑፍ በአማርኛ መጻሕፍት እጅግም ያልተሞከረ፣ ነገር ግን በጣም ጠቃሚ የሆነ የጽሑፍ ዐይነት ነው። "ራስን መግደል የሚፈልግን ሰው እንዴት እንደምትረዳ"፣ "አስቸጋሪ የቤተ ክርስቲያን መሪዎቻችንን እንዴት እንደምናሠለጥን"፣ "ቀጠሮ አክባሪ መሆን እንዴት እንደሚቻል"፣ "አሉድ ጧት አምልኮ እንዴት እንደሚመራ"፣ "ፀጉርህን ሳትነጭ ልጅህን እንዴት እንደምታሳድግ" የሚጠቁሙ የመጻሕፍት ዐይነት ናቸው።ሰዎች ዘዴን፣ የአሠራርና ብልኀትን ማወቅ ይፈልጋሉ። በዚህ አግጣጫ የሚጻፉ መጻሕፍት አንባቢ አያጡም።

*ለቅበተ እምነታውያን (Apologetical) መጻሕፍት፡-* መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እምነት ከጥቃት የሚከላከሉ ማስረጃ እያቀረቡ የሚሞግቱ መጻሕፍት ይፈለጋሉ።

ልጆችና አዳጊ ወጣቶች ሊያነቡዋቸው የሚችሉ መጻሕፍት በጣም ይፈለጋሉ። ከእነዚህ ሌላ፣ በዓለም ዙሪያ ስላለው ቤተ ክርስቲያን ቅስቃሴ እውነተኛ ዜና፣ ክርስቲያናዊ ልቦለድ፣ ግጥም፣ የክርስትና አኗኗርን የሚያመለክቱ ትምህርቶች ወዘተርፈ... ሊነበቡ የሚችሉ ናቸው።

ከመጻሕፍት አርእስትና ዐይነት ሌላ የጸሐፊዎቹም ማንነት ለንባብ ለመጋበዝ አንድ ዋና ምክንያት እንደ ሆነ መጽሐፍ ሻጮች ነግረውኛል። "ማነው የጻፈው?"፣ "የእገሌ መጽሐፍ አላችሁ?" ተደጋግመው የሚጠየቁ ናቸው።

እዚህ አገር በጣም ከተለመዱትና ከሚነበቡት የውጭ አገር ጸሐፊዎች አንዳንዶቹ፡- ዎች ማን ኒ (Watchman Nee)፣ ቤኒ ሂን (Benny Hinn)፣ አንድሪው መሬ (Andrew Murray) ጆን ስቶት (John Stott)፣ ቢሊ ግራሃም (Billy Grahm)፣ ካትሪን ኩልማን (Kathryn Khulman)፣ ጆይስ ሜየር (Joyce Meyer)፣ ዴቪድ ዊልከርሰን (David Wilkerson) ጆን ፓይፐር (John Piper) ማይልስ መንሮ(አንዳንድ ትምህርቶቹ አጠያያቂ ቢሆኑም Myles Munroe) ሲኤስ ሉዊስ (CS Lewis) ሪክ ዋረን(Rick Warren) የተሰኙት ናቸው።

ሌላው ከዚሁ ጋር የሚያያዘው የተርጓሚው ማንነትም አብሮ ይታያል። በእኛ ቋንቋ የሚጽፉትም ቢሆን ማንነታቸው በአንባቢዎች ላይ ሁነኛ ተጽእኖ እንዳለው ሰምቻለሁ። አዳዲስ ጸሐፊዎችን ወደ ንባብ ገበያው መሳብ በጣም አስፈላጊ ይመስለኛል። ቀስ በቀስ ሲለመዱ የምርጫውን ጠርዝ ሊያሰፉት ስለሚችሉ።

### 3ኛ የንባብ ቤቶችን ማቋቋም

ሁሉ ሰው መጽሐፍ ሊገዛ አይችልም፤ ሊገዛ የሚችለውም ሊነበብ የተገባውን ሁሉ እንዲገዛ አቅሙ አይፈቅድም። ስለዚህ የመጻሕፍት ቤት አስፈላጊነት አያከራክርም። በአዲስ አበባ (ትልቋ ከተማ) እንኳ ያሉትን መጻሕፍት ቤቶች እንቁጠር ብንል የእጅ ጣቶቻችንን ቁጥር መዝለላቸውን እንጃ። ክርስቲያናዊ መጻሕፍት ቤቶችማ እንዲያውም ያንሳሉ። ከመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶች ጋር የተያያዙት ካልሆኑ በስተቀር ለንባብ የተመቹ ሥፍራዎች የሉንም። በዚሁ የምሰነዝረው ዐሳብ ትልልቅ ቤተ መጻሕፍት የማደራጀት ሳይሆን ጥቂት የተመረጡ ቤተ መጻሕፍት በየቤተ ክርስቲያኑ አንድ ጥግ/ክፍል እንዲሰጣቸው ነው። ለምን ጋዜጣ ገዝተን ጠረጴዛው ላይ አንበትንም? ከዚያ መጀመር እንችላለን። አሮጌ መጻሕፍት ከየቤቱ አንድ አንድ እንዲያመጡ ብናስታውቅስ?

### ነገረ ባጭሩ

ነፍስ በቂ የእውቀት ምግብ ስታጣ ትራባለች፣ ትክሳለች፣ ትጠወልጋለች። ቤተ ክርስቲያን የጥውልጎች መንጠራወዣ እንዳትሆን ያሰጋል። በእውነት ረኀብ የተጠማች ነፍስን ከየትም አግጣጫ የሚውሰበሰብ ነፋስ ያንገላታታል፤ ይነቅላታል፤ ያንገዋልላታል። ሕዝብም በኅብረት ሊፍገመገም ይችላልና ሥር የሰደዱ መሠረተ ጽኑ ምእመናንን ለማፍራት ማንበብ፣ ማስነበብ ጠቃሚ ተግባር ነው።



# ኢትዮጵያ እና የተሲፋ ጥበቃ

## በስሙ የተጓደድንባቸው ተስፋዎች የት ደረሱ?

(ፕሮፌሰር አታላይ ዓለም እና ንጉሤ ቡልቻ)

### መንደርደርያ

ስለ አገራችን ስለ ኢትዮጵያና ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ሕዝቦቿም የተነገሩትን ተስፋዎች አስመልክቶ የቀረበው ይህ ጽሑፍ በርእሱ እንደ ተገለጸው ጥያቄ ለማስተጋባት የተጻፈ ነው። ጥያቄው የሁላችን እንደ ሆነ በመገመት ለእኛው ለራሳችን ይህንኑ ጥያቄ ያቀርብልናል፤ ለመጠያየቅ እንዲመችን ማኮብኮቢያ ሜዳም ይጠርግልናል።

ይህንንም ሲያደርግ፣ ብሔራዊ የለውጥ ጉጉት መኖሩን፣ ተስፋው የተነገረባቸው መደቦች ምን እንደ ሆኑ፣ የተስፋው ዐዋጅና የነባራዊው ሁኔታ ግርምቢጥ(አይገጥሜ) አተያይ ምን እንደ ሆነ፣ የተስፋው አስተሳሰብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ዕይታ አንጻር ምን እንደሚመስል እና ወደ ጤናማ ተስፋዊነት የሚደረገው ጉዞ ምን መምሰል እንዳለበት እየጠቆመ ነው።

### የሁለንተናዊ ተሐድሶ ጥማት

ኢትዮጵያውያን ባለፉት ኀምሣ ዓመታት ውስጥ የአገራቸውን

ሁኔታ ከውጪው ዓለም ጋር እያስተያዩ ስሜታቸው ሲወድቅ ሲነሣ፣ ተስፋቸው ሲለመልም ሲስለመለም ቆይቷል። ኢትዮጵያዊነት ኩራትም ሐፍረትም እየሆነ ከዛሬ ነገ ይሻል ይሆናል በሚል የተስፋ ቀጭን ክር እየተሳሳብን እስካሁን አለን።

ይህ የተስፋ ጥበቃ ሁሉን አቅጣጫ ያካለለ ሥጋዊም መንፈሳዊም ነው። "የአፍሪቃ የዳቦ ቅርጫት" የሚለውን ሐረግ ማን መጀመሪያ እንዳለው ባናውቅም፣ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እምቅ ሀብት እንዳላት ተነግሯል። በተለይም በግብርናው ዘርፍ ትልቅ ተስፋ ተጥሎ እንደ ነበር አይዘነጋም። በአፍሪቃ አንድነት መሥራችነትና የቀድሞው ንጉሥ በነበራቸው ዓለም አቀፍ ተሰሚነት ምክንያት ከፍተኛ የፖለቲካ ተጽእኖ ልታመጣ የምትችል አገር እንደ ሆነች ሲታሰብም ኖሯል።

በቤተ ክርስቲያን በኩል ምናልባት ከሌላው መስክ ሁሉ በበለጠ ሁኔታ የተስፋ ጥበቃ ነበር ለማለት ይቻላል። ታላቅ መንፈሳዊ ኀይል በዚህች አገር እንደሚገለጥ፣ የእግዚአብሔር ልዩ የጉብኝት ጊዜ እንደሚመጣ፣ የወንጌል መልእክት ከዳር እስከ ዳር እንደሚያስተጋባ፣ የመንፈስ ቅዱስ ድንቅ ሥራዎች ደምቀው እንደሚታዩ፣ ከብሔራዊ ድንበራችን ውጪ የአካባቢውን አገሮችና በሩቅ ያሉትንም ሁሉ ትኩረት የሚስብ መንፈሳዊ መነቃቃት እንደሚሆን፣ ዓለም አቀፋዊ ተጽእኖ የሚያመጣ የእግዚአብሔር ሥራ ከዚህች አገር እንደሚጀመር ተስፋ ሲደረግ ቆይቷል። እነዚህ ብሔራውያን የሆኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና መንፈሳዊ ተስፋዎችና ጥበቃዎች አሁን አሉ ወይ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ስንደረደር፣ በአንዳንድ ሥፍራ በከፍተኛ ስሜት ተጠናክረውና ከርረው የሚገኙ ሲሆን በሌሎቹ ደግሞ ባብዛኛው በተስፋ ደረጃ ያልተገኙ እንኳ ቢሆኑ ቢያንስ ምኞቶች፣ ጉጉቶችና ናፍቆቶች ሆነው እስካሁን በየሰዉ ልቡና እንደሚጉላሉ መናገር ይቻላል።

በየምስባኩ የሚደመጡ ስብከቶቻችን ውስጥ አልፎ አልፎ ይኸው ብሔራዊ ተስፋ መስተጋባቱ አልቀረም። *"ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች"* የሚለው የመጽሐፈ መዝሙር ቃል እንደ ባንዲራ ሆኖ ስለ አገር በተነሣ ቁጥር የሚጠቀስ ዋና መፈክር ሆኗል። ከዚህም ተነሥቶ የምዕመናን ልብ ለዚህ ድንቅ ጊዜ እንዲዘጋጅና አጥብቆም ተስፋ እንዲያደርግ ሲሰበክ ቆይቷል፤ አሁ ንም ይሰበካል። በዚሁ አንጻር እንዲህ ዓይነቱ የተስፋ ስብከት አንድም በማያገባን ነገር ውስጥ ያለብልሃቱ



እየገባን መቀባጠር፤ አንድም የወንጌልን እውነተኛ ተስፋና የጌታ መገለጥ ጥበቃ እንደማጠናከር ጊዜያዊ በሆነ እርግጠኝነቱ ባልታወቀ ምናልባትም ከብሔራዊ ጥሬ ስሜት በበቀለ አጉል ጉጉት ተነሥቶ የሕዝብን ዓይን ማንሸዋረር እንደሆነ የሚቆጥሩ ወገኖች የሚያሰሙት የማስጠንቀቂያ ድምፅ አለ።

ይህ ሁሉ ጉራማይሌ ቀለም ባለበት የክርስቲያን ማኅበረሰብ ውስጥ መኖራችንን ተገዝበን ጉዳዩን በጥሞና ውይይትና በማስተዋል ምርመራ መያዝ ገና ከመነሻው ተገቢ ነው እንላለን።

## የተስፋ ወዋጆች መደብ

ስለ አገራችን ስለ ኢትዮጵያ የተሰጡት ተስፋዎች በልዩ ልዩ መንገዶች የቀረቡና ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተደመጡ ናቸው፤ መልካቸውም ባለብዙ ኅብረ ቀለማት ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለነው አብዛኛውን ጊዜ እነዚህ ተስፋዎች በጸሎት ጉባኤዎች ላይ በትንቢት የተነገሩ ናቸው። አንዳንድ ጊዜምም በራእይና በሕልሞች ለግለ ሰቦች ከታዩ በኋላ ለማኅበሩ በቃል ሲነገሩ የተደመጡ ናቸው።

የዛሬ 45 ዓመት ገደማ ከተነገሩት ትንቢታዊ ቃሎች መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፦

> የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፦
>
> ‹‹በምድራችሁ ላይ የጨለማ፣ የድቅድቅ ጨለማ ጊዜ አለ። ከዚያም የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላች ኋለች። ፈውስም በክንፎቿ ሥር አለ። በከፍታ ላይ አወጣችኋለሁ፤ ለብዙዎችም መጠለያ ትሆ ናላችሁ። የወደቀውን መስቀሌን አነሣለሁ፤ ከመ ስቀሌም ብርሃን ይወጣል፤ በባህር ማዶ ምስክሮቼ ትሆናላችው። ድንቄን ታምራቴን በላይ በሰማይ አሳያለሁ።
>
> እሳት በባሕር ተጭኖ በሰሜን በኩል ወደ አገራችሁ ገባ። በሰሜን ታላቅ እልቂት ይሆናል፤ የወንድም ሰይፍ በወንድሙ ላይ ይሆናል፤ ይህን የማመጣባችሁን ኀይል ልትቋቋሙት አትችሉም፤ በፊቱ እንደ ምናምን ናችሁ።

> ሕዝቡ ወደ እኔ ቢመለስ እኔ አደጋውን እመልሰዋለሁ፤ እኔም እንደመለስኩት ያውቃል፤ እግዚአብሔር መሆኔን ያውቃል። አለበለዚያ የእሳት በረዶ በምድራችሁ ላይ ይዘንባል። ብዙ ደኾች ያልቃሉ። በዋና ከተሞቻችሁ የደም ጐርፍ ይጎርፋል፤ ከምሥራቅም ሌላ ይመጣባችኋል፤ ምድሪቱ ዙሪያዋን የተፈታች ትሆናለች።››

ስለ አገራችን ቤተ ክርስቲያንና ስለምድሪቱም የተነገሩት ትንቢቶች መንታ መልክ ይዘው ይገኛሉ። በዚህች አገር ላይ ታላቅ መርገም፣ ፍርድ እንዳለ፣ በቤተ ክርስቲያንም ማለት በእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ ያለው የሕይወት መልክ ይህንኑ ፍርድ የሚያፋጥን የሚያከብድም እንደ ሆነ ተነግሯል። ከዚህ ጨለማ የመትረፊያው መንገድ ክርስቲያን መሆን አለመሆን ሳይሆን እግዚአብሔርን መፍ ራት ወይም አለመፍራት እንደሆነም ተገልጿል። በአገራችን የክርስቶስ ተቃዋሚ እምነት ከፍ እንደሚል፣ ታላቅ ከፍታ ላይ ሲደርስም እንደሚወድቅ ተነግሯል። የእግዚአብሔር ቃል ድርቅ/ራብ እንደሚመጣ፣ የርስ በርስ ጦርነትም እንደሚሆን ተነግሯል።

ከዚህ አስከፊ የፍርድ ወቅት በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር ለምድሪቱ ልዩ በረከት እንደሚያፈስላት በትንቢት ቃል ተነግሯል። ይህ በረከት ሥጋዊውንም መንፈሳዊውንም አጽናፍ የሚመለከት እንደ ሆነ ከዚህም ታላቅ ሁለገብ በረከት የተነሣ ብዙዎች ወደዚህች ምድር ናፍቀው እንደሚመጡ፣ ብዙዎችም ከዚህች አገር ተነሥተው ወደ ዓለም ዙሪያ ሁሉ ወንጌሉን ለማድረስ እንደሚሔዱ፣ እጦት የሚለው ቋንቋ እንደሚረሳ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚጐበኝ ተነግሯል።

በእነዚህ ትንቢቶች ውስጥ በተደጋጋሚ የምናየው የፍርድና የምሕረትን ግንኙነት ብቻ ሳይሆን የአገርንና የቤተ ክርስቲያንንም ግንኙነት ነው። በሕዝበ እግዚአብሔር ዘንድ ያለው የሕይወት አቋም በምድሪቱ ላይ የሚሆነውን ነገር እንደሚነካ ወይም እንደሚወስን ተመልክቷል።

"የከፍታ ዘመን ለኢትዮጵያ" በተባለው መጽሐፍ ቄስ በሊና ሣርካ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለኢትዮጵያ በተለይ በኢኮኖሚ ዘርፍ ከፍተኛ ለውጥ እንደሚመጣ ተናግረዋል። በሦስት ክፍለ ጊዜያት በራእይ እንደተመለከቷት በሚገልጿት ኢትዮጵያ እጅግ



ላቅ ያለ የግብርና፣ የኢንዱስትሪ የማዕድናትና የመንገዶች መስፋፋት እንደሚመጣ ተናግረዋል። *"[ኢትዮጵያ] ከጎረቤቶቿ ጋር ሰላም ይኖራታል። ያኔ ኢትዮጵያን የጎረቤቶቿ የምግብ ማዕድ በዙሪያዋም ላሉ አገሮች የበረከት ምንጭ አደርጋታለሁ፤ ስለ ስሜ ስል እፈጽመዋለሁ።" (ገጽ 58)*

በመንፈሳዊ በኩልም የሚሆነውን ሲያመለክቱ፦

> ለወንጌል ስርጭት በአገርና ከአገር ውጭ በስፋት የተሰማሩ አገልጋዮችን አየሁ። በታላላቅ ድንቅና ታምራት የሚያገለግሉ አገልጋዮችን በኢትዮጵያ ውስጥ ሲያድጉ ተመለከትኩ። ‘ብዙ ወጣቶችም ወደ ምሥራቅ አገራት ለሚሲዮን ሥራ ይሄዳሉ። በድንቅና በተዓምራት ታጅበው በኀይልና በሥልጣን እየተናገሩ ሕዝብን ወደ እኔ ያፈልሳሉ አለኝ ጌታ። ኢትዮጵያውያን በመንፈሳዊ አገልግሎት ለዓለም እንደ መድኃኒት የምንፈለግበት ዘመን እንደሚሆን አየሁ። ለዓለምም መንፈሳዊ ተሐድሶን እንደምናመጣ ተረዳሁ... ክብር ለሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይሁን። አሜን (ገጽ 75)

ይሁን እንጂ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደ ተገለጸው እነዚህ ነገሮች ከመሆናቸው በፊት ፈታኝ የሆኑ ከባድ የመከራ ዓመታት እንደሚመጡ ተገልጿል።

> ፖለቲካዊና መንፈሳዊ ትግሎች ይፋፋማሉ፤ ... ሥርዐት አልበኝነት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የድንበር ግጭቶች ይስፋፋል፤... አብያተ ክርስቲያንም ሆኑ ምዕመናን በመካከላቸው አለመ ረጋጋትና መለያየት ይሆንባቸዋል። መሠረቷ ክርስቶስ የሆነላት ቤተ ክርስቲያን ጨውነቷ ጠፍቶባት ስትንገደገድ፣ እርስ በርስ ስትነቃቀፍ አየሁ። ጥላቻ ሲበዛ እግዚአብሔርን መፍራት ቀርቶ የልምድ አምልኮ ቤተ ክርስቲያንን ወርሷት እግዚአብሔር አሳየኝ፤... ፖለቲከኞችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እርስ በርሳቸው ይወዳደሳሉ፤ ስለ እውነት የቆሙ ከአደባባይ ላይ ይጠፋሉ (ገጽ 71)

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ግን ምድራቱ ላይ ያለውን የነዘን ልብስ እግዚአብሔር እንደሚያነሣ ልብሱም ሲገፈፍ ሰውም ፍጥረቱም በነጻነት ሲንቀሳቀስ እንዳዩ ተናግረዋል።እዚህ ላይ

ለመሆኑ እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ስለ አንድ አገር ነጥሎ ይናገራልን፤ ዓለሙ ሁሉ መስካችን አይደለምን?አገራዊ ተስፋ እየሰጠ የሰውን ልብ ማማለል ከሰማይ የሚገለጠውን ጌታ ከመ ጠበቅ ይልቅ ምድራዊ ፍስሐ እንዲኅን የሚያዘናጋ መሠሪ አካ ሔድ አይደለምን? ኢትዮጵያ ቅድስት ሀገር ሆነችን? ወዘተረፈ። የሚሉ ጥያቄዎችን እንዴት እንያቸው መባባል ያስፈጋል።

እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመንም ይሁን በአዲስ ኪዳን ዘመን ስለ አገሮች ስለሕዝቦች ፤ ስለዘመናትና ስለመሪዎች እንደሚያስብ እናውቃለን። እንዲያውም ይህ የአገርና የዘመን አቀራረጽ ከእርሱ መለኮታዊ ዓላማና ዕቅድ ጋር የተገናኘ ስለመሆኑ ሐዋርያው ጳውሎስ ለአቴናውያን ባቀረበው ስብከቱ ላይ በተናገረው ቃል ፍንጭ ሰጥቷል።

‹‹--ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፤ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው።›› (ሐዋ17:26-27) ይለናል። ድንበር የለሽ የክርስቶስ ወንጌል በየአገራቱ በየሕዝቡ መካከል ሲሠራጭ እግዚአብሔር በጊዜው የነበሩትን የአገራትና የመንግሥታት ሥርዐ ቶችና ሥልጣኔዎች ለዓላማው መጠቀሚያ እያደረገ ቀጠለ።ወደ ልዩ ልዩ አገራትም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ሐዋርያቱ ተሰማሩ። መንፈስ ቅዱስ በየጊዜው በግለሰቦችም ይሁን በሕዝቦች ላይ የሚ መጣውን ነገር በትንቢት መንፈስ እያመለከተ ያስጠንቀቅ ያሳስብ ነበረ። ለምሳሌ በዚያ ዘመን በዓለም ላይ ስለሚመጣ ታላቅ ራብ በሐዋርያው ጳውሎስ ላይ ስለሚደርስ እስራትና መከራ በትንቢት ቃል ተነግሯል ። (ሐዋ 11:27-30 ፤ ሐዋ 20:11)

በብሉይ ኪዳን ስለ ልዩ ልዩ አገሮችና መንግሥታት ፍርድና ተስፋ የተናገረ አምላክ አሁን በዚህ ጉዳይ መናገሩን አቁሞአል የሚያሰኝ ምን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ አለ? ስለ አሁኑና ስለሚመጣው ዘመን ሲናገር የሚችለው ቅዱስ መንፈስ ዛሬ ምንም አይናገርም ለማለት በምን ሁኔታ እንደፍራለን? ይልቁን መጠየቅ ያለብን ዛሬ ስለ ኢትዮጵያ የተነገሩት የተስፋም ይሁን የፍርድ ቃላት ከመንፈስ ቅዱስ መሆናቸውን በምን እናውቃለን?



እርሱስ ተናግሮ ቢሆን ከዋናው የጌታ ተስፋ አንጻር እነዚህን ጥቃቅን ተስፋዎች እንዴት ልንመለከታቸው ይገባል? የሚል ዐይነት መሆን የሚገባው ይመስለኛል።ሌላ መጠየቅ ያለበት ብርቱ ጥያቄ ብሔራዊ ጉጉታችንን ከጌታ ድምጽ ጋር ምናልባት ተምታትቶብን እንደሆንስ የሚል ራስ መርማሪ ጥያቄ ነው።

ከትንቢት ቃሎችና ከራእይ መገለጦች ሌላ በስብከቶቻችንና ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በተጻፉ ጥቂት መጻሕፍት ውስጥ ይኸው ብሔራዊ ተስፋ ሲነገር ይደመጣል። በእነዚህ መንገዶች የሚሰጡት መገለጫዎች መሠረት የሚያደርጉት በአብዛኛው በመዝሙር 68 ቁጥር 31 ላይ ያለውን “ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።” የሚለውን ዐረፍተ ነገር ነው።በዚህ ጥቅስ ዙሪያ ብዙ ዐሳቦች ሊቀርቡ የሚችሉ እንደ መሆናቸው አተረጓጐሙም የተለያየ መልክ ሊይዝ ይችላል። ከሚነሡት ጥያቄዎች አንዱ በመጽሐፍ ቅዱስ “ኢትዮጵያ” ተብላ የተጠራችው አገር ይህች ያሁኒቷ፣ የኛ ኢትዮጵያ ናትን? የተነገሩላትስ ተስፋዎች ተፈጽመው ይሆን ወይስ ገና የሚጠበቁ ናቸው? የሚሉ አነጋጋሪ ጉዳዮች ናቸው።

ኢትዮጵያ ወይም ኢትዮጵያውያን በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ ለ40 ጊዜ ያህል ተጠቅሰዋል። በተጠቀሱበት ቦታዎች በልዩ ልዩ መንገድ በፍርድም በተስፋም በታሪካውያን ድርጊቶችም የተነገሩ ቃሎች አሉባቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰችው ኢትዮጵያ በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ስያሜዋ "ኩሽ" በሚል ቃል የተወከለ ነው።

የእኛ አገርም ሲቃውንት የመጀመሪያው የዕብራይስጡ አጠራር “ኢትዮጵያ” ሳይሆን "ኩሽ" እንደ ሆነ ይናገራሉ። ለምሳሌ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በመዝገበ ቃላት መግቢያቸው ላይ እንዲህ ይላሉ፡-

> *“ኢትዮጵያ” ከኩሽ ሞት በኋላ በ፪ ሺህ ፱፻፺ ዓመት በበጥሊሞስ ዘመን የወጣ ሐዲስ እንግዳ ጽርአዊና ደኃራዊ ስም ነው። ሊቃናት ብሉያትን ከዕብራኒ ወደ ዮናኒ ሲመልሱ ዕብራይስጡ ኩሽ የሚለውን የኩሽን ስም ሁሉ ኢትዮፕስ ስላሉት በዚህ ምክንያት ከግብፅ ወዲህ ያለው የኩሽ አገር ሁሉ ኢትዮጵያ ተብሏል። የግእዚያ” ብሉይ ከጽርእ ስለተቀዳ እንደ ጽርኡ ኢትዮጵያ*

> *ይላል እንጂ እንደ ዕብራይስጡ ኩሽ አይልም ትርጓሜውም ጥቁር፣ ጠቋራ ማለት ነው። (ኪ.ወ.ክ. ገጽ 13 ይሉናል።)*

የውጪ አገር ሊቃወንትም ይህኑ አስተሳሰብ በሚያሳይ መልክ ያተቱት በመጻሕፍት ይገኛል። ለምሳሌም ያንግስ አናሊቲከል ኮንኮርደንስ ኢትዮጵያ በሚለው የቃል አገባብ ላይ ይህን ጽፏል፡-

> *"ኢትዮጵያ" የሚለው ቃል ዕብራይስጡ "ኩሽ" ለሚለው ስም ግሪኮችና ሮማውያን የተጠቀሙበት ልዋጭ ነው። ኩሽ የካም ልጅ ነው ዘሮቹም ከግብፅ በስተ ደቡብ ባለው አገር ይኖሩ ነበር። ይህም በሰፊ እይታ የታየ እንደ ሆነ፣ ኑቢያን ሰናርና ቆርደፋን እንዲሁም ለሜናዊውን አቢሲንያ ያጠቃልላል። በጣም ውሱን አድርገን ካየነው ግን ነጭ ዐባይና ጥቁር ዐባይ ከሚገናኙበት ጀምሮ እስከ ግብፅ ደቡባዊ ድንበር ያለውን የሜሮኤን ግዛት ብቻ ይመለከታል።" (Young's Analytical Concordance PP-308)*

የመልክዐ ምድራዊው ቦታ አስተያየት ከሞላ ጎደል እንደሚያሳየው እንግዲህ የትንቢቱ ቃል በተወሰነ መልኩ ኢትዮጵያንና ከእርሷ በስተ ሰሜን ምናልባትም በስተ ደቡብ ያሉትን የጥቁር አፍሪቃን አገሮች ሁሉ ሊያጠቃልል የሚችል እንደ ሆነ ለጊዜው እንስማማና ለዚህች ኢትዮጵያ የተሰጠው የተስፋ ቃል "እጆቿን ፈጥና ወደ እግዚአብሔር መዘርጋቷ" እንዴት ባለ መንገድ ይፈጸማል? እንበል። ብዙዎች እንደምንገነዘበው ይህ እጅ መዘርጋት ለእግዚአብሔርና ለፈቃዱ የመገዛት ምልክት ነው።

ፓ/ር በቀለ ወልደ ኪዳን በዚሁ ርእሰ ነገር ላይ ለምስክር መጽሔት በሰጡት ቃለ መጠይቅ ይህ "እጅ መዘርጋት የመሸነፍ፣ የመረታት፣ የመማረክ ምልክት ነው፤ እንደ መጽሐፉ ቃል ይህ የሚሆነው በንስሓና በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው" ይሉና ትንቢታዊው ቃል እንዴት ሊፈጸም ይችላል ብሎ ለሚጠይቅ የራሳቸውን አስተያየት እንዲህ ሲሉ ይሰጣሉ፡-

> *ኢትዮጵያ በሙሉ በንስሓና በኢየሱስ በማመን ወደ እግዚአብሔር ልትመለስ? በጥቁርና በነጭ አባይ ወንዞች ሸለቆ የሚኖሩት ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ*



> *ለኢየሱስ ሊማረኩ? የአፍሪቃ ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ እጃቸውን ለክርስቶስ ሊሰጡ? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አዎ፤ ነገሩ ለማመን ያስቸግራል፤ ነገር ግን ከዚህ መጽሐፍ ትምህርት ውጪ አይደለም። ነነዌ በአንድ ጊዜ ንስሓ አልገባችምን? (ዮና. 3፥5-10) በዚያን ጊዜ የነዋሪዎችዋ ብዛት ከአንድ መቶ ሃያ ሺህ እንደሚበልጥ መጽሐፉ ራሱ ገልጿታል። ቁጥራቸው ይህን ያህል የሆነ አረማውያን እንዴት እንደዚህ በአንድ ጊዜ ንስሓ ሊገቡ ቻሉ? ልዑል እግዚአብሔር የነቢዩን የዮናስን ስብከት የሚያምኑበትንና ንስሐ የሚገቡበትን ጸጋ ሰጣቸው ከማለት በስተቀር ሌላ የምንለው አይኖረንም (ኤፌ 2፥8-9)። ስለዚህ እግዚአብሔር መንግሥታትን ሁሉ በሚገሥጽበት ጊዜ ኢትዮጵያ ፈጥና እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች' ቢባል የማይታመንበት ነገር ሊሆንብን አይገባም። አለኝ የምትለውንና የምትመካበትን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ተራ በተራ ከእጆችዋ ባስረገፋት ጊዜ ባዶ እጆችዋን ወደ እርሱ ትዘረጋለች። (ምስክር ቁ. 15፤ ሚያዝያ 1990 ዓ.ም.)።*

እነዚህ ተስፋዎች በመዝሙሮቻችን ውስጥም ላለፉት አራት ዐሥርት ሲንጸባረቁ ቆይተዋል፤ ተስፋዎቹና ተስፋ ጥበቃዎቹ በልመናም በዐዋጅም ዐይነት ቀርበዋል።ስለ ኢትዮጵያም ከዚያም አልፎ ስለምድር ሁሉ

ኢትዮጵያን ጎብኛት

ተመልከታት

በቃል ኪዳንህ ዐስባት፤

***

ወይም        የክብር መንፈስ በእኛ ላይ ይፍሰስ

በእሳት ቁጥቋጦ ውስጥ ሙሴን ያናገርከው

የመላእክትን ምግብ ለሕዝብህ ያደልከው

ስማን ጨኸታችንን እግዚአብሔር ሆይ ተነሥ፣

በኢትዮጵያ ምድር የድል መንፈስ አፍስስ።

አጋንንቶች ይውጡ ስማቸው ይደምሰስ

ሽባዎች ይነሡ ድውዩም ይፈወስ

ጠላት ሲወድቅ እንይ በሰይፍ ሲወጋ

በምድረ ኢትዮጵያ የክብር እጅህን ዘርጋ

***

ወይም ሲያጠፉት ይነዳል፣ ሲያፍኑት ይብሳል

ገና በኛ ወንጌል ዓለም ይሰወጣል።

***

ወይም ጌታችን ያቀደው ለኛም የገለጸው፣

ይህ ጅማሬው እንጂ አይደለም ፍጻሜው

የወንጌል አዝመራ ነዶው ሚከመረው

አስደናቂው መከር ገና ወደ ፊት ነው።

ወይም ***

ከዚህም የሚበልጥ፣ የጌታ ኀይል ሲገለጥ

እናያለን ገና የክብሩን ደመና

ምድር ስትሞላ በጌታ ምስጋና

ሌሎች ብዙ ዝማሬዎችና ጸሎቶች ዐዋጆችም ተነግረዋል።



"ፈውስን በተስፋ ተጠባበቅን፤ እነሆም ድንጋጤ ሆነ" (ኤር. 14፥19)

ከእግዚአብሔር ጋር የጸጋ ቃል ኪዳን በነበራቸው በሕዝበ እስራኤል መካከል በአስጨናቂ የታሪክ ወቅት የተነሣው ነቢዩ ኤርምያስ የተናገረው ቃል ነው። ከቃል ኪዳኑ የተነሣ ወይም በትንቢት ስም ከመጡት ንግርቶች የተነሣ በሕዝቡ ዘንድ የነበረው የአምንታዊ ቀኖች፣ የብርሃን ወቅቶች ጥበቃ በታላቅ ግራ መጋባት ሲለወጥ የሚያሳይ አሳዛኝ ሥዕል ነው።

መሳፍንቱና ገበሬዎቹ፣ አፍረውና ራሳቸውን ተከናንበው የሚቈዝሙበትና እንስሳቱ ግጦሽ ባለማገኘታቸው ዐይኖቻቸው የፈዘዙበትን አሳዘኝ ትዕይንት ተመልክቶ ኤርምያስ ትካዜውን እንዲህ ሲል ያንጎራጉራል፦

*ይሁዳን ፈጽመህ ጥለኸዋልን?*

*ነፍስህስ ጽዮንን ተጸየፈቻትን?*

*ፈውስ እስከማይገኝለት ድረስ ለምን ከፉኛ መታኸን?*

*ስለ ስምህ ብለህ አትናቀን፤*

*የክብርህንም ዙፋን አታዋርድ፤*

*ከእኛ ጋር የገባኸውን ኪዳን ዐስብ፤ አታፍርሰውም።*

ይህ ትካዜና የእሮሮ፣ የግራ መጋባትና የልመና ዜማ በኢትዮጵያውያን ዘንድ አሁን ያለውን ስሜት የሚያንጸባርቅ ይመስላል። ብዙ ወገኖች "የስማነው ተስፋና አሁን የምናየው እውነታ እጅግ ተራራቁብን?" የሚል ድምፀት ያለው የልብ ማመንታትና የተስፋ መስለምለም ሁኔታ ወስጥ ገብተዋል።

"ትልቅና ንጹሕ መንፈሳዊ መነቃቃት ተጠባበቅን፤ ነገር ግን ከፍተኛ መንፈሳዊ ዝቅጠት ውስጥ ወደቅን፤ ደማቅ ጤነኛና ብርቱ አገራዊ ቤተ ክርስቲያን እንደምትገነባ ተጠባበቅን፣ ነገር ግን ከዚህ ይልቅ በብዙ ቦታ የቤተክርስቲያን አካላዊ ፍርስርስ ይታያል፤ ዓለም አቀፍ ተጽእኖ ማምጣት የሚችል ጠንካራ የፖለቲካ አቋምና ብሔራዊ ሰላም ተጠባበቅን፤ይህን በመጠኑ ብናይም አሁንም ሥጋት አልለቀቀንም። ከእኛ አልፎ ሌሎችን

ለእስራኤል ቤት እንዲህ አለ፡-

*"ብትታዘዙኝና ኪዳኔን ብትጠብቁ እነሆ ከአህዛብ ሁሉ እናንተ የተወደደ ርስቴ ትሆናላችሁ" (ዘፀ. 19፥5)*

ለዳዊት እንዲህ አለው፡-

*"እግዚአብሔር ቤት እንደሚሠራልህ በግልጽ እነግርሃለሁ፤ ዘመንህን ጨርሰህ ወደ አባቶችህ በምትሔድበት ጊዜ፣ ከተከፈለት ልጆችህ አንዱ በእግርህ እንዲተካ አደርጋለሁ ... በቤቱና በመንግሥቴ ላይ ለዘላለም አኖረዋለሁ፤ ዙፋኑም ለዘላለም ይጸናል።" (1ዜና. 17፥10)*

በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ "ተስፋችን" ተብሎ ተጠርቷል (1ጢሞ. 1፥1)፤ "የክብር ተስፋ የሆነው በእናንተ ወስጥ ያለው ክርስቶስ ነው" ተብሎም ተጽፏል (ቆላ. 1፥27)፤ አዲስ ኪዳናዊው ተስፋ የመዳን ተስፋ ነው። በእምነትና በመንፈስ ቅዱስ በልባችን የሚያድር ነው። ጳውሎስ እንዲህ አለ፡- *"በእርሱ በመታመናችሁ የተስፋ አምላክ ደስታንና ሰላምን ይሙላባችሁ፤ ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ተስፋ ተትረፍርፎ እንዲፈስላችሁ ነው።" (ሮሜ 15፥13)።* ድነታችን ራሱ አሁን የተጨበጠና ገና በተስፋ ያለ ነገር ነው።

"በተስፋ ድነናልና" እንደ ተባለ የምንሰብከውም የምሥራች "የወንጌል ተስፋ" ነው (ቆላ. 1፥23)። "*ሥጋዬ* በተስፋ ይኖራል" ብሎ ንጉሥ ዳዊት የተነበየው በአዲስ ኪዳን ዘመንም የሚዘልቅ የእለኝታ መዝሙር ነው (ሐዋ. 2፥26)።

የተስፋ ሙላትና የተስፋ ጭንገፋ (ዝግጅት)

እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ ከእርሱ ሁሉን ቻይነት የተነሣ፣ ከፍጹም ታማኝነቱም የተነሣ ሁልጊዜ ተፈጻሚ ነው። ይሁን እንጂ የኪዳን አስተሳሰብ እንደሚያመለክተን በኪዳን ተቀባዩ እንደኛው ወገን ያነከሰ ነገር ሲገኝ ተስፋው እንደሚጨናገፍ፣ ወይም ቢያንስ ቢያንስ የተስፋው ሙላት እንደሚዘገይ፣ እንደሚንገታገት መረዳት ይቻላል። ሕዝብ እስራኤል ወደ ከነዓን (ከነስሟ የተስፋይቱ ምድር) እንዲገቡ የተሰጣቸው ተስፋ በፍጥነትና በተድላ ያልሆነው ከእግዚአብሔር ዐሳብ ወላዋይነት ወይም ማመንታት ወይም ዐቅም ማነስ እንዳልሆነ አስረግጠን



እናውቃለን። ተስፋውን ለመጨበጥ በእነርሱ በኩል ከነበረው ቁርጠኛ ታማኝነት ማጣት፣ የልብ ዳተኝነት፣ ወላዋይ ፍላጎትና፣ መንፈስ ድንዳናነት መሆኑንም ለመገንዘብ በቂ ምስክር ከታሪካቸው እናገኛለን።

*"በዚያ ትውልድ የተቆጣሁት ለዚህ ነበር፤*

*እንዲህም አልሁ፡- ልባቸው ሁልጊዜ ይስታል፤*

*መንገዴንም አላወቁም፤*

*ስለዚህ በቁጣዬ እንዲህ ብዬ ማልሁ*

*ወደ እረፍቴ ከቶ አይገቡም።" (ዕብ. 3፥10-11)*

ባልታዘዙትና ባላመኑት ላይ የከነዓንን በሮች ቢዘጋም እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባውን ተስፋ ፈጽሞታል። በግለ ሰቦች ሕይወትም ይኸው የተስፋ ጭንገፋ ሲከናወን መመልከት ይቻላል። በፊሪሓ እግዚአብሔርና በጥንቃቂ በመኖር ሲጨበጡ የሚችሉ ተስፋዎችን በምን ግዴ ኑሮ ለሚሔዱ እግዚአብሔር ሲነፍግ ማስተዋል ይቻላል። ለካህኑ ዔሊ የተነገረው እንዲህ ተብሎ ነው፡- *"ቤትህና የአባትህ ቤት ለዘላለም ያገለግሉኝ ዘንድ ተስፋ ሰጥቼ ነበር፤ አሁን ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ - ይህን ከእንግዲህ አላደርገውም፤ የሚያከብሩኝን አከብራለሁ፤ የሚንቁኝም ፈጽሞ ይናቃሉ።" (1 ሳሙ. 2፥30)።*

ተስፋ ይዞ መሞት፣ ተስፋ ይዞ መኖር

ሁለቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክስተቶች ናቸው። አንዳንዶች የተሰጣቸውን ተስፋ በዐይናቸው እንደሚያዩት አጥበቀው እየተረዱ እየጠበቁ ቆይተው ተቀበሉት። ለምሳሌ፣ ሽማግሌው ስምዖን እና መበለቲቱም ሐና። *"ጌታ ሆይ በገባኸው ቃል መሠረት አሁን ባሪያህን በሰላም አሰናብተው፤ ዐይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን ዐይተዋልና።" (ሉቃ. 2፥29)።*

አንዳንዶች *"... የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል ሳያገኙ እምነታቸውን እንደ ጠበቁ ሞቱ፤ ሆኖም ከሩቅ ዐይተው ሰላም አሉት።" (ዕብ. 11፥13)።* ምንም እንኳ እነዚህ በሁለት ምድብ የሚታዩ ሰዎች የተለያዩ ቢመስሉም የሚያገናኛቸው ዋና የሕይወት ዘይቤ አለ፤ ይኸውም ኑሮአቸው የተስፋ ጥበቃ መሆኑ ነው። የተስፋ

ማረፊያው ከቦታው የማይነቃነቅ ልዑል አምላክ በመሆኑ የተስፋ ቃሉ ሙላት አሁን ቢደረስበት ወይም ዘግይቶ ቢመጣ ለውጡ የዘመን ርቀት ብቻ ይሆናል። ሁለቱም ዐይነት ሰዎች ባለ ተስፋዎች ናቸው። እንግዲያው ተስፋዊነት አንድ የኑሮ መልክ ነው ማለት ነው።

### የተባረከው ተስፋችን

ስለ ብሔራዊ ተስፋም ሆነ ስለ ግለ ሰባዊ ተስፋ የተባለውን ሁሉ ካልን በኋላ ከሁሉ የላቀና የጸናውን የክርስቲያኖች ተስፋን ማንሣት ተገቢና አስፈላጊ ነው። በዚህ ታላቅ ተስፋ ፊት ሌሎች ተስፋዎች ሁሉ ንዑሳንና ደቂቅ ይሆናሉ። በዚህ ክቡርና ደማቅ ተስፋ አንጻር የሌሎች ተስፋዎች ብርቅርቅታ ሁሉ ይደበዝዛል። የታላቁ የአምላካችንና የአዳኛችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መገለጥ ብሩኩ ተስፋችን ነው። እኛ ብቻ ሳንሆን ፍጥረት ሁሉ በምጥ ሆኖ የሚጠብቀው ቀን ያንን ቀን ነው። ያ ቀን የቤዛ ቀን ነው፤ ሟች በስባሽ ሥጋ ወደ ክቡር አካልነት ይለወጣል፤ የሰማይ ግርማ ይለብሳል። እኛ ክርስቲያኖች አማኞች ብቻ ሳንሆን ተስፋ ጠባቂዎችም ነን። ጥቢቃ የኑሮ ዘይቤያችን ነው። በአገራዊ ተስፋ ርእሰ ጉዳይ ላይ በየትኛውም ጎራ ብንቆም ከዚህኛው የተስፋ ጥበቃችን ለአፍታ እንኳ ልንዘናጋ አይገባም። ይህን ተስፋ መጠበቅ ብቻም ሳይሆን ልናውጀው ተጠርተናል ‹‹ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ›› ብሎ ስብከቱን የጀመረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የወንጌሉ ቃል በፍጻሜ ዘመን አስተሳሰብ ዐውድ ውስጥ ሊነገር እንደሚገባው ሲያሳየን ነው። ስለ ጌታ ራት በሰጠው መግለጫ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ 11፤26 ‹‹ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁ ››ማለቱ ከሞቱና ከትንሳኤው ቀጥሎ ያለው ታላቅ ክስተት መገለጡና መንገሡ ስለሆነ የጌታ ምዕአት ዋና የትኩረት ግባችን መሆኑን ያሳያል ። ለቤተክርስቲያንም ለዓለምም ልናውጀው የሚገባን ብርቱ ተስፋ ‹‹ኢየሱስ ይመጣል ›› የሚለው ነው ።

### ወደ ጤናማ ተስፋዊነት ጉዞ

ስለ አገራችን፣ ስለ ሕዝባችን፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ የተሰጡትን ተስፋዎች፣ የተነገሩትን ትንቢቶች በየልባችን ውስጥ የሚገኙትን ጥበቃዎችና ናፍቆቶች ምን እናድርጋቸው? እንዴት እናስተናግዳቸው? በምን መልክ እንያዛቸው? እንዴት እንያቸው? የሚሉትን ተግባራውያን ጥያቄዎች ማንሣት የአሁኑ ጉዳያችን



ነው። ከሩት ለፊታችን የሚደቀኑ አማራጭ መልሶች አሉ። "የሰማናቸውን የተስፋ ዐዋጆች አጥብቀን ይዘን፣ ሳልሰሙትም እያደረስን፣ ፍጻሜያቸውን እንከታተል" የሚል አንድ መንገድ አለ።

"በትንቢት ቃል የተነገረውን ሁሉ ማመን ስለማይጠበቅብን የዚህን የኋላ ዘመን ተስፋ ነገር ቀዝቀዝ አድርገን ብንይዘውና እንደማንኛውም ሕዝብ 'ኖርማል' ኑሮአችንንና የዕለት ትግላችንን ብንቀጥል ልባም አካሄድ ይሆንልናል" ማለት ደግሞ ሌላው የአስተያየት ዐይነት ነው።

"ታላቅ ተስፋ ቢነገረንም እዚያ ለመድረስ እንቅፋቱ ብዙ ስለሆነ ከፊታችን ያለውን የመከራና የቅጣት ዘመን እንዴት በፈሪሐ እግዚአብሔር እንደምናመልጠው መነጋገር የበለጠ ዋጋ አለው" የሚልም አመለካከት ይኖራል።

ሌላም ጥያቄአዊ መልስ አለ፦ "ለመሆኑ ኢትዮጵያ አዲሲቱ ጽዮን ናትን? የእስራኤል የራሷ የፍጻሜ ዘመን ተስፋ አከራካሪ በሆነበት ሁኔታ እንዴት ኢትዮጵያን ከሌሎች አገሮች በተለየ ሁኔታ ልንመለከትና የዓለም ሁሉ ማዕከል እንደ ሆነች ዐይነት ልንነጋገር እንችላለን?" የሚል።

በእነዚህ ልዩ ልዩ የአስተሳሰብ ስርጭቶች መካከል ሆነን ሳለ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢዎች ለወደፊት ዕይታችን ይጠቅሙናል ብለን የምናስባቸውን ጥቂት መንደርደሪያዎች እናዋጣ።

- እግዚአብሔር ሕያው አምላክና ለፍጥረቱም ዐሳቢ በመሆኑ ስለ ሕዝብ፣ ስለ አገር ስለ ቡድኖች ስለ ግለ ሰቦችም መናገሩ መጽሐፍ ቅዱሳዊው ታሪክ የሚያረጋግጠው ነገር ነው። ከዚህ የተነሣ ስለ አገራችንም ስለ ቤተ ክርስቲያንም የአሁንና የወደፊት ሁኔታ የተነገረውን ፍርድና ተስፋ ማዳመጥ ተገቢ ነው።

- በስመ እግዚአብሐ?ር በመነገሩ ብቻ ራእይም ሆነ ትንቢት መንፈሳዊ ይዘት እንዳለው መቁጠር የማያዋጣ አካሔድ እንደ ሆነ አሁንም ያው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክና ምክር ያስገነዝበናል። የእውነት ነቢያት እንደ ነበሩ ሁሉ የሐሰት ነቢያትም ነበሩ። የኤርምያስ መጽሐፍ ይህን መንታ ገጽታ በግልጽ ያስተነትናል። ስለዚህ በአሁኑ

የኢትዮጵያ ሁኔታ ርግጡን ተስፋ ከምኞት ዜማ መለየት ዋና ጥሪያችን ሊሆን ይገባል። ስለ ፍርድና ተስፋ ተደጋግሞ በሚነገርበት ዐውድ ውስጥ ተመሳሳይ ምት ያሳሳበው ባዕድ ጭፈራ ገብቶ ቢሆንስ ብሎ መጠየቅ ጥንቁቅ አካሔድ ነው። ማንኛውም በትንቢት ቃል የተነገረን መልእክት በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፉት ቃላት እኩል ደረጃ እንድንሰጠው አዲስ ኪዳን አይፈቅድልንም። ስለዚህ ነው "ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ያዙ" የተባለው።

- ስለ አገራችን ኢትዮጵያና ስለ ሕዝባችን የተሰጡት ተስፋዎች ለእኛ ለኢትዮጵያውያን አሳሳቢና አንገብጋቢ ጉዳዮች ቢሆኑም፣ እውነተኛዎች ናቸውም ብንልም ከዋናውና ከታላቁ ተስፋ አንጻር ታይተው ልከኛ ደረጃ ሊሰጣቸው ይገባል። ስንኖርም ስንናገርም ልሁሉ እንዳቅሙ ማጨብጨብ የማስተዋል ሥራ ነው። አገራችንን ኢትዮጵያን ልንወዳት ልናስብላት ለልማቷ ለብልጽግናዋ ለሰላሟም ተግተን ልንሠራ ይገባል። ይህን ስናደረግ ግን ሰማያዊውን አገራችንን እያሰብንና እየናፈቅን ሊሆን ያሻል።ሁለቱን አስተሳሰቦች ማቃረንም አያስፈልግም።

- የተስፋ ጥበቃ ቦዘን ተቀምጠው፣ ዐይን አፍጥጠው የሚያከናውኑት ተግባር ሳይሆን፣ በውስጡ ብርቱ ተሳታፊ በመሆን የሚቀበሉት ነገር ነው። "የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽማችሁ የተስፋ ቃሉን እንድትቀበሉ፣ ጸንታችሁ መቆም ያስፈልጋችኋል።"የሚል ምክር የምናውቅ እኛ የጌታን መገለጥ የምንጠብቅ ሰዎች የጥበቃ ዘመን የኑሮ ስልታችን ፈቃደ እግዚአብሔር ምንድነው? እንዴትስ ልንፈጽመው እንችላለን? እያሉ መጠያየቅ በጎ እያደረጉ ወደ ተስፋው ሙላት መገሥገስ ሊሆን ያስፈልገዋል።

- ከታላላቅ ተስፋዎች ጋር ተያይዞ የተነገረውን የፍርድ ማስጠንቀቂያ እንደሌለ መቁጠር አንድም ስለ እግዚአብሔር ዐሳብና ፍላጎት ደንታቢስነት ሲያሳይ፣ እርሱ ሥልጣንና መለኪያ ያለው ጌታ መሆኑን ከመቀበል ይልቅ ለእኛ ፍላጎት መሟላት የምንሰማመጠው ከበርቱ ያስመስለዋል። ምናልባትም በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነገር በክፉ ሥራ ላይ የጽድቅ ፍርድን



የሚያሳርፈውን ጌታ ምሕረት መለመን ነው። ከዚህም የተነሣ ያለንበት ዘመን የጌታን ፊት በቅንነት ለመፈለግና ወደ እርሱ በትሕትና ለመመለስ የምንቈርጥበት ጊዜ ሊሆን ያስፈልጋል።

- ሕይወት ከእግዚአብሔር በመጣ ተስፋ ስትቃኝ ትለመልማለች፣ ትፈካለች፤ አግጣጫ ይዛ ወደ ፍሬአማ ግብ ትገሰግሳለች። ስለዚህ ለጊዜው በሚታየው የተጓሳቢጦሽ ነባራዊ ሁኔታ ምክንያት እግዚአብሔር እንደሰጠን ያረጋገጥነውን ተስፋና በልባችን ያደረውን ሰማያዊ ትምክህት መጣል አይገባም።

እግዚአብሔር በራሱ ጊዜና በራሱ አሠራር የሚፈጽማቸውን ነገሮች ለእርሱ ጥበብና ችሎታ አሳልፈን እየሰጠን በእምነትና በጥንቃቄ እንድንኖር መንፈስ ቅዱስ ልባችንን ወደ እውነትና ወደ ቅዱስ ኑሮ ያዘንብልልን።

# ካሪዝማዊ ቅርስ

*(የካሪዝማዊው እንቅስቃሴ ዕጣ ፈንታ እና ለቀጣዩ ትውልድ የምናወርሰው ቅርስ)*

ርእሱ ሁለት ቅርንጫፎች አሉት። አንደኛው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እንቅስቃሴን የወደ ፊት ዕድል የሚመለከት ሲሆን፣ ሁለተኛው ለመጪው ትውልድ የምናስተላልፈውን ቅርስ የሚመለከት ነው። 'ሁሉቱን ምን ያገናኛቸዋል?' የተባለ እንደ ሆነ "ነገ" የሚለው ዐሳብ ነው። ነገ ምን ይሁን? የነገዎቹ ምን ይሁኑ? ለነገ ምን እናድርግ?

"ሞኝ የዕለቱን ብልኅ ያሙቱን" መባሉ አርቆ ማየት፣ አገናዝቦ መራመድ ዋጋ ያለው ርምጃ መሆኑን ለመግለጽ ነው። እኛ የዛሬ ሰዎች ብቻ አይደለንም፤ የትናንት ዘር ፍሬ ነን፤ የነገንም ፅንስ ይዘን የምንጓዝ ነን። የማይነካካ ምንም ነገር የለም። ስለዚህ መለስ ቀለስ እያልን፣ አሻግረንም እያየን የሕይወትን ርምጃ እንሔዳለን። 'የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች (ካሪዝማዊ) እንቅስቃሴ ዕጣ ፈንታ ብሩኅ ነው? ጨለማ?' የሚለው ጥያቄ በከፊል ሊመለስ የሚችለው 'መነሻው ሰማያዊ ነው? ምድራዊ?' ከሚለው ጥያቄ መልስ ጋር ተያይዞ ነው።

ጸጋ ስጦታዊው (በግሪክ ልሳን ካሪዝማዊው) እንቅስቃሴ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ነው አይደለም?የሚል ሙግት ባለበት ዓለማቀፋዊ ዐውድ ውስጥ ሆነው የሚናገሩት ታዋቂው የነገር



መለኮት ምሑር ጄ.አይ ፓከር ለመልሳቸው መደላድል ለመስጠት ሁለት መመዘኛዎች ያስቀምጣሉ፤ የእምነት መግለጫዊና ሞራላዊ (creedal and moral)። ሁሉቱንም በአብዛኛው ከዮሐንስ መልእክት ውስጥ ከሚገኙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች አንጻር ያይዋቸዋል። "ኢየሱስ በሥጋ እንደ መጣ የሚክድ መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም" የሚለውና እግዚአብሔርን እወዳለሁ የሚል ትእዛዙን የሚያከብርና ወንድሞችን የሚወድ መሆን እንዳለበት የሚናገረውን ጥቅስ (1ዮሐ 4:3 እና 4:25)መሠረት አድርገው እንዲህ ይላሉ፦

> *እነዚህን መመዘኛዎች ተጠቅመን ካሪዝማዊውን እንቅስቃሴ ስንፈትሸው እግዚአብሔር በውስጡ እንዳለበት ግልጽ ሆኖ ይታያል። በእንቅስቃሴው ጠርዝ ዙሪያ የሚርት ወይም የአሳሳች መንፈሳዊነት ገጽታዎች ይታያሉ ብለን ብናስብ እንኳ (ለዚያውስ የትኛው ሪቫይቫል ነው እነዚህ ችግሮች ሳይነኩት ያለፈ?)፣ በየቦታው ያመጣው ዋና ውጤት ጠንካራ ሥላሴያዊ እምነት በአዲስ ኪዳን ከምናገኘው መለኮታዊ አዳኝና ጌታ ጋር ግላዊ ኅብረት፣ ንስሓ፣ ታዛዥነትና ለክርስቲያን ወንድሞች በልዩ ልዩ አገልግሎት የሚገለጽ ፍቅር እንዲሁም ያለ ምንም ትጋት የተቀመጠውን ቤተ ክርስቲያን ሒያጅ የሚሸነቁጥ የወንጌል ስርጭት ቅናት ሆኖ እናገኛለን።*

በሃያኛውና በሃያአንድኛው ክፍለ ዘመን በታላቅ ፍጥነት ተሰራጭቶ በየክፍለ ዓለማቱ ላሉ አብያተክርስቲያን ትልቅ መነቃቃት የሰጠው ይህ ጸጋ ስጦታዊ እንቅስቃሴ የመለኮት እሳት መሆኑን የሚያሳዩ በበጎ ፍሬ የተሞሉ ብዙ ምልክቶች ቢኖሩም፣ በእኛ ዘንድና በኛ ሁኔታ ያለንበትን አካሄድ እየቃኘን፣ ብሔራዊ ኀላፊነታችንንም እያጠለልን መነጋገር ዋጋ እንዳለው መርሳት የለብንም። ምክንያቱም ዮሐንስ ቡንያን እንዳለው "ከመንግሥተ ሰማይ በር አጠገብም እንኳ ወደ ገሓነም የሚወስድ መንገድ አለ"፤ ስለዚህ "የካሪዝማዊው ቅስቃሴ ዕጣ ፈንታ ምን ይሆናል?" የሚለውን ጥያቄ በቀጥታ ከመመለስ ይልቅ እኛን የሚጠቅመን የነገውን ሁኔታ ዛሬ እንዴት ባለ መንገድ እንቀይሰው? እንቅስቃሴው እንደ ጎርፍ ነውና ጎርፉ ከየሰፈሩ ይዞት የመጣውን ጉዳጉድ ገፈት እንዴት ገሸሽ እናድርግ? ውሃውን እንዴት እንጠቀምበት? የሚለው ይመስለኛል። እዚህ ላይ "ገፈት"፣ "አሰር"፣ "ቆሻሻ" ስል

መንፈስ ቅዱስ የጎደፈና የሚጣል ነገር ያመጣል ማለቴ እንዳልሆነ ግልጽ ነው ብዬ ዐስባለሁ፤ ነገር ግን በበራችን የሚያልፈው ጎርፍ ከየግቢው በሚጣል ቆሻሻ ሊያድፍ ይችላል ለማለት ያኽል ነው። ለመጪው ትውልድ መተላለፍ ያለበት ቅርስ ንጹሑ ውሃ ነው። ይህ ውሃ ምን መልክ አለው? መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ በዚያውም የተቃኘ ልምምዳዊ ዕይታ ይዘን መዝለቅ አለብን።

## ቀቢጸ ተስፋ እና ተስፋ

መጪው ዘመን፣ የጸጋ ስጦታዎች እንቅስቃሴ፣ አዲሱ ትውልድና የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ተስፋ አላቸው ወይ? ዙሪያ ገባችንን ስናይ ወደ ተስፋ እጦት የሚያንደረድሩ ብዙ ቁልቁለቶች ይታዩናል። በየቤተ ክርስቲያናችን ብዙ ጊዜ የምናየው ውል ያጣ የሚመስለው የአምልኮ ጉራማይሌ፣ በእውነት በሥራ ላይ ውሎ ከሚታየው የመንፈሳዊ ኀይል መገለጥ ይልቅ ባንዲራው እጅጉን የሚውለበለብለት የድንቅና ታምራት ድምቀት፣ የሕይወት ንጽሕናና ብርታት የራበው፣ በጩኸትና በግርግር የደከመ ክርስቲያን ማኅበረ ሰብ፣ በሕዝብ መካከል በይፋ ለመሰብሰብና ለመሥራት በተሰጠ ፍቃድ ፊት ሕዝብን ለበጎ የመለወጥ ጉልበት የጠፋበት ሁኔታ ሁሉ ተደራርቦ ሲታይ እግራችን ወደ ብዙ ዐቅም ስላቢ ረግረግ እየሰጠመ የሚሔድ ይመስላል። እናም ተስፋው የሰለለ የሩቅ ድምፅ ይሆናል።

ነገር ግን የቤተ ክርስቲያንና የመጪው ትውልድ ባለቤቶች እኛ አይደለንም፤ ልዑል እግዚአብሔር ነው። ይህን ሁሉ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ እያለፈ፣ አሁንም ሰዎችን እየማረከ ያለው የክርስቶስ ወንጌል ብዙ አሳሳች (counterfeit) ልምምዶች ባሉበት ጫጫታ ውስጥ ኩልል ብሎ የሚወጣው የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለእውነተኛው የኀይልና የጥበብ መገለጥ በየሰዉ ልብ ውስጥ የተቀመጠው ከፍተኛ ራብና ጥማት ትልልቅ ተስፋ ፈንጣቂ ምልክቶች ናቸው።

የመጪው ዘመንና የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ተስፋው ያው ራሱ ሕያዉ መንፈስ ነው። *‹‹ከዚህም በኋላ መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ፤ ሽማግሌዎቻችሁ ሕልም ያልማሉ፤ ጎልማሶቻችሁም ራእይ ያያሉ።››* (ኢዮኤል 3:1)።

በበዓለ ኀምሣ ቀን ሐዋርያው ጴጥሮስ ይህን ትንቢት ጠቅሶ ተናገረና ልባቸው በጥልቅ ለተነካ አድማጮቹ እንዲህ የሚል ቃል ጨመረላቸው፡- *‹‹የተስፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ እንዲሁም ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉትም ሁሉ ነውና››* (ሐዋ 2:39)። ስለዚህ እውነታን ሳንደብቅ ተስፋ ሰባኪዎች መሆን የጊዜው ጥሪያችን ነው።

## "ስባት ዕንቁዎች"

ይህን የእውነታና የተስፋ ጥምር ድምፅ ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የሚያግዘን አንድ አካሔድ በጠቅላላው የመንፈስ ቅዱስ ኑሮአችን ውስጥ ያገኘናቸው፣ እንዲሆኑልን የምንሻቸውና በሥሥት ዐይን የምናያቸውን ዕንቁዎች ተራ በተራ መቁጠር፣ መወልወል፣ ማጉላትና ማሳየት ነው። እነዚህ ሁልጊዜ ሊኖሩ የሚያስፈልጉ፣ ሳይቋረጡ መሸጋገር የሚገባቸው ዕንቁዎች ምንድናቸው? ሌላ ደርዳሪ ቢመጣ ቁጥራቸውን፣ አቀማመጣቸውንና ስሞቻቸውን ሊቀያይር ቢችልም ለእኔ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችና ከመንፈሳዊም እንቅስቃሴ አንጻር የሚታዩኝ አንኳር ቅርሶች እነዚህ ናቸው፡-

- ሕያው አምልኮ
- ቅዱስ ሕይወት
- የቃሉ ፍቅር
- የክርስቶስ ማዕከላዊነት
- ወንድማዊ ፍቅር
- መልእክተኛነት
- ብርቱ የጌታ መመለስ ጥበቃ

## ሕያው አምልኮ

ባለፉት አርባ ዓመታት በአገራችን የታየው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ አንድ ብሩኅ ገጽታ፣ የማኅበር አምልኮን የደንብና የልማድ ወህኒ ከማድረግ ይልቅ ያምላክና የሰው ሕያው ግንኙነት ማድረጉ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው ስግደት (አምልኮ) የቦታ፣ የታሪክና የባሕል ጥያቄ መሆኑ ቀርቶ የመንፈስ

ነገር ነው። በመንፈስ እና በእውነት በሚደረግ አምልኮ ውስጥ ሰላማዊ ነጻነትና ውብ ሥርዐት ይሰፍናሉ። ሰዎች ከንቱ ድጋም ሳይሆን ትኩስ ተራክቦ ከአምላክ ጋር ያደርጋሉ። ይህ በታላቅ ጥንቃቄና ጉጉት መያዝ ያለበት ቅርስ ነው። ጥንቃቄ የጎደለው ቀን ነጻነቱ ፈዋሽ መሆኑ ይቀርና ዕብደት ይሆናል፤ ሥርዐቱ ውበት መሆኑ ይቀርና ወህኒ ይሆናል፤ ስጦታዎቹ ማከሚያ መፍትሔ መሆናቸው ይቀርና መደባደቢያ በትሮች ይሆናሉ።

ወደ ሰማይ ለሚያርግ አምልኮ እርሱ ራሱ መንፈስ ቅዱስ እንዲቀሰቅሰን ራሳችንን በተጠማ ልብ፣ በትሕትና እና በጉጉት እያዘጋጀን መጠበቅ ዋና ጥሪያችን ነው። የማኅበር አምልኮአችን ቲያትራዊነት እንዳያጠቃው መንፈሳችንን እየመዘንን ነቅተን መጠበቅ አለብን። በጋራ በምናደርጋቸው ጉባኤዎች እውነተኛነትና የልብ ንጽሕና እስከተጠበቀ ድረስ የአምልኮ አገላለጽ ልዩነቶቻችንን በገር ልብና በአስተዋይ አእምሮ ሚዛን ይዘን መጓዝ አለብን። ‹‹ሕዝቤ በዓል ያደርግልኝ ዘንድ ልቀቀው›› ተብሎ እንደተጻፈው ለታላቁ ጌታ በአንድነት የምናቀርበው ውዳሴና ስግደት በማንኛውም የጠላት ሤራ መተጓጎል የለበትም። ወደ ኋላ በሚጎትት የሕግ አክራሪነትም ሆነ በአፍጢም በሚደፋ ሥርዐት አልባ ግርግር እንዳይደናቀፍ ብርቱ ጥንቃቄ ያሻዋል።

## ቅዱስ ሕይወት

መንፈስ ቅዱስ ከነ ስሙ ቅዱስ ነው። በየትም ቦታ የሚነሣ ካሪዝማዊ ቅስቃሴ እውነተኛነት አንዱ ማጥለያ፣ የተንቀሳቀሰው ሰው ሕይወት በፈሪሓ እግዚአብሔር እና በፍቅረ እግዚአብሔር እንዲሁም በኀጢአት ጠልነት የተሞላ የመሆን የአለመሆን ጉዳይ ነው። መንፈሱ ኀይል ሰጪያችን ብቻ ሳይሆን ቀዳሻችንም ነው። ኀይሉም ተራራ የመፈንገል ብቻ ሳይሆን፣ የኀጢአትን ሥር የመንቀልም ነው። መጪው ትውልድ ጦሩን ሰብቆ ጋሻውን አንግቦ መጠበቅና መዋጋት ያለበት እያደባ፣ እያሟለጨ ወደ ቅዱሳን ማኅበር የሚገባ የቅድስናን ሰላቢ ነው። ይህ እንግዲህ መሥዋዕታዊ ኑሮ ይጠይቃል፤ ጥሪያችንም ‹‹መስቀሉን ተሸከሙ›› የሚል ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃም ይሁን በኛው አገር የሕይወት ንጽሕና መዳከም ብርቱ የነበሩ የጸጋ ሰዎችን ጉልበት ገዝግዞ እንደጣለብን እናውቃለን። ስንት ጠንካራ እንቅስቃሴዎች ተሰለመለሙ?! ስንት የመንፈስ ጀግና ዐቅም ሟሸሸ?! ታላቅ መንፈስ በውስጡ



ያደረበት ሶምሶን በእንዝህላል አካሄዱ ለራሱም ለሕዝቡም ውርደት ምክንያት ሆነ። እግዚአብሔር የውርደት ዘመኖቻችንን በመንፈሱ ብርታት፣ በጽድቅም ጉልበት እንድንበቀላቸው ይርዳን። የበቀሉም የመትረፊያውም መንገድ ውስብስብ አይደለም። የፈሪሓ እግዚአብሔርና የፍቅረ እግዚአብሔር ጎዳና ነው። አባትነቱን ስንወደው፣ ስንረካበትም ለቀልውጥ አንወጣም፤ ዳኝነቱን ስንፈራው ስናውቀውም በአጉል ድፍረት አንሮጥም።

*“ለሰው ሳያደላ በእያንዳንዱ ላይ እንደ ሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ የምትጠሩት ከሆነ፣ በዚህ ምድር በእንግድነት ስትኖሩ በፍርሀት ኑሩ።” (1ኛ ጴጥ 1:1-17)*

## የቃሉ ፍቅር

ጤነኛ መንፈሳዊ እቅንስቃሴ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተጻፈውን ቃል ይወዳል፤ ያከብራል፤ ይታዘዛል፤ ያስፋፋል። ለአዲስ ትውልድ የምናስተላልፈው ታላቅ ጥሪት ማንንም የማይፈራ፣ ግንባሩን የማያጥፍ የእውነት ፊታውራሪ የሆነውን ቃለ እግዚአብሔርን ነው። እርሱን የመስማት፣ የማንበብ፣ በቡድን የመወያየት፣ የመስበክ፣ ለክርክሮች ብያኔ ሰጪ የማድረግና በየአገልግሎቱ ሁሉ ዋና መነሻ የማድረግ ባሕል ገላችን ሲሆን ይገባል። እውነት አዋቂነት ብቻ ሳይሆን ለእውነት ተገዢነት እጅግ መበረታታት ያስፈልገዋል። የመንፈስ አርበኞች ነን ብለን ብንፎክርም መንፈሱ በጦሩ ሜዳ አፈፍ የሚያደርገው ሰይፍ እኮ ቃሉ ነው። በእጃችን ከርሱ የቀለጠፈ ምንም መሣሪያ የለም። ይህ ሰይፍ ሁላችን ልንታጠቀው የሚገባ ሰይፍ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ጥቂት ሞያተኞች በምስባኩ ላይ የሚያቀርቡት የክት ድግስ ሳይሆን፣ እያንዳንዱ ሰው በቤቱ ገበታ ሊመግበው የሚገባ የወትሮ ቀለብ ነው። የሚጠቅመን የጋራም የግልም መብል ሲሆን ነው።

## የክርስቶስ ማዕከላዊነት

ካሪዝማዊው እንቅስቃሴ በመሠረቱ የክርስቶስ ወዳጅ ነው። ያረፈብን መንፈስ መንፈስ ቅዱስ ሲሆን፣ አድምቆና አጥልቆ የሚያሳየው የእግዚአብሔር ዕቅድ ሁሉ መጠቅለያ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። ‹‹እርሱ ያከብረኛል›› ብሎ ጌታችን የተናገረለት መንፈስ ለሰው ጉልበትና ዝና ማድመቂያ ወይም ለቡድን መጠሪያ ጌጥ እናድርግህ ስንለው ትዕቢታችንን ይጠየፋል፤ ሽረር ብሎም ይሔዳል።የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ እንዲዘልቅና

ማኅበረሰብን እንዲለውጥ ከተፈለገ የክርስቶስን ንግሥና ከሚሻሙ ነገሮች መጠንቀቅ አለብን።እኛ ራሳችን በክበሬታ ወንበር ፤ የእኛ ቤ/ክ ወይም ድርጅቶች ዙፋኑ ላይ እንዳይቀመጡ አጥብቀን መከላከል አለብን።ሲሠዉላቸው ሲመጡ ልብሳቸው እንደቀደዱት ሐዋርያት ማለት ነው። ክብራችን የጌታ የኢየሱስ ስም መድመቁ ነው። መንፈሱ ክርስቶስን ማዕከላዊ ያደርጋል ስንል፣ የጌታችንን አንድ ገጽታ ብቻ ሳይሆን የማንነቱን ሙላት ማለትም ጌትነቱን፣ አዳኝነቱን፣ ፈዋሽነቱን፣ መምህርነቱን፣ ወዳጅነቱን፣ ፈራጅነቱን ወዘተረፈ ያካተተ ምሉእ ክርስቶስ ያሳውቀናል ማለታችን ነው። እኛ ዘንድ ያለው እንቅስቃሴ ይህ ምልዐት የሚታይበት መሆኑን ማረጋገጥ ትልቅ ኀላፊነታችን ነው።

## ወንድማዊ ፍቅር

ሐዋርያው ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን "ፍቅር አፍሳሽ" መንፈስእንደ ሆነ ይነግረናል (ሮሜ5፡5)። እግዚአብሔርንም ሰውንም ለመውደድ በልባችን ላይ የፍቅር መንደልደያ አሸንዳውን የሚዘረጋውና የሚሞላው መንፈስ ቅዱስ ነው። ፍቅር የወዲያው ብልጭታ ብቻ ሳይሆን፣ የኀመራ የመንፈስ ፍሬ ነው። የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ አለ እያልን የፍቅር ድኽነት ከወረሰን ግን አጠያያቂ ቦታ ላይ ቆመናል።እውነተኛ ነገረ መለኮት የእግዚአብሔር ፍቅር በጥልቅ የመረዳት ዐቅም ሊሰጠን ይገባል። በሪቫይቫል ርእሰ ጉዳይ ላይ በጻፉት ምዕራፍ ዴቪድ ስሚዝ ሁላችንን የሚያሳስብ ነገር ይናገራሉ።

> *አንድ የሪቫይቫል ቅስቃሴ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለሚስፋፋው የእግዚአብሔር መንግሥት ሁነኛ አስተዋጽኦ ስለማድረጉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለኪያው ምንድነው ቢባል ሪቻርድ ላቭሌስ የሚያስጠነቅቀን ይህንን ነው፦ "የሪቫይቫል ንጽሕና ከነገረ መለኮት ይዞታው ጋር እጅጉን ተይይዟል። ያለ ሥል የእውነት ቢላዋ ጥልቅ ቀዶ ጥገና ሊደረግ አይችልም"*
>
> *የዚህን አባባል እውነትነት የሚጠራጠር ማንም ቢኖር አፍ የሚያስይዘውን የሩዋንዳውን ጭፍጨፋ ልብ ብሎ ማጤን አለበት። በሁሉም አብያተ እምነት ያሉ ክርስቲያኖች ሲጠይቁ የቆዩት ጥያቄ፣ "ወንጌል በደንብ ተዳርሷል፤ ያልተቋረጠ ሪቫይቫል ይካሔድበታል ተብሎ በሚታሰበው የአፍሪቃ ክፍል እንዴት ይህን የመሰለ ለኀሊና የሚሰቀጥጥ ጭካኔና አረመኔነት ተከሰተ"? የሚል ነው። አንድ ጭንቅ የያዛቸው የካቶሊክ ጳጳስ ሲናገሩ "በጣም ጥሩ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተምረዋል ያልናቸው መጀመሪያ የመግደያውን መጥረቢያ ይዘው ከወጡት መካከል ናቸው" ብለዋል። ለወንጌላውያኑ ደግሞ ጥያቄው ይብሱን አስጨናቂ ይሆናል። አንድ ሚሲዮናዊ እንዳሉት "የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ቁጥር ዕድገት እጅግ ከፍ ቢልም ጥንፍፍ ያለ መሥዋዕታዊ ደቀ መዝሙርነት በመጥፋቱ ቤተ ክርስቲያን የክፋትን ጉልበት ለመቋቋም ኀይል አልባ ሆና ተገኝታለች። 3 (ትርጉም የእኔ)*

እንግዲያው የመንፈስ ቅዱስ ኀይል እግዚአብሔርን በማወቅ የተገኘ የፍቅር ኀይል ሆኖ በመካከላችን ካልንተሠራፋ ምን ይዞ ጉዞ?!

## መልእክተኛነት

መንፈስ ቅዱስ ላኪ መንፈስ ነው። ከአብ ጋር ሆኖ ወልድን ለሥራ ላከው፤ ወልድ ደግሞ እርሱን ወደኛ ሲልከው የኢየሱስ ምስክር እንድንሆን ለመልእክተኛነት ታላቅ ኀይሉን ይዞ መጣ። መንፈስ ቅዱስ ለወንጌል ስርጭት መተኪያ የሌለው የኀይል ምንጭ ነው። ከዲያብሎስ መንግሥት እስራት ከጨለማ ሥልጣን ሰዎችን ነጻ ለማውጣት አብሮን የሚሠራ ራሱ መለኮት የሆነው መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎቹም ያሹናል። ይኸው መንፈስ በጥልቅ ካደረብን ታዛቢ ተቀማጮች ከመሆን ይልቅ በጽናት ተራማጆች እንድንሆን ያደርገናል። የቤቱን ጓዳዎች ብቻ እየዞረ፣ በየኮሪደሩ እየተጠማዘዘ ለመኖር የሚፈልግ እንቅስቃሴ እያደር ይመክናል፤ ወይም ብዙ ሳይቆይ እግሮቹ እርስ በርስ ተጠላልፈው መራመድ ያቅታቸዋል። ወንጌል አድራሽነት የጤናና የትኩስነት ዋስትናችን ነው።

## ብርቱ የጌታ መመለስ ጥበቃ

ካሪዝማዊ - ጴንጤቆስጤያዊ እንቅስቃሴ በቀደሙት ዘመናት አንድ ዋና መልኩ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ተመልሶ መምጣት በጉልህ ድምፅ ማብሰር ምዕመናንም ይህን ውድ ጌታ እንዲጠብቁ

ማነቃቃት ነበር። እውነት ለመናገር የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ጸጋዎች መውረድ የመጨረሻው ዘመን ክስተት ነው። ‹‹እነሆ በመጨረሻው ዘመን መንፈሴን------ አፈስሳለሁ›› ያለው ትንቢት "የጌታ ቀን ሳይመጣ" ሰዎች ከፍርድ እንዲድኑ የጌታን ስም መጥራት እንደሚገባቸው የሚያስገነዝብም ነው።(ሐዋ 2፡16-21) ቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ ለቤዛ ቀን የታተምንበት በመሆኑ (ኤፌ.4፤30) ለዚያ ቀን ልባችንን ማነቃቃቱ ተገቢ ነገር ነው። ያ መንፈስ የርስታችን መያዣ ሆኖ ስለተሰጠን ጌታ ሲገለጥ ስለሚጠብቀን በረከትና ጸጋ በውስጣችን ጉጉት መፍጠሩ የጤና ምልክት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያስወድደው ቅዱስ መን ፈስ ነክቶን ከሆነ "እባክህ ቶሎ ቶሎና "እያልን እንዘምራለን። ‹‹ላይህ እናፍቃለሁ ››እያልን እንዘምራለን።

አሁን ግን አንድ ከፍተኛ ሥጋት የተፈጠረበት ጊዜ ነው። ሥጋቱ ምንድነው ቢባል ካሪዝማውያን ነን የምንል ሰዎች አሁን-ዛሬ ስለሚገኝ ምድራዊ ብልጽግና እጅጉን የምንጨነቅ የመንፈሱን ስጦታዎችም ለዚሁ ዓላማ የምናሰልፍ የጌታችን መመለስ በእምነት አንቀጻችን ላይ ጎልቶ ቢቀመጥም በልብ ጽላታችን ላይ ግን የደበዘዘ መሆኑ ነው። ጴንጤቆስጤያዊነት ወይም ካሪዝማዊነት በድል የተነሣውንና ያረገውን ተመልሶም በክብር የሚመጣውን ጌታ በናፍቆት የማይጠብቅ ከሆነ አፈር አፈር ማለቱ አይቀርም፤ እያደርም ከአፈሩ ጋር ሊቀላቀል ይችላል። ነገር ግን ዛሬም በዐዲስ ጉብኝት ያ መንፈስ ሲመጣ የንጋት ኮከብ ወደ ሆነው ሙሽራ አንገታችንን ቀና ያስደርጋል።

ጥንቁቅ ፔክክብ

እነዚህን ሰባት "ዕንቁዎች" ጥሪታችን አድርገን ለቀጣዩ ትውልድ እናስተላልፍለት ስንል ማንሣት ያለብን ዋና ጥያቄ ቅርሱስ ይታወቅ፤ ለመሆኑ ማስተላለፊያው ይሠራል ወይ? የሚል ብርቱ ምርምር ነው። ከተከታዩ ትውልድ ጋር ያለን ዝምድና ዐደራ ለመረካከብ የሚያስችል ነው ወይ? ይህን ጥያቄ በአምንታ መመለስ ካቀተን ሥራችን ሁሉ የእንቧይ ካብ እንዳይሆን ያስፈራል! ለትንታኔ የሚያወላዳ ጊዜ ባይኖርም ለማስተላለፍ የተመቸ ጎዳና እንዴት ልናበጅ እንደምንችል ፍንጭ የሚሰጡንን መነሻዎች ልወርውር።

- ቀጣዩን ትውልድ በቅን መንፈስ እንውደደው። ዐደራ ለማስረከብ የተመቸ ሁኔታ በአስረካቢና በተረካቢ መካከል



የሚኖር ቀረቤታ፣ አመኔታ፣ መከባበርና ቤተ ሰባዊነት ነው።

- አዲሱን ትውልድ የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ ለአንተ ነው እንበለው፤ እናበረታታው፤ እናስጠጋው፤ እናስተ ዋውቀው። በስጦታዎቹ ቅን ሥራ እንዲሠራ በር እንክፈትለት፤ ምሳሌም እንሁነው።

- ከልካይነት ብቻውን መካን ፍልስፍና መሆኑን ተገንዝበን አዎንታዊ ተግባር እናከናውን። አዎንታዊ እንሁን ስንል ያለ ፈውን ዘመን ግርማ በትዝታ እያሞጋገስን ያሁ ኑን አካሔድ በደምሰሳው አንራገም ማለታችን ነው። ከቤተ ክርስቲያን ወጣቶች ጋር በነበረን ውይይት ላይ አንድ ወጣት የተናገረው ትዝ ይለኛል። እንዲህ ነበር ያለው፦ ‹‹የሚያገኘን ሁሉ የሚነግረን ያ ዘመን እንዴት ዕፁብ እንደ ነበረ ነው። የኛ ዘመን ይህ ትውልድ ደግሞ ርባና ቢስና ከንቱ እንደ ሆነ ነው። እንዲያውም እኔ የሚመስለኝ ሠርጉ ሁሉ አልቆ በለቅሶ ጊዜ የተወለድን ዕድለ ቢስ ልጆች ሳንሆን አንቀርም››

  ይህን ሰምቼ ታላቅ ተግሣጽ ተቀብያለሁ። ጥሪው በከንቱ እናባብላቸው ሳይሆን፣ ለየዘመኑና ለትውልዱ በሕያውነት የሚሠራ አዎንታዊ አምላክ መኖሩን አምነን እንንቀሳቀስ ነው። ‹‹ለእናንተና ለልጆቻችሁ ------ በሩቅ ላሉት ሁሉ ነውና ተብሎ የተነገረለት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ተስፋ ››ታላቅ ብሥራት ነው።

- እውነትን ለመንገር ከፍቅር የመነጨ ድፍረት ይኑረን። የተግሣጽ በትር የጨበጠ እጃችንን የሚመራው የፍቅር ልብ መሆኑን እናረጋግጥ። መጪውን ትውልድ በእግዚአብሔር ሥርዐትና ዕውቀት ካልሄድን የሚመ ጣውን አደጋ እናሳየው።የሰው ጫጫታ፦ የአጀብ ሆታ፤ ምንጩ ያልተጣራ ድፍን ስሜት የሚያራግበው ሁካታ ሳይሆን የመለኮት ጉልበት እንደሚያሻን፤ እውነተኛ የመንፈስ ሥራ በመካከላችን መገለጡ እጅግ እንደሚያስፈልገን እናስረዳው፤ ከሰማይ የመለኮት ኀይል ካልመጣ በኛ ግርግር ብቻ የዘመኑን ተግዳሮት እንደማን ወጣው እናስገንዝበው። ግርግር ለሌባ ይመቻል።

*19) ያለውን አምላክ በደስታ እንጠባበቃለን ፤ በዚህ ጊዜ ሁላችን ርስ በርስ ስንነጋገር ሁለት ጽንፎች (ጥጎች)መሸሽ አለብን።እነዚህም ሥጋዊ ድሳዊነት (carnal triumphalism) እና ግልል ምሁራዊነት (detached Intelectualism) ናቸው። በነዚህ ምትክ ግን መንግሥቱን እየገነባ ላለው ጌታ አክብሮት የተሞላ አምልኮ እናቀርባለን።3 (ትርጉም የእኔ)*

መንግሥትህ ትምጣ እያልን የጌታን ምስፍና የምንጠባበቅ ካሪዝማውያን ክርስቲያኖች አሁን ሁሉን እንደጨበጥን ዐይነት ፉከራና ሽለላ ማብዛት፣ ማስተዋል በጎደለው ግርግር የጌታን ስም ለሥላቅ መዳረግ ሥጋዊነት ነው። ስለ ድል ብናወራም ይህ ዐይነቱ ድል ሥጋዊ ድሳዊነት ነው። በጌታ መመካት ለጌታ በመገዛት የሚመጣ ነው። የተረጋጋጠ ድል ያለው በእውነቱና በሥርዐቱ ውስጥ ነው። በዚህ ተጻራሪ ደግሞ ከጣጣ ፈንጣጣው ለመገላገል የሚንጫጫውን ሕዝብ በልብ እየናቁ፣ ራስ እየነቀነቁ ከዳር መቆም ምንም አይረባንም። ቤቱ የእኛ ነው፤ መንፈሱ ለእኛ ነው፤ ተልእኮው የሁላችንም ነው። በቅዱስ ድፍረትና ትሕትና በእግዚአብሔር በኩል መሰለፍ የጊዜው ጥሪያችን ነው።

እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሥሉስ አምላክ ይርዳን!



**ዋቢ መጻሕፍት**


1. J. I Packer, *Keep in Step with the Spirit* [Leicester IVP,1984], p. 184-185
2. David Watson, *One in the Spirit* [London Holder and Stoughton,1973] p.22
3. David Smith, *Against the Stream: Christianity and Mission in an age Globalization* [Leicester IVP 2003 p. 57, 59, 64

# ምን ዐይነት መሪነት

ብዙ ጣጣ ቢኖርበትም "ምን አባቱ" ብለን መተው ከማንችላቸው የሕይወት ጉዳዮች አንዱ መሪነት ነው። የምናተኩርበት ዐውድ ቤተ ክርስቲያን ይሁን ወይም ቤተ ሰብ፣ አገር ይሁን መንደር መሪነት በጥሞና መታሰብ ያለበት ጉዳይ ነው። ስለ መሪነት ሳስብ ከማስታውሳቸው ንባቦች አንድ መንደርደሪያ ልውሰድ፤ ቻርልስ ሲምፕሰን የተባሉ የቤተ ክርስቲያን መሪ ገጠመኝ ነው።

"መኪና ተከራይቼ ወደ ሎስአንጀለስ አየር ማረፊያ የነዳሁበት ያ ቀን ትዝ ይለኛል። ከዚህ በፊት መንገደኛ ሆኜ ባውቀውም መኪና እየነዳሁ ለመሄድ ግን የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር። ባለ ስድስት መስመር ፈጣን አውራ ጎዳና ውስጥ ገብቼ ሳሽከረክር ባለቤቴ የከተማውን ካርታ ይዛ ትረዳኝ ነበር። ብዙ ከሄድን በኋላ ነው ራሱን ሎስ አንጀለስን አልፌ እንደ ወጣሁ ያወቅሁት።

ምንም አይደል፣ በቂ ጊዜ አለን አልኩና ከዋናው መንገድ ፈቀቅ ብዬ ቀይ መብራት ያቆመውን ነጂ 'ወደ አየር ማረፊያው የምደርሰው እንዴት ነው?' ብዬ ጠየቅሁ። 'ወደ ኋላ ዞርና ወደ ደቡብ ሂድ፤ የሚቀጥለውን ዋና ጎዳና በቀኝ በኩል ያዝና ብዙ ኪሎ ሜትር ወደ ፊት ሂድ፤ አታጣውም' አለኝ።

ዞረን ወደ ደቡብ ሄድን፤ የሚቀጥለውን ቀኝ ያዝንና ብዙ ነዳን፤ ግን ኤርፖርቱ የለም። ቀኑ እየመሸ መጣ፤ ጊዜም እያነሰ



ነው። 'ምናልባት አውሮፕላኖቹ የሚበሩበት አግጣጫ ይመራኝ ይሆን?' ብዬ ዐሰብኩ፤ ግን እርሱም አልሠራም።

ከዋናው መንገድ እንደገና ወጣሁና 'የቤንዚን ማደያው ሠራተኛ ሊረዳኝ ይችላል' ብዬ ወደ ማደያው መኪናዬን አስጠጋሁ፤ ቦታው ጨለምለም ብሏል።

'እባክዎ ሊረዱኝ ...?'

እኔ እንግሊዝኛ ስናገር እርሱ በስፓኒሽ ይመልስልኝ ጀመር።

'ሌላ የሚረዳኝ ...?'

ምንም መግባባት አልተቻለም፤ ስፓኒሾች ሠፈር ነበር የገባነው። ቦታው እንደ ጠፋኝ በደንብ ገባኝ። 'ምነው የማውቀው ባይመስለኝ ኖሮ' አልኩና በልቤ አንድ መንገድ ላይ ስንወጣ መብራት አቆመን።

'እባክዎን ወደ ሎስአንጀለስ አየር ማረፊያ እንዴት እንደምንደርስ ሊነግሩኝ ይችላሉ?' አልኩና አጠገቤ የነበረውን ሌላ አሽከርካሪ ጠየቅሁ።

'ተከተለኝ' አለኝና እንደ ረፈደብኝ ያወቀ ይመስል ይከንፍ ጀመር። ሰውየውን አላውቀውም፤ መንገዱን ማወቁንስ በምን ዐውቃለሁ? አንድ ነገር ግን ርግጥ ነበረ፤ መንገዱን እኔ አለማወቄ። እሱ ወደ ቀኝ ሲዞር እኔም ወደ ቀኝ፣ ወደ ግራ ሲዞር እኔም ወደ ግራ፣ ቢጫ መብራት ሲጥስ እኔ ቀይ እየጣስሁ፣ ሲያፈጥን እያፈጠንሁ የእርሱን ጅራት ብቻ እንደ ተከተልሁ ከአሥር ደቂቃ ግስገሳ በኋላ የሎስ አንጀለስ አየር ማረፊያ ላይ ከቸች ስንል መንግሥተ ሰማይ የገባሁ ነው የመሰለኝ። ምስጋናዬን በታላቅ ፈገግታ ገልጬ ተሰናበትኩትና ወደ አውሮፕላኑ አመራሁ፤ ለጥቂት ሳይዘጋ ደረስሁ።

መሪነት ምን እንደ ሆነ የገባኝ ያን ቀን ነው። መሪነት የሩቅ ጥቆማ አይደለም፤ መሪነት ማመላከት አይደለም፤ መሪነት ወደሚፈለገው ግብ ራስ ሔዶ ማሳየት ነው።"

ይህን ያሉት ቻርልስ ሲምፕሰን ናቸው። የእርሳቸውን እዚህ ላይ እንግታና ወደ እኛ ወደ አገራችን ወደ ቤተ ክርስቲያናችን እንመልከት።

እኛ መሪዎች አሉን ወይ? ዛሬ በቤታችን ወስጥ፣ በቤተ ክርስቲያን፣ በአገር ደረጃ፣ በኅብረተ ሰብ መካከል የሚሔዱበትን የሚያውቁ፣ ወደ ርግጠኛ ግብ የሚገስግሱ፣ ይዘው የሚያደርሱን መሪዎች አሉን? እኔ እንጃ! እኔ እንጃ! እኔ እንጃ!

በየቦታው፣ በየመደቡ "መሪዎች" መሾማቸው፣ በየስብሰባው "መሪዎች" መምረጣችን፣ ማሠልጠናችንና መሰየማችን አልቀረም:: ይህ ሁሉ ግን እርግጠኛ መሪዎች እንዳሉ ማስተማመኛ የሚሆን አልመሰለኝም። ምናልባት እያፈራን ያለነው "ነገር አርቃቂዎች"፣ "ካርታ ነዳፊዎች ብቻ"፣ "እስከ ጊዜው ይገፍ ልቀይ ተግደርዳሪዎች"፣ "ዒላማ ቢስ ተኳሾች" ወዘተርፈ... ቢሆንስ? ገና በበቂ ያልተመለሰ የመሪነት ጥያቄ አለ፤ በቤተ ክርስቲያንና ከዚያም ውጭ የእውነተኛ መሪ ጥማት ሕዝቡን እንዳንገበገበ ነው፤ ብዙ ዐይኖች ይንከራተታሉ፤ "ኑ በዚህ" የሚላቸው ሰው ፍለጋ። የማን ዐይኖች? የወጣቶች፣ የሽማግሌዎች፣ የሴቶች፣ የሰባኪዎች፣ የዘማሪዎች፣ የነጋዴዎች፣ የተማሪዎች ...።

## ሰራት ዐይነት ጠማማ መሪዎች

መጽሐፍ ቅዱስ የተጨባጭ ሕይወት መጽሐፍ ነው፤ በተበላሸ መሪነት በሕዝብ መካከል የደረሰውን ስንት ዐበሳ በጣም በሚሰብ ትረካ ይነግረናል። ከእነዚያ መካከል አራቱን ለትምህርታችን ላንሣላችሁ።

### 1 ዳጠው ደፍጥጠው - ለምባ ገነን መሪነት

ይህ መሪ "እኔ ያልሁት ብቻ ትክክል ነው፤ ከተባለው ውልፍጥ ማለት ለሞት/ለውድቀት/ይዳርጋል" የሚል ዘይቤ አለው። የሰሎሞን ልጅ ሮብአም አንዱ ምሳሌ ነው (1ኛ ነገሥ. 12)። "ትንሺቱ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ትወፍራለች" የእብሪት ንግግር ነው። በጊንጥ በመግረፍ ማንነቱን ለማሳየት መፈለጉ የሰው መንፈስ በጅራፍ እንደማይገራ ያልገባው መሆኑን ያሳያል። "መንፈሳዊ ሥልጣንን መጠቀም" በሚል ሽፋን ሥጋዊ ዕቡይነትን በእግዚአብሔር መንጋ ላይ መጫን ከጎረምሶች ባልንጀሮች ያገኘው ምክር ሕዝቡን ወደ ዐመፅ፣ እስራኤልን ወደ መከፋፈል፣ ሮብዓምን ወደ ሐፍረት የዳረገ ክፉ ምክር ነበር።

"እሺ ብትላቸውና ለዚህ ሕዝብ አሁን ባሪያ ብትሆን፣ በገርነት ብትናገራቸው በዘመኑ ሁሉ ባሪያዎች ይሆኑልሃል" የሚለውን



የአስተዋይ ሽማግሌዎች ምክር ናቀው። ሰዎችን የመምራት ጥበብ እዚህ ውስጥ አለ።

ለምንመራቸው ሰዎች ሎሌ የመሆን፣ የማገልገል፣ የባርነትና የትሕትና መንፈስ ማግኘት ዋናው የመሪነት ቁልፍ ነው። የመሪነት ጥንካሬም የክንድ ጡንቻ ብርታት ሳይሆን የልብ ስፋት ኀይል ነው።

### 2 "ታዲያ ምን ይደረግ?" - ግድ የለሽ መሪነት

የአምባ ገነንነት መድኃኒት ግድ የለሽነት አይደለም። ሰዎችን አታስጨንቁ ማለት እንደ ፈለጉ እንዲሄዱ ተዉአቸው ማለት አይደለም። ግድ የለሽነት ልክ እንደ አምባ ገነንነት ለእግዚአብሔር ሰዎችና ሥራ ,ደንታ ቢስ የመሆን ገጽታ ነው።

ካህኑ ዔሊ አሳዛኝ ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር ይህን የሕዝብ መሪ ሲወቅሰው "ልጆቹን የእርግማን ነገር እንዳደረጉ አውቆ አልከለከላቸውም" ብሎታል (1ኛ ሳሙ. 3፥13)፤ ደግሞም "ከእኔ ይልቅ ለምን ልጆችህን አከበርህ?" ይለዋል (1ኛ ሳሙ. 2፥29)። አንዳንድ ጊዜ ግድ የለሽነታችን የሚመነጨው ከሰው ክብር ጥቅም ወዳጅነት ወይም ሌላ ነገር እንዳናጣ ከመሳሳት ነው። መጨነቅ ባለብን ጉዳይ ላይ "ምን ላደርግ እችላለሁ?!" በሚል ያልፀዳ ልስላሴ ነገሩን ገሸሽ በማድረግ ኀላፊነትን በተገቢው መንገድ አለመወጣት በዔሊ ቤት ላይና በሰበቡም በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እንደ ደረሰው ያለ "ኢካቦድ" (የክብር መጥፋት) እንዲመጣ መጋበዝ ነው። እግዚአብሔር የጽድቅ ሐሞት ይስጠን።

### 3 ምንደኛ - ጥቅም ለሳዳጅ መሪነት

በመሪነት ጥቅም ይገኛል? እንዴታ! "ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል"። ይህ ሥጋዊ የጥመት አስተሳሰብ በከፍተኛ ደረጃ የእግዚአብሔርን ቤት የሚያውክ፣ መንጋውን የሚበትን በሽታ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ብዙ ሰዎች ጥቅም ፍለጋ ብለው መሪነት ላይ አይቀመጡ ይሆናል፤ ሥፍራውን ከያዙ በኋላ ግን የግል ጥቅም የሚያገኙበትን ሁኔታ ሲያዩ ራስን ገዝቶ በቅን መንገድ ለመራመድ ከባድ ፈተና ይሆንባቸዋል። ተፈትኖ የወደቀው የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ ሳዖል ለዚህ የተግሣጽ

ሥልጣን አለን፤ ሥልጣናችን ግን የወኪል ነው፤ ሙሉ ተጠያቂነትም አለብን። በመጀመሪያው ምዕራፍ "ግዙ" ያለው አምላክ በሁለተኛው ምዕራፍ "ከዚህ ብሉ፤ ከዚያ አትብሉ" ብሎ ያዝዛል። በሦስተኛው ምዕራፍ "ወዴት ነህ?" ብሎ ይጠይቃል። እኛ ተጠያቂ ነን፤ እርሱ ግን ሁሉን ጠያቂ፣ ተቆጣጣሪና ብያኔ ሰጪ ነው። እኛና እርሱ የደረጃ ሳይሆን ልዩነታችን የዐይነት ነው። ፈጣሪና ፍጡር።

የተባለው ሁሉ ተብሎ ግን እግዚአብሔር ሰው የመምራትን ኀላፊነት እንዲሸከም መፍቀዱ ለዚህም መጥራቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተሳሰብ ነው። ኀጢአት ጥቁር ጠለሸቱን እየቀባው የሰው መሪነት አስፈሪ ጭራቅ ቢሆንም፣ ለፍጥረት ሁሉ ደኅንነትና ለእግዚአብሔር ሀብታት መጋቢነት የተጣለብን ኀላፊነት አልተሻረም። በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ውስጥ እንደም ናየው ልዑል እግዚአብሔር በምሕረቱ እያደሰና ጸጋውን እየሰጠ ለሕዝቡ መሪዎችን ይሾማል፣ ይቀባል፣ ያሠለጥናል። ሙሴን ለነጻ አውጪነት፣ ዳዊትን ለንጉሥነት፣ ነህምያን ለአዳሽነት ጠራቸው፤ አስነሣቸው፤ አበቃቸው።

## ሱሴ ምሳሌያዊ መሪነት

በሥጋ የተገለጠው አምላክ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰማይን ኑሮ በምድር ላይ የኖረ ሰው ነው። "*መንግሥትህ ትምጣ*" እርሱ የሰጠን ጸሎት ነው። "*አምላክ ሆይ... የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው። ጽድቅን ወደድህ፤ አመፅንም ጠላህ ...*" የተባለለት ይህ ጌታ የመሪነት ምሳሌና መደምደሚያ ነው። ጌታችን በምድር ላይ በነበረ ጊዜ "ልጆቹ"፣ ተማሪዎቹ ሊከተሉት የሚገባውን የመሪነት ዘይቤና የዘይቤውም መሠረት ምን እንደ ሆነ ገልጧል። ከእርሱ ወዲያ መሪነት ላሳር፤ ከእርሱ ወዲያ እውቀት ላሳር ነው። እርሱ እንዴት እንዳስተማረን እስኪ ባጭሩ እንመልከት።

በወንጌሎች ውስጥ ጌታችን በትምህርቱም ሆነ በተግባሩ የገለጠው የመሪነት ስልት በጣም ሥር ነቀል የሆነና እርግጠኛ ውጤት የሚያመጣ ነው።

> *"እንደምታውቁት በአሕዛብ ዘንድ ነገሥታትና ገዢዎቻቸው፥ ሥልጣናቸው ይታወቅላቸው ዘንድ ከበታቻቸው ያሉትን ሰዎች ሰጥ ለጥ*



> *አድርገው ያስተዳድሯቸዋል። በእናንተ ዘንድ ግን እንዲህ መሆን አይገባውም። ከእናንተ መካከል ትልቅ ለመሆን የሚፈልግ የሁሉም አገልጋይ ይሁን፤ የሁሉ የበላይ መሆን የሚፈልግ የሁሉ ባሪያ ይሁን። እኔ ራሴ እንኳን ወደዚህ ዓለም የመጣሁት ሰዎች እንዲያገለግሉኝ ሳይሆን፥ ላገለግላቸውና ሕይወቴንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጌ ለመስጠት ነው።" ማርቆስ 10፥42-45 (ሕያው ቃል)*

ሥልጣን የራስን ማንነት ከፍ ማድረጊያ፣ ፈቃድን መፈጸሚያ፣ ተቃራኒዎችን ማስገበሪያ መሆኑ የተረጋገጠበትን የዚህን ዓለም የመሪነት አካሄድ ከነሥሩ የሚመነግል ዐሳብ ነው። መሾም ማለት ጌትነት ሳይሆን ሎሌነት/አገልጋይነት ነው። "ትልቅነትን" አይቃወምም፤ የትልቅነት ትክክለኛ ፍቺ ግን ሁሉንም ማገልገል መቻል ነው ይለናል። መብለጥን አይቃወምም፤ ብልጫ ግን በገዛ ፈቃድ የሌሎች ባሪያ መሆን ነው ይለናል።

በሰዎች መካከል አለቅነት ሲሰጠን፣ ልናገለግላቸው ዕድል እንደ ሰጠን እንድናስብ ያበረታታናል። ሌሎችን ለምኞታችን እንድን ጠቀምባቸው ሳይሆን ቢያስፈልግ ራሳችንን ለእነርሱ ጥቅም እንድንሠዋ ይጋብዘናል፤ የእኔ የመሪነት ባንዲራ ቀለሙ ይኸው ነው ይለናል፤ ራሱንም እንደ ዋና ምሳሌ ያቀርባል።

ወደ ምድራዊ ሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ በአንዲት የማትረሳ ምሽት ከራት በኋላ አስገራሚና ልብ የሚነካ ሥራ ይሠራል። ከማዕድ ተነሥቶ ልብሱን ያስቀምጥና ፎጣ ታጥቆ፣ ውሃ በሳህን ጨምሮ የተማሪዎቹን እግር ማጠብ ይጀምራል። ብዙ ሀይ ሀይታና "ፈጽሞ አይደረግም!" የሚል መከላከል ቢያጋጥመውም በልቡ የቆረጠበትን ተግባር ያከናውናል፤ ፍሬ ነገሩንም እንዲህ ሲል ያብራራል።

> *"እናንተ 'መምህር ጌታ' እያላችሁ ትጠሩኛላችሁ ...ትክክል ነው ... በእርግጥም ነኝ፤ ታዲያ እኔ ጌታችሁና መምህራችሁ ስሆን እግራችሁን ተጎንብሼ ካጠብኩ እናንተ ባልደረቦች ደግሞ አንዳችሁ የአንዳችሁን እግር ማጠብ ይገባችኋል፤ .... እኔ ምሳሌ? አሳይቻችኋለሁ አገልጋይ ጌታውን፣*

*መልእክተኛ ላኪውን አይበልጥም፤ ይህ ግልጽ ነው" (ዮሐ. 13፥ 13-16 ሕያው ቃል)*

በዚህ ንግግሩ ውስጥ ጌታ በቃሉና በተግባሩ መሪነት አገልጋይነት እንደ ሆነ፣ ወዲያውም ደግሞ ምሳሌያዊነት እንደ ሆነ አረጋግጦ ነገረን።

## በፈርጣማ ጡንቻ እንደቁስ ወይስ እንደ ድመት እንፍረገረግ?

ጠንካራ መሪ ማለት ምን ዐይነት ሰው ነው? ጥሩ መሪ ማለትስ? አልሰማ ያለውን ሞገደኛ ሕዝብ እየደቆሰ ፀጥ የሚያደርገው ነው? ወይስ ከእግሩ ሥር ወድቆ "እናንተ ያላችሁት ይሁን" እያለ የሚለማመጠው ነው። የጌታችን ንቁ ተማሪ ጴጥሮስ ከሁለቱም ምርጫዎች የተለየ ማለፊያ ምክር ሰጥቶናል። *"ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኀይል አትግዙ" (1ኛ ጴጥ. 5፥3)።*

ወዳጆቼ፤ ሰዎች የሚያደምጡን በጩኸታችን ብዛት አይምሰላችሁ፤ በእውነት የሚታዘዙን በጉልበታችን ጥንካሬ አይደለም። የመሪነት ቁልፉ ሌሎች እንዲያደርጉ የምንፈልገውን አድርገን ማሳየት ነው። እንደ ምሳሌአዊነት ለዘለቄታው ሰዎችን መምራት የሚቻልበት ጥበብ አይታየኝም። ምሳሌ ስንሆን እኮ የምንናዘዘው ነገር ሲደረግ መቻሉን እናረጋግጣለን፤ ወዲያም እኛ ራሳችን የምንከተለው የሕይወት መሥመር ያ መሆኑን በተጨባጭ እናሳያለን። "ከእልፍ መመሪያ አንድ ምሳሌ!"

ጳውሎስ በወጣትነቱና በዐይናፋርነቱ ለሚሸማቀቀው መሪ ለጢሞቴዎስ እንደዚህ አይለውም፡- "ጢሞቴዎስ ሆይ፤ ማንም ልጅነትህን አያጥላላብህ፤ አንተም ራስህንና አንገትህን አቀርቅረህ አትሂድ፤ ሁልጊዜ ኮት መልበስህን አትርሳ፤ ትከሻህን ሰበቅ እያደረግህ ድምፅህን ጉርነን አድረገህ ተናገር፤ ሲንጫጩብህ ጠረጴዛውን በቡጢ ምታና 'አንድ ጊዜ ጸጥታ!' በላቸው። ጥያቄ የሚያበዙትን አንድ ሁለቱን ከሥራ አባርራቸው፤ ሌሎችን ደግሞ ሰላምታ ሲሰጡህ በግንባር ብቻ መልስላቸው ..."

በፍጹም እንዲህ አላለውም፤ የሥልጣን ማረጋገጫው መንገድ ይህ አይደለም፤ ይልቅስ ያለውን እንስማ፡- *"... ማንም አይናቅህ፤ የምታስተምረውን ትምህርት፥ በኑሮህ፥ በፍቅርህ፥ በእምነትህና በንጽሕ አካሄድህ እያሳየህ ለምዕመናን ሁሉ ምሳሌ ሁን።"*

የሚያስከብረን ይኸው ነው። የተሰጠንም የመሪነት ስልት



ምሳሌአዊ አገልጋይነት ነው።

## የሎሌ ወይም ምሳሌያዊ መሪነት ዋና ዋና መርሖች

ሎሌው መሪ ብዙ ሊከተላቸው የሚገባ የአስተሳሰብና የድርጊት መመሪያዎች ቢኖሩትም ዋናና ጠቃሚ ናቸው የምንላቸውን ሦስቱን ልጥቀስ።

### 1. <u>ስለ እግዚአብሔር የሰዎች አገልጋይ መሆኑን አጥብቆ ይወቅ</u>

የልዑል እግዚአብሔር ጽኑ ትኩረት የሰው ልጅ ነው። መሪዎችን ሲጠራ ለሚገለገሉት ሰዎች ብሎ ነው እንጂ ለመሪዎቹ ብሎ አይደለም። የእርሱ ጥንቃቄ ለተቸገረው አዳም ስለሆነ መሪዎች አጋሮቹ ናቸው።

- የመሪነት ምክንያቱ ሰው ነው

ያህዌ ሙሴን በምድረ በዳ ሲጠራው በራሱ ቃል የተናገረው ይህንን ነው። *"... የሕዝቤን መከራ በእውነት ዐየሁ፥ ... ጩኸታቸውን ሰማሁ፤ ሥቃያቸውን ዐውቂአለሁ፤... አወጣቸው ዘንድ ወረድሁ... ሕዝቤን ከግብጽ ታወጣ ዘንድ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ..." (ዘፀ. 3፥7-10)*

ሙሴ ራሱ የሚያሳዝን ሰው ነበረ፤ በትልቅ ማዕረግ በቤተ መንግሥት አድጎ፣ ፍትሕ ለማስፈን የበኩሉን ጥረት ቢያደርግም ሳይሳካለት ቀርቶ ሕይወቱን ለማትረፍ ሸሽቶ የበግ ጠባቂ ሆነ፤ ይሁን እንጂ ጥሪው "ሙሴ ሙሴ ሆይ፤ ከስንት ማዕረግ ወርደህ እዚህ የሰው በግ ጠባቂ መሆንህ አሳዝኖኛል፤ አሁን እንዴት አድርጌ እንደማከብርህ ዐሳብ መጥቶልኛል..." የሚል አልነበረም። የመሪነት ቀዳሚ ምክንያት ሕዝበ እግዚአብሔር ነው። ለእነርሱ ሲል ነው መሪዎችን የሚያስነሣው። በአዲስ ኪዳንም "ለቤተ ክርስቲያን እረኞች፣ አስተማሪዎችን ... ሰጠ" ነው የሚል።

- የመሪነት አንጻሮት (focus) ሰው ነው

አሳታዊ በሆነ ብርቱ ቃል ነቢዩ ሕዝቅኤል እንዲህ ይላል፡- *"ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ራሳቸውን ለሚያሰምሩ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው፤ እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ*

*አይገባቸውምን?" (ሕዝ. 34፥2)።*

*ራስ ማሰማራት ማለት ጥቅም፣ ምንዳእ፣ ምቾት፣ ተድላ፣ ዝና፣ ታይታ የሚገኝበትን ሁሉ መፈላለግ ለዚሁ ሲባል ወደ መሪነት መምጣት ወይም ከመሪነት አለመውረድ ነው። ነገር ግን የሎሌ መሪ/የእውነተኛ እረኛ ትኩረት በጎች ናቸው፤ በጎች! በጎች! የደከሙ በጎች፤ የታመሙ በጎች፤ የተሰበሩ በጎች፤ የባዘኑ በጎች፤ የጠፉ በጎች። ማጽናት፣ ማከም፣ መጠገን፣ መመለስ፣ መፈለግ ነው ሥራው። ሌላ ምን ሊሠራ ነው? ተግባሩ ሁሉ ከበጎች ደኅንነት ጋር የተያያዘ ነው።*

- የመሪነት ሥራ መለኪያው ሰው ነው

ከጌታችን በኋላ የዘመነ ሐዲስ ብርቱ *መሪ* የነበረው ቅዱስ ጳውሎስ አገልግሎቱን የሚለካው በጻፋቸው መጻሕፍት ብዛት ወይም በሰበከው ስብከት ረቂቅነት ወይም በተጓዛቸው ማይሎች ቁጥር አልነበረም፤ በመንፈስ ቅዱስ በተሠሩት ሰዎች ማንነት ነበረ እንጂ።

*"... የእኛን ማንነት ለማወቅ ከሌላ የተጻፈ የምስጋና ደብዳቤ የሚያስፈልጋችሁ አይመስለኝም ... ምክንያቱም ማንም ሰው ሊያነበው የሚችል በልባችን የተጻፈ መልእክታችን እናንተ ናችሁ ... በቀለም ሳይሆን በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ ... በልብ ጽላት ላይ የተቀረጻችሁ ... የክርስቶስ ግልጽ ደብዳቤዎች ..." (2 ቆሮ. 3፥ 2-3 ሕያው ቃል)።*

ሎሌ *መሪነት* ስለ እግዚአብሔር ብለን በእርሱ ፈቃድ ለእርሱ ክብር ሰዎችን ማገልገል ነው።

### 2. <u>ባለ ቁርጥ ሥራ መሆኑን ይረዳ</u>

*መሪነት ለሰዎች አገልግሎት የምንጠራበት መስክ መሆኑ ርግጥ ነው። ይሁን እንጂ መስኩ ላይ በዘፈቀደ አንሄድም፤ በሰማያዊ መሐንዲስ የተተለመ ትልም አለ፤ ቅያስ አለ። ርዝመቱ፣ ስፋቱ፣ ሥራው የሚወስደው የጊዜ መጠን ሁሉ ዕቅድ ወጥቶለታል።*

እግዚብሔር እንደ ሰጠን ጸጋ *መጠን*፣ እንደ ሰጠን እምነት *መጠን*፣ እንደ ፈቃዱ የሥራ ድርሻ አበጅቶልናል። የሁሉ *መሪ ጥሪ* አንድ ዐይነትና እኩል አይደለም። *ሙሴን ቢጠራው* ሕዝቡን ከግብፅ ለማውጣትና በአስፈሪው ምድረ በዳ ለመምራት



ነው፤ ኢያሱን ቢሾመው ለሕዝቡ የማለላቸውን ምድር በታላቅ ተጋድሎ እንዲያወርስ ነው፤ ነህምያን ቢያስነሣው የፈረሰውን ግንብና የኢየሩሳሌምን በሮች እንዲጠግን ነው፤ ጳውሎስን ቢመርጠው ለአሕዛብ የክርስቶስን ምሥራች እንዲያበስር ነው፡ ፡ የእግዚአብሔር *መንግሥት ሥራ* ትልቅና ሰፊ ቢሆንም የእኛ ድርሻ የተወሰነችና ልትጠናቀቅም የምትችል ናት። ዋናው ጉዳይ 'የእኔ የቱ ነው? እስከ ምን ድረስስ ነው?' የሚለው ጥያቄ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምድር ዕድሜው ረጅም አልነበረም፤ ነገር ግን ሲያልቅ አልተጸጸተም። "በምድር ላይ የሰጠኸኝን *ሥራ* ፈጽሜ አከበርሁህ" በሚል የተደላደለ ቋንቋ ነው የጨረሰው። 'እንዴት ይህ ሆነ?' የተባለ እንደ ሆነ ኀላፊነቱን ከማን እንደ ተቀበለውና የኀላፊነቱ ዝርዝር ምን እንደ ሆነ አጥርቶ ያውቅ ስለ ነበር ነው።

### 3. <u>የመንፈስ አንድነት ለመጠበቅ የመሪነት ድርሻ እንዳለው ይወቅ</u>

*መሪነት ተከታይነትን ማምጣቱ አይታበልም። ሎሌው መሪ የሚከተሉትን ሰዎች ወደ እውነተኛው እረኛ እያቀረበ እርሱም የዚህ ጠቅላይ መሪ ተከታይ መሆኑን ማስመስከር ይገባዋል፤ "መንጋው አንድ፣ እረኛውም አንድ" እንደ ተባለው።*

ይህ ሳይሆን ቀርቶ ሰዎችን ሁሉ እንደ ልቃቂት በራሱ ዙሪያ የሚጠመጥም እንዝርት ከሆነ፣ "ለስሙ መጥሪያ እንቅብ ከሰፋ" እውነተኛውን የአንድነት መንፈስ አጠፋ ይባላል። ይህ ዐይነት ፈተና የተጋረጠበት ሐዋርያው ጳውሎስ በየመሪዎቻቸው ዙሪያ እየተኮለኮሉ አንድነታቸው ፍርክርኩ የወጣባቸው የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በተባ ብዕር ይገሥጻል። የየኮከቡ ጭፍራ ለመሆን እንዳልተጠሩ አበክሮ ሲያስረዳ ከዋክብቱን እያረገፈ ይጥላል፤ "ጳውሎስ ምንድን ነው? አጵሎስስ ምንድን ነው?"

*መሪዎች ሆይ፤ ከአንዱ የንጋት ኮከብ ሌላ በየሰፈሩ ችቦ አትለኩሱ። ያ ደማቅ ኮከብ የሕዝብ ዐይኖች ሁሉ ማረፊያ ይሁን!*

ጳውሎስ የአንድነትን *መንፈስ ለመጠበቅ* የተጠቀመበት ሌላው *መንገድ መሪዎችን የጋራ* ሀብት የማድረግ *ጥሪ* ነው። *መሪዎች*፣ ባለ ስጦታዎች በየራሳቸው ምንም ያይደሉ ቢሆኑም የተሰጡን ግን ለጥቅም፣ ለእግዚብሔር ሕንጻ ግንባታ መሆኑን ያስተንትናል፡

በአንድ ጥግ መሆን ከሚያመጣው ድኽነት እንድንተርፍም ያሳስባል። "ዘራፍ የጳውሎስ አሽከር!" እየተባለ እንዲፎከር አልፈቀደም። 'ብታውቁበት ሁሉ የእናንተ ነው፤ ባለ ጠጎች የምትሆኑት በመነጣጠል አይደለም፤ በመተባበር እንጂ' ማለቱ ነው። የሰዎች የስሕተት አደራደር መንገድና የጳውሎስን አዲስ ድርድር በሥዕል መግለጥ ይቃጣኛል።




ነገሩን ለመቋጨት በዚህ ክፍል ያልሁት፣ ሉሌ ምሳሌያዊ መሪ ሰዎችን የሚያገለግል፣ የሥራ ዓላማው ጥርት ብሎ የሚታየውና አብረው የሚሠሩትን ሰዎች አንድነት የሚያሳድግ መሆኑ ይታወቅ ነው። የሉሌ ምሳሌያዊ መሪነት መርኅ ያልኋቸውን እነዚህን ሦስት አእማድ ስመለከት በዘመናዊው የመሪነት ሥልጠና ውስጥ ከሚጠቀሱት ሦስት የመሪ ተግባር መለኪያዎች ጋር ስለተመሳሰሉብኝ ለማገናዘቢያ የሥዕል መግለጫውን አስፍሬስሁ።






ስለ መሪነት ሊባል የሚቻለው ብዙ ነው፤ ግን ሁሉም አልተባለም። ያልነውን እኩሌታ እንኳ እያደረግን ብንኖር ስንት በጎ ለውጥ በሆነ። ወንድማችን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ ብቃት የሚጠይቀውን ይህን የአዲስ ኪዳን አገልጋይነት በተፈጥሮ ጉልበትና በአእምሮ ብልጠት ሊወጣው እንደማይችል በውል ገብቶታል። ስለዚህ *"... በራሳችን እንዳች እንኳ ልናስብ የበቃን አይደለንም"* ይላል። በዚያው ትንፋሽ ደግሞ *"በመንፈስ ለሚሆን ለአዲስ ኪዳን አገል ጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን።"ይላል (2ቆሮ. 3)።*

ድፍረታችን በክርስቶስ በኩል ነው። የማንችለውን እንድንሆን ለጠራን፣ የጠራንን እንድንሆን ለሚያስችለን ለአምላክ ምስጋና ይሁን።

## የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ሥራ በወንጌል ተልእኮ ውስጥ ያለው ሚና

*ሰዎቹ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በየቋንቋችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን ----›› (ሐዋ 2፡11)*

በየዓመቱ በድምቀት ለሚከበር በዓል ከየአገሩ የመጡ እግዚአብሔርን ፈሪዎች የተከማቹባት ኢየሩሳሌም በሕዝብ ተጨናንቃለች፤ ሆቴሎች ተጣበዋል ፤የገባያው ቱማታና የየጎዳናው ላይ ተንቀሳቃሽ ትምምታ ይህን ወቅት ሞቅ ያለ ገጽታ ሰጥተውታል።ያው እንደወትሮው ባንድ ቋንቋ ተግባብተው የእስራኤልን አምላክ አክብረው የመቅደሱ በዓል ላይ ሰንብተው ወደ የአገራቸው የሚመለሱት እንግዶች ዛሬ እንግዳ ነገር ገጠማቸው፡ ፡ ምንም ያልተማሩ ያልተራቀቁ ገጠር አደግ ገሊላውያን ያለ አንዳች ጎልዳፋነት ኖረውበት ሰምተውት የማያውቁትን የልዩ ልዩ አገር ቋንቋ ቀልጥፈው ይናገራሉ። በዐረብኛ፤ በጳርትኛ በላሜድኛ ፤ በጳንጦስኛ--- የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ ይናገራሉ። ለስግደት ለጸሎት ለበዓል ለአምልኮ የመጡት እነዚህ እንግዶች የየተወለዱበትን ሀገር ቋንቋ ሲሰሙ ተገረሙ ተደነቁ ‹‹ለካ እግዜሩ ጳንጦስኛ ይናገራል ፤ የእግዚአብሔር ሥራ ለካ በሰሜን አፍሪቃ ቋንቋም ሊተረክ ይችላል !ለካ የእስራኤል አምላክ የሊቢያ አውራጃም አምላክ ነው። ------



ይህ በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ የተመዘገበው ክስተት ልዕለ ተፈጥሮአዊ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መሆኑን አንዘነጋም ፤መንፈስ ቅዱስ በራሱ ጸጋ በልዩ ልዩ ልሳናት የመናገርን ስጦታ ለምዕመናን እንደሚያድልም እናምናለን። የበዓለ ሃምሳው ቀን ተዓምር የያዘውን ታላቅ ነገረ መለኮታዊ ፋይዳ ሳንረሳ በቋንቋና በትርጉም ሥራ አንጻር የሚያመለክተንን ጉልሃን እውነቶች እስኪ እንይ፡-

መጀመሪያ ነገር እግዚአብሔር አምላክ ቋንቋዎቹን ያውቃል፤ ይናገራል፤ ይሰማል።ለልዑሉ ፈጣሪ ባይተዋር የሆነ ‹‹ራስና ጅራቱ የማይለይ ቅብጥርጥር ግራ አጋቢ ቋንቋ የለም፤ለእርሱ ቁዋንቁዋ ሁሉ ጥርት ያለ፤ ግልጽና ሲደመጥ ፤ ሊነገር የሚችል ነው።

ሁለተኛ ነገር እያንዳንዱ ቋንቋ የሰብአዊ ዐቅም ውሱንነት ካስከተለው የሰው የመረዳት ችሎታ መጠን ከልካይነት በስተቀር ነገረ እግዚአብሔርን ፤ታላቅ ሥራውን ለመናገር የበቃ ነው። ይህ ለመንፈሳዊ ዓለም የተመቸ ይህኛው ያልተመቸ ይህ ቅዱስ ይህ ርኩስ የሚባል ቋንቋ የለም ።የአስተሳሰብ ዓይነቶችና ትምህርቶች በተስፋፋበት ባህል ቋንቋውም ሊዳብር ሊበለጽግ እንደሚችል የታወቀ ቢሆንም ሰዎች የእግዚአብሔርን ማንነት ለመረዳት የሚበቃቸው ተግባቦት በየትኛውም ቋንቋ ቢሆን ሊቀርብ ይችላል።

ሦስተኛ ቋንቋ የማንነት መለያም ነውና ሰው በገዛ ራሱ ቋንቋ ሲያደምጥና ሲናገር የበለጠ ይደሰታል፤ክብር ይሰማዋል።

አራተኛ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ በተለይም የወንጌል መልእክት ለሁሉ ዓይነት ሕዝብና በልዩ ልዩ ቋንቋ ተናጋሪ ፍጡር የተቀረበ ማዕድ ነው።በባሕል በመልክዐ ምድር ወይም በዘመን ያልተከለለ የፍጥረት ሁሉ ድንት ዐዋጅ ስለሆነ በየእምሮው ቋንቋ ብቻ ሳይሆን በየልቡም ቋንቋ ሊያደምጠው ይገባል።

የወንጌል ተልእኮ/ታላቁ ተልእኮ ምንድነው?

የእግዚአብሔርን ደግነት የመንገር ፤ የማወጅ ፤ የማስረጽ ስምሪት ነው።

በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የተገኘውን የዕርቅ ዕቅድ ከፈጣሪ ጋር

ለተኳረፈው የሰው ልጅ የማቅረብ ዲኘሎማሲ ነው።

የኢየሱስ ክርስቶስ  ሕይወት ወደ ሰብአውያን ሕይወት ውስጥ እንዲዘልቅ ለአካላዊ ጆሮ ለልቡና ጆሮም መናገር ነው።

የክርስቶስ ኢየሱስ የሕይወት ዘይቤ በሚያምኑት መካከል የሠርክ ልብስ እንዲሆን የማሠልጠን ተግባር ነው።

ለሁለንተናዊ ሥርነቀል ለውጥ radical transformation የሚያ በቃውን የእግዚአብሔር የምሥራችና የመንግሥቱን ሥርዓተ እሴት ማስረጽ ነው።

እንዚህን አስተሳሰቦች ወንጌላውያኑ ማቴዎስና ማርቆስ ከጻፏቸው ትረካዎች እንገነዘባለን። ሐዋርያው ጳውሎስ ከጻፋቸው ደብ ዳቤዎችም እንረዳለን። ማቴ 28፡18-20 ማር 16፡15 2ቆሮ 5፡ 18-21

እንግዲያው ታላቁ ተልእኮ ሰዎች የእግዚአብሔርን የምሥራች ያውም ኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቱንና የሕይወት ዘዩውን የማስተዋወቅ ወደ ተግባራዊ ኑሮም የማዝለቅ ጥሪ ነው። የዚህ ታላቅ ተልእኮ ምንጭ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ነው። የተ ግባሩ አካሔዱ መመዘኛም ማስተካከያውም ይኸው ቃል ነው።

## ክርስትና - ቃላዊ እምነት

በክርስትና ውስጥ የተገለጠው የዘላለም ሕይወት (ያሁኑንም የወደፊቱንም ይጠቀልላል) የሚገኘው  በዕውቀት ነው። በዘር ፤ በደም በንክኪ የማይገባ ይልቁን በአእምሮ ልቡና በኩል ወደ ሰው ውስጠኛ መንፈስ የሚዘልቅ ዕውቀት የሕይውት መንገድ ሆኖ ተልጧል። ጌታችን እንዲህ አለ፦

‹‹የዘላለም ሕይወትም፤ ብቻህን እውነተኛ አምላክ የሆንከውን አንተንና የላክኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው።››(ዮሐ 17፤3)

ይህም ዕውቀት በመሠረቱና በዋናነት የሚገኘው በቃል ከተሰጠ መግለጫ ነው።‹‹ከዓለም ለሰጠኸኝ ሰዎች የአንተን ማንነት ገለጥሁላቸው ፤ ---------- የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቼአቸዋለሁ›› ብሎ ያለው ጌታ ኢየሱስ የመለኮትና የሰው ግንኙነት ሰነድ ቅዱስ ቃሉ እንደሆነ ሲያስገነዝብ ነው።(ዮሐ17፤6)



ለሐዋርያቱ የተሰጠው ታላቁ ተልእኮ‹‹ስበኩ --- አስተምሩ›› የሚሉ ትእዛዞች ያዘለ ነውና በቃል አማካይነት የሚተላለፍ ሕያው ተልእኮ ነው።

እምነት የክርስትና ዋና መለያ ቢሆንም ‹‹ስለ እርሱ ሳይሰሙ እንዴት ያምኑብታል››ብሎ ሐዋርያው  ጳውሎስ እንደጠየቀው ‹‹እምነት የሚገኘው መልዕክቱን ከመስማት ነው›› ( ሮሜ 10፤14-17)እንግዲያው ክርስቲያንነት ቃላዊ ነው ፤ ተግባቦታዊ ነው። ስለዚህ ሰዎችን ከመጽሐፍ ቃል ጋር ማገናኘት ዋና የተልእኮው ሥራ ነው ።መጽሐፉን  በሚገባቸው ቋንቋ ማቅረብ የዚህ ተልእኮ አካል ነው።‹‹ሂዱና ስበኩ›› ማለት ሂዱና ዐውጁ ማለት ብቻ አይደለም። አንዱ ሰው እንደተናገረው ‹‹ሂዱና ተግባቦትን ፍጠሩ ›› መልእክቱ እንዲገባቸው አድርጉ፤ የምሥራቹ ቃል መታወቁን አረጋግጡ፤ መደመጡ ብቻ ሳይሆን መሥረፁን ተመልከቱ የሚያሰኝ ታላቅ ዐደራነው።

## ኢየሱስ ፍጹሙ የተግባቦት አርኣያ

እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔርን ከሰው ጋር ለመግባባት የሚያስችል ሞዴል ያቀረበ ማንም የለም። የእግዚአብሔር አሳብ፤ የእግዚአብሔር መልዕክት ከሰማይ አደባባይ በተደለቀ ታምቡር ወደ ምድር ያስተጋባ ‹‹ስማ በለው ›› ሳይሆን ‹‹ቃልም ሥጋ ሆነ››በተባለ ምስጢር ወደ መሬት የወረደ ነው። ይህ ትሥጉታዊ አርኣያ (ሞዴል) የኢየሱስ  ክርስቶስ መታወቂያ ነው። ያባት እቅፍ ምስጢር የመሬት ላይ ተጨባጭ ዐዋጅ ሆነ። ኢየሱስ ተርጓሚ ነበር፤ የሰማይን ቋንቋ መስማት ለተሳነን ለእኛ እሱ ራሱ መልዕክቱን በምድር ቋንቋ በግዘፍ ይዞ መጣ፤ እንዲያውም መልዕክቱ ራሱ ሆነ።

ክርስቲያን መልእክተኞች ከዚህ የመጠቀ የተግባቦት ዘዴ አናውቅም። እንግዲያው ክርስቲያን መልዕክተኛነት መሠረቱ ሕይወትንም ቃልንም ተርጓሚነት ነው። ሊደመጥ ሊታወቅ በሚችልበት ሁኔታ ማቅረብ መቻል ነው።

‹‹ሕይወት ተገለጠ፤ አይተነማል ፤እንመሰክርማለን -------የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኂለን ›› ያለው ዮሐንስ በትስብእት የተገለጠውን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥልቅ ከመረዳት በመነጨ ልቡና ሆኖ ነው ፤ የሚሰሙትም በዚያው ዓይነት ግንዛቤ ወደ ኅብረቱ እንዲገቡ የሚማጠን የወንጌል መልዕክተኛ

ሆኖ ነው፡፡(1ኛ ዮሐ 1፤2-3)

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ ‹‹የወንጌል እምብርቱ መልዕክቱ እንጂ የቋንቋው ቅርጽ አይደለም›› ከሚል እምነት ይነሣል፡፡ ይህም መልዕክት ደርዝ የሌለው ወይም ሰዎች የማይረዱት የድምጾች ወይም የፊደላት ስብስብ ሳይሆን በአድማጩ ልቡና ፍቺው ሊጨበጥ በአንባቢው አእምሮ ትርጉሙ ሊታወቅ የሚችል መልዕክት ነው፡፡

እንግዲያው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ የክርስቶስን ሞዴል ተከትሎ ቃሉን ሥጋ የማድረግ ሊተረክ ፤ ሊሰማ፤ ሊታወቅ የሚችል የማድረግ የትሥጉታዊነት ጥሪ ነው፡፡

## የትርጉም ሥራና የወንጌል ተልእኮ ታሪካዊ እይታ

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራና የወንጌል ስርጭት ተደጋግፈውና ተጣምረው የኖሩ አግልግሎቶች ናቸው፡፡ የትኛውም ቀድሞ የተደረገ ቢሆንም አንዱ ለአንዱ መነሻ ወይም መጎልበቻ መሆኑ አልቀረም፡፡ በሰፊው የክርስቲያን መልዕክተኛነት/ሚሲዮናዊነት ታሪክ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ አንጻባራቂ ሥፍራ አለው፡፡ የቅዱሳት መጻሕፍትን መልዕክት ሰሚዎቹ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲደርስ ማድረግ ዛሬ የተፈለሰፈ ዘዴ ሳይሆን ከመነሻው ጀምሮ የነበረ እውነተኛ ተግባቦት የሚያስገድደው ነገር ነበረ፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ዐዋቂዎች እንደሚነግሩን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በነበረበት ዘመን በአካባቢው የሚነገረው ቋንቋ አረማይስጥ ስለነበረ እርሱም ያስተማረው በዚሁ ቋንቋ ነው፡፡ ይህም ማለት በዕብራይስጥ የተጻፉትን ቃላት ንባብ በስብከቱ ውስጥ ወደ አረማይስጥ መልሶ ለሰሚዎቹ አቅርቧል ማለት ነው፡፡ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ያሉ ካህናት የግዕዙን ንባብ አሰምተው በአማርኛ ቋንቋ ስብከታቸውን እንደሚያብራሩት ዐይነት ማለት ነው፡፡

እርሱ ብቻ ሳይሆን ወንጌላውያኑም የእርሱን ትምህርትና ሕይወት ሲጽፉ በመሠረቱ ጌታ ከተናገረበት ቋንቋ ወደ ዘመኑ ዐለምአቀፍ ቋንቋ ወደ ጽርእ (ግሪክ) ተርጉመው እንደነበረ መረዳት ይቻላል፡፡ለዚህም አብነቱ በወንጌላት ውስጥ አልፎ አልፎ ተጠቅሰው የምናገኛቸው የአረማይስጥ (ሴማዊ) ቃላት ናቸው፡፡ ‹‹ረቡኒ›› መምህር፤ ‹‹ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ››አምላኬ አምላኬ



ለምን ተውኸኝ የሚሉት አባባሎች የአረማይስጥ ቃላት ናቸው፡፡

እንግዲያው ከወንጌል ብሥራት ጋር ከመነሻው ጀምሮ የተያያዘ የትርጉም ባህል አለ ማለት ነው፡፡

ሃሮልድ ኩክ ‹‹የክርስቲያን መልእክተኝነት ጉልሃን እይታዎች›› በተባለው መጽሐፋቸው በተለይ የሥነጽሑፉን ሚና ከትርጉም ሥራ ጋር አያያዘው ገልጸዋል፡፡‹‹ክርስትና እንዴት ተስፋፋ;›› በሚለው ንዑስ ምዕራፍ ውስጥ እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹ሥነጽሑፍ ባያሌው ሥራ ላይ ውሏል፡፡ መጀመሪያ ይህን ያህል መደበኛ የሚባል የሥነጽሑፍ ቅስቃሴ ሳይሆን ለአጣዳፊ ተግባራዊ ጉዳዮች የሚውል ጽሑፍ ነበረ፡፡ ለምሳሌ ጳውሎስ ገና ሕፃናት ለነበሩት አዲዲስ ቤተክርስቲያኖች የጻፋቸውና ለወጣት አጋሮቹ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ የጻፋቸው መልክእቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

የክርስትና እምነት ግሪክ ቋንቋ ወደ ማይነገርባቸው ቦታዎች ሲስፋፋ እነዚህን መልእክቶችና ሌሎችም የቅዱሳኑ መጻሕፍት ክፍሎች በየቋንቋው መተርጎም አስፈላጊ እየሆነ መጣ፡፡ በምሥራቅ ላሉት በሲሪያክ ቋንቋ ለግብፃውያን በቆጵጢክ ቋንቋ በምዕራብ አውሮጳና በሰሜን አፍሪቃ ላሉት በላቲን እንዲሁም ለባርቤሪያውያን ነገዶች በጎቲክ ቋንቋ ይተረጎም ጀመር፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዘውም ስለሚሲዮን ሥራ ሲያነሱ እንደነ አቡነ ቄርሎስና አቡነ ሜቶዲየስ ያሉ የግሪክ መነኮሳት ለስላቪክ ሕዝቦች ወንጌልን እንደሰበኩ ለመጽሐፉ ቅዱስ ትርጉም እንዲመች በማሰብ ለቋንቋቸው ፊደል ቀርጸው ለጽሕፈት እንዳስገበሩት ተርከዋል፡፡››

እኒህ ሰው የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት ለሚሲዮን ወይም ለታላቁ ተልእኮ ሥራ ያደረጉትን ሁነኛ አስተዋጽኦ አንሥተው ሲናገሩ አንድ በዘመኑ የተለመደ አባባል ጠቅሰዋል ይህም፡-

‹‹መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበራት የወንጌል ተልእኮ ደንገጥሮች ናቸው፡፡›› የሚል ነው እነዚህ ማኅበራት በወንጌል እንቅስቃሴ መንገድ ጠራጊነትና ለቤተክርስቲያን ዕድገት ትልቅ ሚና እንደነበራቸው የሚገልጽ አባባል ነው፡፡

በመጀመሪያው ምዕተዓመት ውስጥ በአፍሪቃ የክርስትና መስፋፋትና የአፍሪቃዊ ቋንቋ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጎም ሥራ የተያያዘ እንደነበረ ደግሞ የቤተክርስቲያን ታሪክ ምሑር

የሆኑት ዶ/ር ማርክ ሾው እንደዚህ በማለት ያስረዳሉ።

‹‹በ300 ዓ.ም የግብፅ ክፍል ደግሞ ለየት ያለ ክርስትና እየተስፋፋ ነበረ። የገጠሩ ሕዝበ ክርስቲያን ቁጥር ጉልህ ነበረ። አትናቴዎስ እንደጻፈው በ303 ዓ.ም በቁጥር ከ 100 በላይ የሆኑ መነኩሳት በግብፅ ተሰራጭተው ነበር። ሃርናክ እንደገመተው ከሆነ በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የግብፅ ቤ/ክ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ አባሎች ነበሯት ከነዚህም የሚበዙቱ የዐባይን ወንዝ ተከትለው በተቋቋሙት የገጠር መንደሮችና ከተሞች ውስጥ የሚኖሩ ነበሩ።

የግሪክ ቋንቋ በማይናገሩት ሕዝብ መካከል ለመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ ትልቅ ገበያ ነበረ። ከ3ኛው ምታመት መገባደጃ ጀምሮ እስከ 8ኛው ምታመት ድረስ በየወቅቱ የትርጉም ሥራዎች በዋናዎቹ የቅጽጥ (ኮፕቲክ) ቋንቋዎች ማለትም ሳሂዲክ፣ ቦሃሪክ እና ባሽሙሪክ ልሳናት ቅዱሳት መጻሕፍት ተተርጎሞው ነበር። በእነዚህ አገርኛ ቋንቋዎች በተመሠሩት ትርጎሞችና በአጥቢያ አብያተክርስትያናት መበራከት ምክንያት የክርስትና እምነት በግብፅ አፈር ውስጥ ሥር እየሰደደ መጣ።››

ዘመነ ተሐድሶ በከፍተኛ ደረጃ የወንጌል እውነት የጎላበት እንቅስቃሴ እንደነበረ እናውቃለን። ይህም የእውነት ፍንዳታ መሠረቱ ቃለ እግዚአብሔርን የመረዳትና ያንንም የማስተጋባት ጸጋ ነበረ።

ሳሙኤል ኤስኮባር‹‹ወቅቱ የወንጌል መልእክተኛነት ነው A TIME FOR MISSION" ብሎ በጻፈው መጽሐፉ ይህንኑ ጉዳይ እንደዚህ ሲል ያብብራል።

‹‹በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱስን በየቋንቋዎቹ የመተርጎምና የማሠራጨት ቅስቃሴ የጠነከረበት ወቅት ነበረ ።የአዳሾቹ ትኃት የመነጨው እግዚአብሔር ሕይወትን፣ ተሐድሶንና ዕድገትን የሚሰጠው በመጽሐፍ ቅዱስ ቃሉ አማካይነት ነው ከሚለው ጥልቅ እምነት ነው----ቸርጉዊን እንደሚለው ‹‹ከሞላ ጎደል ሁሉም ዋና ዋናዎቹ አዳሾች ብዙ ልዩ ልዩ ተግባራት ትንፋሽ አሳጥተው ባተሌ ቢያደርጓቸውም የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ ውስጥ እጁን ያላስገባ አንድም አዳሽ አለነበረም፣ እንዲያውም አንዳንዶቹ ዋና ጥሪያቸው ይኸው ጉዳይ እደሆነ ይቆጥሩ ነበረ። ከሁለት ተኩል ምታመቶች በኋላ ያበበው የፕሮቴስታንት የወንጌል መልእክተኞች



(ሚሲዮናውያን) ቅስቃሴ ከሚሲዮን ሥራ አካሔድ ስልቶች ውስጥ አንዱ ዋናው ሥራ የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም እንዲሆን ያስቻለው ይኸው የቀዳሚቀዎቹ አዳሾች ያስተሳሰብ መንገድ ነበረ።››

በተለይ በአፍሪቃ ውስጥ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ ወንጌልን ከማስፋፋት ጋር ጥልቅ የኅብረተሰብ ለውጦች እንዲመጣም ያስቻለ መሆኑን ለማሳየት ኤስኮባር የታወቁትን የሚሲዮን ምሑር ዴቪድ ቤሬትን ይጠቅሷቸዋል።

‹‹መጽሐፍ ቅዱስ በአፍሪቃ ኅብረተሰብ ውስጥ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣቱን መናገር ከቶውኑ ማጋነን ሲሆን አይችልም። መጀመሪያ የተተረጎሙት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ለብዙዎቹ አፍሪቃውያን በቋንቋቸው የቀረበ የመጀመሪያ የታተመ ጽሑፍ ነበረ።ብዙ ፀረ ማይምነት ዘመቻዎችም የጀመሩት ከዚሁ የንባብ እፍታ በኋላ ነው።ወንጌል ማንበብ መቻል በብዙዎቹ ቤተክርስቲያኖች ዘንድ አንድ ሰው ከመጠመቁ በፊት ከሚቀርቡት መለኪያዎች አንዱ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ለአፍሪካውያን መተኪያ የሌለው የነገሮች ሁሉ ብይን መስጫ መርኅ ሆኖ ተገኘ። ከዚሁ የተነሣ ከቃሉ ውጪ ከሆኑ የምዕራባውያን ሃይማኖታዊ ቅኝ ገዥ አስተሳሰቦች ተላቆ መንፈሳዊ ነጻነትን የማግኘት ፍላጎት እየዳበረ መጣ።››

ዶ/ር ማርክ ሾውም በአፍሪቃ ውስጥ የካቶሊክንና የፕሮቴስታንትን ሚሲዮኖች አገልግሎት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ አንጻር ሲያመዛዝኑ እንዲህ ይላሉ።

‹‹በሰሜን አፍሪካ የነበረው የካቶሊክ ሚሲዮን አንድ ዋና ስሁተት የነዋሪውን የበርበር ሕዝብ ደቀመዝሙር ለማድረግ አለመቻል ነበረ። ‹‹በበርበር ጎሣ የሆኑ ክርስቲያኖች ቢኖሩም በበርበር ቋንቋ የተተረጎመ መጽሐፍ ቅዱስ አልነበረም ፤ በርበራውያን የሆኑ ካህናት / አገልጋዮችም አልነበሩም ፤ በበርበር ቋንቋ አንድ ጊዜም ስብከት ተሰምቶ አይታወቅም ነበር።››

አገራችን ኢትዮጵያ ቅዱሳት መጻሕፍት በጧቱ ከደረሳቸው አገሮች አንዷ ናት። በሕዝቧ ቋንቋ ተተርጎሞ የቀረበላት ገና ክርስትና አምስት መቶ ዓመት ሳይሞላው ነው።ያን ጊዜ በሰሜናዊ ኢትዮጵያ ክፍል መግባቢያ የነበረው የግዕዝ ቋንቋ የትርጉሙ ዓላማ ነበረ።

ማርክ ሾው የእግዚአብሔር መንግሥት በአፍሪቃ በተባለው

መጽሐፋቸው እንዳስፈሩት «በኢትዮጵያ የክርስትና እምነት መስፋፋት በተደጋጋሚ የሚጠቀሱት ሶርያውያን መነኮሳት ፤ተሰዐቱ /ዘጠኙ/ ቅዱሳን ጉልህ ተግባራት መካከል ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ የአገሬውን ሕዝብ ቋንቋ መማራቸው ፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ግዕዝ ቋንቋ መተርጎማቸውና እየዞሩ መስበካቸው ነበረ፡፡»

እነዚህ መነኮሳት የቅዱስ ጳኩሚስን ሥርዐተ ምንኩስና ማስፋፋታቸው ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን በጅቷል ወይስ ጎድቷል የሚለው ውይይት የሚያነጋግር ቢሆንም ለሃይማኖቱ መስራጨት ግን ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳይደረጉ የሚካድ አይደለም፡፡

ባለፈው አንደ መቶ ዓመት ገደማ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የወንጌል መልእክት እንደገና በቀረበበት ሂደት ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ አብሮት እንደተጓዘ መመልከት ይቻላል ፡፡ ብዙ ሕዝብ በሚናገርባቸው ሦስት ቋንቋዎች አማርኛ፤ ኦሮምኛ እና ትግርኛ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ መተርጎሙ የወንጌል ሥራ እንዲስፋፋ የቤተክርስቲያንም ጉልበት እንዲጠነክር ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

ለቀደሙት የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ አንባብያን መጽሐፍ ቅዱስን በአማርኛ ቋንቋ ተርጉመው ያዘጋጁት አባ አብርሃም የሚታወሱ ሰው ናቸው፡፡

በታላቅ ተጋድሎአቸውና በጠቃሚ ሕይወታቸው ታሪካቸው ሲወሳ የሚኖሩት የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ ኦነሲሞስ ነሲብ (አባ ገመቺስ) ለወንጌሉ ሥራ መስፋፋት ሁነኛ አስተዋጽኦ አበርክተው አልፈዋል፡፡ ይህንኑ የታሪክ ውልብታ «ደማቆቹ» በተሰኘው አዲስ መጽሐፍ ላይ ያሰፈረው ሰሎሞን ጥላሁን እንደዚህ በሚሉ ቃላት አስቀምጦታል፡፡

«የመጽሐፉ መጠናቀቅ ለብዙዎች ደስታን ከማጎናጸፍ ባለፈ ለተከታዩ የወንጌል ጉዞ የውስጥ ጥንካሬ ፤ በተለይም በገዛ ቋንቋው መጽሐፉ ለቀረበለት ሕዝብ የእውነትና የዕውቀትን ፈለግ በማመላከት ረገድ ዐቢይ የሆነውን ሚና ተጫውቷል፡፡»

አሁንም በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ የብሔረሰብ ቋንቋዎች የተደረገውና የሚደረገው የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጉም ሥራ ከወንጌሉ ቃል መስፋፋት፤ ከቤተክርስቲያን ተከላ ፤ ከደቀመዛሙርት ማፍራት፤



ከኅብረተሰብ ሁለንተናዊ ለውጥ ጋር የተያያዘ መሆኑን መመ ልከት ይቻላል፡፡

## እንግዲያው ምን እናድርግ?

እግዚአብሔር በሟቱ ቃሉ እንዲደርስን ለኢትዮጵያውያን ያደረገውን ቸርነት በምን እንመልሳለን; አንዱ መንገድ ይህን የምሥራች በገዛ ቋንቋቸው ሳልሰሙ ሰምተውትም በእምነት ሥር ሳልሰደዱ ብሔረሰቦቻችን በእጃቸው ሊይዙትና ሊረዱት የሚችሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የማቅረብ ጥረት ማገዝ ነው፡፡ ቃሉን ከተቀበልንበት ጊዜ ርዝመት አንጻር ሲታይ አንኳን በድንበራችን ላሉ በሩቅም ላሉት ሁሉ የብርሃን ወጋገን የማሳየት ኀላፊነት እንዳለብን ሊካድ የማይችል ሐቅ ነው፡፡

በአገራችን የሚታየውን የተቀየጠ ክርስትና ፤ የተጥበረበረ ነገረ መለኮትና የተሳከረ የሥነምግባር አካሔድ እንዴት ማረምና ማበጀት ይቻላል; እያንዳንዱ ምዕመን የሚያምነውን አጥርቶ ሊረዳ በሚችልበት በሚገባው ሁኔታ ቅዱሳት መጻሕፍት ካልቀረቡለት ከየጎዳናው የሚቦንነው አቧራ የእውነትን ንጹህ ውሃ ማደፍረሱ አይቀርም ፡፡ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ዛሬ «ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ስለተሰጠው እምነት መጋደል» የሚያስፈልግበት ወቅት ሆኗል ፡፡ ቤተክርስቲያን የጌታን ቃል ሳይበረዝና ሳይከለስ ለሕዝብ ለማድረስ ቃፌር መቆም አለባት፡፡ በዚህ ሙያ ለተሠማሩ ሁሉ ተገቢ ድጋፍ መስጠት አለባት፡፡

በኢትዮጵያ እየተበረታታ ባለው የብሔር ብሔረሰቦች ባህልና ቋንቋ የማዳበር ፖሊሲ ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲሰጥ መደረጉ የቋንቋ ጉዳይ ትልቅ ቦታ እንደተሰጠው ያመለክታል፡፡ ይህን አካሔድ ቤተክርስቲያን ለወንጌል ሥራ ለቤተክርስቲያንም ጥንካሬ በጎ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ልትሠራበት ይገባታል፡፡

እውነተኛና ብርቱ የክርስቶስ ቤተክርስትያን በእግሯ እንድትቆም የምራቸውን የሚሹ ሁሉ ስለቅዱሳት መጻሕፍት ትርጎም ጉዳይ ሊያስቡ ይገባል፡፡ እኛ ሁላችን ከጌታ ዘንድ ጥሪ ደርሶናል «አብ እኔን እንደላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ» መባላችን እንደ ክርስቶስ ትሥጉታዊ ወይም ሥጋኂኒነት ፤ ተሰሚ ፤ ተደማጭ መልእክት አቅራቢነት ዐደራ እንደተሰጠን ያመለክታል፡፡ ሁላችንም ተርጓሚዎች ነን፡፡

# ዙረት ወይስ ስምሪት?

ሰውን ሁሉ ምን ያዞረዋል? አርፎ አንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለምን አይቀመጥም? እንደ አበባ ቀሳሚ ንብ ወይም እንደ ቆሻሻ አጣጣሚ ዝንብ ከጸሎት ቤት ጸሎት ቤትን ከ"ቸርች" ወደ "ቸርች" ምን ያቅበዘብዘዋል? ዘዋሪስ እግሩን ካልታከተው ይዙር፣ ግን ሲመጡበት የሚያስተናግዳቸው፣ ሲሄዱበት የሚሸኛቸው የየቤተ ክርስቲያኑ አገልጋይ (መሪ) ይህን ሽርሽር ዝም ብሎ ይፈቅዳል? ወይስ በዚህ ፈጣን የለውጥ ዘመን እንደዚህ ዐይነት ጥያቄ መጠየቅ ራሱ ጅልነት ነው?

ዘመኑ ምንም ያህል ፈጣን ይሁን፣ ለውጡም ምንም ያህል ትንግርት ይሁን የሆንነውን ለምን ሆንን? እንዴትስ ልንሆን ይገባል? ብሎ ማለት ጅልነት ሊሆን አይችልም። በጉዳና ላይ የሚሮጥ ጉበዝ ሁሉ የትም ልድረስ ብቻ ሩጫዬን አታስቁሙኝ የሚል ከሆነ ምናልባት የልቡናው ጤንነት መጠየቅ ያለበት እርሱ ነው እንጂ ወዴት እንደምንሄድ መጠያየቅስ ጅልነት አይሆንም።

**እሺ ሰውን ሁሉ ምን ያዞረዋል?**

በውል የተሠራ ጥናት ቢኖርና ሰዎች ለምን የአምልኮ ስፍራቸውን (ቤተ ክርስቲያናቸውን) እንደሚለዋውጡ የተደረገ የምርምር ውጤት ቢቀርብልን የተሻለ እንነጋገር ነበር። ይሁን እንጂ እሱ



ተሰልቆ እስኪሠራ ድረስ ብለን ጉዳዩን አናነሣም አንልም። ከጋራ ትዝብቶቻችንና ከየራሳችን ልምዶች ተነሥተን መነጋገር እን ችላለን። ምእመናን (ወንጌላውያን በሆኑት አብያተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አማኞች በተለይ) ከነበሩበት ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላ የሚሄዱባቸው አያሌ ምክንያቶች አሉ።

- "እግዚአብሔር የሰጠኝን ጸጋ ልጠቀምበት አልቻልሁም፤ ሁልጊዜ ሌሎች ቦታውን ይዘው እኔን የኳስ ሜዳ ተመልካች አደረጉኝ፤ መተናፈሻ እፈልጋለሁ፤ በእኔስ ጌታ አይጠቀምም እንዴ?" የሚል ሮሮ አሰምተው ለማገልገል ክፍት ያለ በር ወዳገኙበት ቦታ ፈቀቅ የሚሉ ብዙዎች አሉ። አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም የራሳቸው ጉጉት ብቻ ሳይሆን አጠገባቸው ያሉ ባልንጀሮቻቸውም "በውስጥህ ትልቅ ራእይና ሸክም፣ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ይዘህ ለምን ጊዜ ታባክናለህ፤ ወጥተህ ቸርች ብትከፍት አብረን ልንሆን እንችላለን" የሚል ማበረታቻም አግኝተው የሚወጡ አሉ።
- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባሉ መሪዎች/አገልጋዮች መካከል ያለመግባባት ሲጠነክር፣ አይሎም ወደ ጠብና ረብሻ ሲዛመት፣ ችግሩን ለመፍታት ዐቅም ሲያንስ "ከነገሩ ጦም እደሩ" በሚል ዘይቤም፣ በርጋታ ጌታን የማመልኩበት ቦታ ለመፈለግ ሰዎች ቤተ ክርስቲያናቸውን ትተው ወደ ሌላ ቦታ ይሔዳሉ።
- "የቃሉ ራብ አንገበገበኝ፣ የመንፈሱ ውሃ ጠማኝ የኅብረት ፍቅር ናፈቀኝ። እዚህ ያለሁበት ይህን ማግኘት አልቻልሁም" በሚል የጠራ ውሃ፣ የበሰለ ምግብ ፍለጋ ደግሞ አባልነታቸውን ቀይረው ይሻላል ወደሚሉት ቤተ ክርስቲያን/ጸሎት ቤት የሚሔዱ አያሌ ናቸው።
- አብረውኝ ያሉት የእኔ ዐይነት ሰዎች አይደሉም፤ በዕውቀት፣ በብሔር' በቋንቋ፣ በኑሮ ደረጃ፣ በአመለካከት አንጣጣምም፤ የሚመስሉኝን ፈልጌ ብሔድ በነጻነት ሌላ ቦታ ጌታን ላመልክ እችላለሁ የሚል አስተያየት ይዘው ቤተ ክርስቲያን የሚቀይሩም አሉ።

እዚህ ከቀረቡት ምክንያቶች ውጪም ዝውውሩ በብዙ ዐይነት ሰበብ ሊፈጸም ይችላል። በጋብቻ ምክንያት፣ በመኖሪያ ቦታ

ለውጥ ምክንያት፣ በባልንጀርነት መሳሳብ ምክንያት፣ ጌታ አዲስ ቦታ እንድሔድ መርቶኛል በሚል ዐሳብ ወይም በሌሎች ብዙ ምክንያቶች ዙሪቱ፣ ዝውውሩ ቅያሬው ሊከናወን ይችላል።

እንግዲያው ዐይን ጨፍነን ከአንድ የማምለኪያ ሥፍራ ወይም ቤተ እምነት ወደ ሌላው መሔድ ፍጹም የማይገባ ነው ለማለት አንችልም፤ ወይም በተጻራሪው ከአንዱ ወደ አንዱ ከዚያም ወደ ሌላው መዘዋወር የየግለ ሰቡ መብት ስለሆነ በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም መነጋገር የለብንም ማለት አንችልም። ይልቁን የአዲስ ኪዳንን የቤተ ክርስቲያን እውነታ እያስተያየን የእኛን ዘመኑን አካሔድ መፈተሽ ተገቢ ነው እላለሁ። በዚህ ጠቃሚ ፍተሻ ውስጥ የበኩሌን ልወርውርና እንድንነጋገርበት በር ልክፈት።

የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን አንጡራ ማንነትና የአሠራሯን እንዴትነት፣ የተልእኮዋንም ባሕርይ አጥርቶ ሾለመገንዘብ የአብዛኛው ችግር መነሻ ሳይሆን አልቀረም።

## ግጥምጥም አካል ወይስ ዘራፊ ከዋክብት?

ክርስቶስ የሠራት ቤተ ክርስቲያን እርሱ ራስ የሆነላት የብልቶች ግጥምጥም ናት እንጂ፣ አንዳንድ አንጸባራቂ ከዋክብት ብልጭ ድርግም የሚሉባት የቴአትር መድረክ አይደለችም። እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ እየሰጠ፣ ሕዝቡን እንዲያገለግሉ እየሾመ የሚያቆማቸው የጌታ አገልጋዮች ማናቸው ትልቅ እንደ ሆነ ባምንም ምእመናንን እንደ እሳት ራት በዙሪያቸው የሚያሽከረክሩ፣ በየእንጥሽታቸው መብራት ድርግም የሚል ኅምላሎች መሆን አለባቸው ብዬ አላስብም። የእነርሱ ዋና ተልእኮ ይህን ባለብዙ ብልቶች አካል በጤና እንዲሠራ፣ ተገጣጥሞ ወደ አንዱ የተባበረ ግብ እንዲንቀሳቀስ እያንዳንዱ ብልት ራስ ወደሚሆነው ወደ ክርስቶስ እያደገ በኅብረቱ ውስጥ ሙሉነቱን እንዲያገኝ መርዳት ነው።

በቤት ዘይቤም የተነገረ እንደ ሆነ የቤቱ አለቃ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ስለዚህ የአባታችን ቤት ውስጥ ሁላችን ኀላፊነት፣ ተጠያቂነት፣ የሥራ ድርሻና ተሳታፊነት ያለን እንደሆንን ተገንዝበን አሁን ባለሁበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለሁት በጌታ ቸርነትና ጸጋ ነው፤ እዚህ ስለሚሆነው ሁሉ እኔም የራሴ አስተዋጽኦ አለኝ፤ የሚጠይቀኝም አለ፤ ለሰው ብዬ አልሰነብትም



ለሰው ብዬም አልፈናቀልም። ለአካሉ ደኅንነት ያስፈለኝን ሁሉ እሠራለሁ፤ ዋናው አዛዡ የእረኞች አለቃ መድኃኒቴ ነው የሚል ቁርጠኝነት ያስፈልገናል።

## ደማዊ ትሥሥር ወይስ ባሕላዊ ስምምነት?

*"... ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ደም አማካይነት ቀርባችኋል ... የሚለያየውን የጥል ግድግዳ ያፈረሰ ሰላማችን እርሱ ራሱ ነውና።" (ኤፌ. 2፥13-14)*

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብረን የምንጸልየው፣ ቃሉን የምንሰማውን ሰዎች ያስተሳሰረን ዋናው ነገር የባሕልና የቋንቋ የኑሮ ደረጃ ወይም የጓደኝነት ክር አይደለም። ከእነዚህ ውስጥ የትኛውም ነገር በራሱ የሚናቅ፣ የሚገፋና የሚጠላ ነው ብዬ አላስብም፤ ነገር ግን የአንድነታችን መሠረት ክቡር ደሙ ብቻ ነው። እነዚህን የመግባቢያ ወይም የመጣያ ሰበቦች ሁሉ ጥሶ የሚዘልቅ ብርቱ ትሥሥር ተበጅቶልናል። እኛ ሰለምንፈቃቀድ የሠራነው ማኅበር ወይም የአካባቢ ዕድር ሳይሆን ቤተ ክርስቲያን የእርሱ ደማዊ ኪዳን ያሰባሰባቸው ሰዎች ማኅበር ናት። እንግዲያው የባልንጀሮቼን ቋንቋ ታግሼ፣ ባሕላቸውን አክብሬ፣ ሰውን የማወቀው በሥጋው አቋም ሳይሆን በክርስቶስ ውስጥ ባለው ሥፍራ ነው ብዬ፣ የዘላለም ዕጣ ፈንታችን አንድ ላይ ነው ብዬ፣ በፍቅርና በማስተዋል አብሬ ልኖርና ላገለግል ተጠርቻለሁ። ይህ ጥሪ ብዙ ትዕግሥት ይጠይቃል፤ ብዙ ትሕትና ይፈልግብኛል። "ኤጭ ምንአባቱ ሌላ ቸርች ጠፋ እንዴ!" ብዬ ውልቅ እንዳልል አደብ ያስገዛኛል።

## የእኔ ጥቅም ወይስ የጌታ ተልእኮ?

"የትኛው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልሁን?" የሚለው ጥያቄ ቢያንስ ከሁለት አንጻር ሊመለስ ይቻላል። አንደኛው የበለጠ ጥቅም የማገኘው የትነው? ይህም ማለት የተሻለ ትምህርት፣ የተሻለ የአምልኮ ሥርዐት፣ የተሻለ የስብሰባ አዳራሽ፣ የተሻሉ ሰዎች የተሻለ የአስተዳደር ዐይነት፣ የተሻለ ...።

ሁለተኛው መንገድ እኔ እዚያ በመሆኔ የበለጠ ሊጠቀም የሚችለው ቤተ ክርስቲያን የትኛው ነው? ምን አስተዋጽኦ ላደርግ እችላለሁ? እኔ ላበጀው፣ ወይም ለዕድገቱ የድርሻዬን

ሳበረክትለት የምችል ቤተ ክርስቲያን የትኛው ነው? ምናልባት ከእነዚህ ጋር ተዛምዶ ሊጠየቅ የሚችለው ሌላ ጥያቄ ጌታ የት እንድሆን ይፈልጋል? የሚል ነው።

ለእኔም ለቤተ ሰቤም ሕይወት መታነጽ የሚበጀው የቱ ነው ብዬ ቦታ መፈለጌ ክፉ ባይሆንም በተልእኮ አስተሳሰብም ቤተ ክርስቲያንን መምረጥ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው። እኛ በአካል ውስጥ ያለን ብልቶች ባለጠቃሚ ሥራና ድርሻ እንደሆንን ካሰብን ምቾታችንን እየፈላለግን ብቻ ወገኖችን መጥቀም ችላ እንዳንል ያሰጋል። ወዲያውም ቤተ ክርስቲያን የእኛን ልዩ ልዩ ፍላጐቶች ማሟላት ያለባት የሸመታ ቦታ እንደሆነች ዐይነት እንዳናስመስላት ያሳስባል።

## እረኛ የሌሉ ጠባቂ ወይስ የሕዝቡ?

“ራሳቸውን ለሚያስማሩ እረኞች ወዮላቸው!” ያለው ነቢዩ ሕዝቅኤል ነው። ራስ ማስማራት ማለት ከበጎቹ የሚገኘውን ጠጉር እየሸለቱ ሱፍ መልበስ፣ ከሥጋቸው ጮማ በልቶ መወፈር፣ በእነርሱ መጠቀም ማለት ነው። በምትኩ በጐቹን ችላ ማለት፣ ሲሰበሩ አለመጠገን፣ ሲባዝኑ አለመመለስ፣ ሲጠፉ አለመፈለግ፣ ለአራዊት መብል ሲሆኑ ዳር ቆሞ መመልከት ማለት ነው።

ምዕመናን ከአንዱ ቤት ወደ ሌላው የሚያሂዙራቸው አንድም የጠኔ ብርታት ነው። ምግብ ይፈልጋሉ፣ ፍቅር ይፈልጋሉ፣ ሰማያዊ ርካታ ይሻሉ፣ ስምሪት ይሻሉ። ይህን ተገንዝቦ በትጋትና በትሕትና የማይጠብቅ፣ በየዐቅማቸው የማያሰማራ እረኛና አገልጋይ ባለበት ቦታ ወንድሞችና እኅቶች በየበሩ እየሾለኩ ቢወጡ፣ መንገድ ቢንከራተቱ እንዴት እንገረማለን? ኢየሱስ መድኃኒታችን ራብ ያጠወለጋቸውን አምስት ሺህ ሰዎች በመገበ ጊዜ በቡድን በቡድን በኀምሣና በመቶ እንዲቀመጡ ማዘዙ በሥርዐትና በቅልጥፍና አገልግሎቱን (ምገባውን) ለማዳረስ የሠራው ዘዴ ነው። ይህ የምድር እንጀራ ጉዳይ ቢሆንም ሰማያዊውም ምገባና ጥበቃ ስልት፣ ጥንቃቄ፣ ትጋትና ርኅራኄ የሚያሻው መሆኑን እናስተውልበታለን።

የአገልግሎት መንፈስና ጸጋ ያላቸውን ወንድሞችና እኅቶች ልብ ብለን ኀላፊነት እየሰጠን ማስማራት ለእነርሱም ለቤተ



ክርስቲያንም ዕድገት ዘላቂ መሠረት መጣል ነው። የዐዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ጥቂት ባለሙያዎች የሚራኮቱባት ሜዳ አይደለችም፤ ይልቁን ሁሉ በትክክል እየሠራ አካሉን ለማነጽ የሚገነባበት ቤት ናት። ጎሽ እያሉ እያበረቱ፣ እያረሙ፣ እያቀኑ፣ እያንዳንዱ ምዕመን የተልእኮው ሠራዊት ተሰላፊ እንዲሆን ማስቻል የአገልጋዮች ዋና ጥሪ ነው።

ይህን ሁሉ ካልን በኋላ ግን ይህ የምእመናንና የአገልጋዮች ቀኝ ግራ ፍልሰት ለምን ይህን ያህል ያሳስበናል? ቢባልስ የሆነው ይሁን ብለን ችላ ብንል ከባድ አደጋዎች ስለሚገጥሙን ነው።

- ዋናው አደጋ በዚህ የፍልሰት ጉዳና ላይ ብዙዎች በየጥጋ ጥጉ፣ በየመንገዱ ዳር ወድቀው የመቅረታቸው፣ እየከሱ የመጠውለጋቸው ተጠያቂነት በሌለበት ሁኔታ ከሚኖሩት ኑሮ የተነሣ ከእውነተኛው የክርስቶስ ደቀ መዝሙርነት የወጣ ሌላ ፍጥረት ሆነው ማደጋቸው ነው።

- የቤተ ክርስቲያን አካላዊ አንድነት እየሳሳ፣ ግርማዋ እየደበዘዘ፣ ሥልጣንዋም እየተረሳ፣ እንደ አንድ ተራ ድርጅት እየታሰበች በሕዝብ ዘንድ ከበሬታዋ እየጠፋ፣ ተሰሚነቷ እየከሰመ ቢሄድ የሁላችንም ሰቀቀን ነው።

- ባለማስተዋል በሚደረግ ፍልሰት የአገልጋዮች ልብ መድከሙ፣ ተስፋ መቁረጡ አንድ ሌላ አደጋ ነው፤ ምናልባት ከዚህም የተነሣ የእውነተኛይቱን ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገጽታ ያላስተዋሉ አገልጋዮች ፍልሰቱን ለማስቆም የንግድ ታክቲክ እንዳይጠቀሙም ያሰጋል። "እኛ ቸርች ጥሩ ኪቦርድ ቢኖር ኖሮ!"፣ "ከውጭ አገር ተናጋሪ ብናስመጣ ኖሮ!"፣ "ወለሉን በሥጋጃ ምንጣፍ ብንሸፍነው ኖሮ!" የሚሉ ዐይነት ታክቲኮች።

ጤነኛ ምክንያት የሌለው ዙረትና ፍልሰት በአገራዊ ተልእኮአችን ላይ የወንጌልን ሥራ ለመሥራት በምናደርገው የጋራ ጥረት ላይም ክፉ ጥላ ሊጥልብን ይችላል። እንደተጠራነው የልዑል እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሆነን ከመታየት ይልቅ ልዩ ልዩ ጥቅሞች የሚያናፏኍን የወንበዴዎች ዋሻ ከመሰልን እንዴት

## የወንጌል ጥሪ ምላሽ ያገኛል?

ቤቶቻችንን ልቦቻችንንም መፈተሻ ጊዜ ነው፤ እያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ ካለሁበት የጸሎት ቤት ወይም ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌው የምሄድበት ምክንያት ምንድነው? ብሎ ይጠይቅ። ራስ ወዳድነትና እብሪት፣ ግድየለሽነትና ብቀላ የሚገፋፉት ከሆነ የአዲስ ኪዳንን ቤተ ክርስቲያን ማንነት በውል አልተገነዘበም፤ ክብሯንም እንደ አልባሌ ነገር ቆጥሯል። ይህ ሰው ወደ ንስሓና ጸጋ ልመና ማቅናት ይሻለዋል። እንደኔው ደካማ ከሆኑ ሰዎች ጋር በመንፈስህ ብርታት የምናድግበትን ሰማያዊ ተሓድሶ ስጠን ቢል ይሻለዋል። በሌላ በኩል ደግሞ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት፣ ቡተልዕኮም ስሜት የሚንቀሳቀስ የሆነ እንደ ሆነ ማጣሪያው ውጤቱ ነው። አካሔዱ የምዕመናንን ሕይወትና የክርስቲያን አገልግሎትን እያፈረሰ፣ የወንጌልን ዕድገት እየገታ ነው? ወይስ ሕይወት እየገነባ? ለክርስቶስ አካል አንድነት ቁብ በሌለው መንገድ ኅብረትን እያፈረሰ፣ የወንጌል ጉልበት እያሚሰሰ ነው? ወይስ የወንጌልን መስክ እያሰፋ የአካልን ኅብረት እያሰመለመ ነው? መልሳችን የኋለኛው ከሆነ ለምን ቦታ ትቀይራለህ ብሎ መሞገት ያስኬደናል ወይ እያልሁ እጠይቃለሁ።

በአገራችን ያለውን የፍልሰት ርምጃ ልብ ብለን ስናጤን ከጤነኛውና ከትክክለኛው ምክንያት ይልቅ የታመመውና የተሳሳተው አካሔድ የሚበዛ ይመስለኛል። ስለ ቤተ ክርስቲያን ቆም ብለን መጠየቂያ ጊዜ ነው።

መሪዎች፣ አገልጋዮችና መጋቢዎች ሕዝባችንን በመጠበቅና በመንከባከብ ፈንታ በጅራፍ እያሳደድነው፣ በቸልታ ግልምጫ እየገረፍነው፣ በቡድናዊ ስሜት እያገለልነው፣ በጠኔ እየገደልነው፣ በሐሜትና በአግቦ አለንጋ እየቀጣነው፣ በጠብና ጭቅጭቅ እያደነቆርነው፣ በግፍ እየገዛነው ፍዳውን ስናሳየው ቤቱን ለቅቆ ቢባዝን የማንጠየቅ ይመስላችኋል?

የእረኞች አለቃ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይማረን፤ በጎች እንዴት እንደሚጠበቁም ያሳየን! የወዳጆቻችንን ምክር እንስማ፤ ብዙ የማይወዱንን ሰዎች ወቀሳም እንስማ፤ የምእመናንን ምክር እንስማ፤ ከሁሉ ይልቅ በቃሉ በኩል የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ እንስማ።



ቤተ ክርስቲያን ክብርት የጌታ ሙሽሪት ናት። ለዕድገትዋና ለውበቷ አብረን እንሥራ እንጂ አናጣጥላት፤ በሠርጉ ቀን በታላቅ ሐሤት ደስ እንዲለን አሁን በትዕግሥት እንሸላልማት።

## ወንጌላዊ ክርስትና ምንድነው?

መርዶም ሆነ ብሥራት ምክንያት ይሻል። ወይ አባትህ ሞተዋል ቁርጡን እወቀውና እረፈው፣ ወይም ሚስትህ ወልዳልሃለችና ፈንድቅ፣ ፎክር፣ ሽልል! ፈጣሪ "የምሥራች አለኝ" እያለ ማወጅ ከጀመረ ቆይቷል። "ወንጌል" የሚለው ቃል ትርጉሙም ይኸው ነው። መልካም ዜና የምሥራች ማለት ነው። እንግዲያው 'እግዚአብሔር ለአዳም ልጅ የሚነግረው መልካም ዜና ምንድነው?' ማለት ሲያሻን ነው።

በበደሉና በዐመፁ ከእግዚአብሔር የተጣላው የሰው 'ልጅ የት ልግባ?' እያለ ሲጨነቅ ተበዳዩ አምላክ ራሱ ክሶ መታረቂያውን በግ አርዶ 'ና ታረቀኝ' አለው። ያ የታረደ በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ይባላል። መታረቂያውም መንገድ እርሱን አምኖ 'መጣሁ ተቀበለኝ' የሚል ሙጥኝታ ነው። ባጭር ቃል የወንጌላውያን እምነት ለዚህ የእርቅ ጥሪ እሺ በማለት ላይ የተመሠረተ ነው።

ወንጌላዊ አማኝ ሆንኩ ስል ራሴን ለማትረፍ ሳደርገው የምችለው አንድም በጎ ነገር የለም፣ የጻድቁን አምላክ ሚዛን የሚያረካ አንድም መልካምነት እኔ ዘንድ አልተገኘም፣ ሁለንተናዬን በርኅሩኅ ጌታ ላይ እጥላለሁ ማለቴ ነው። "አዳም በበደለ መድኃኔዓለም ክሶ፣ ቆሟል ቀራንዮ ከለሜዳ ለብሶ" ብሎ የተቀኘው ማን እንደ ሆነ ባላውቅም እውነቱን ብሎአል።



የወንጌላውያን እምነት ጥሩ ሰው ለመሆን የሚደረግ የራስ በራስ ጥረት ሳይሆን፣ ከፍርድ ነጻ የወጣ ወንጀለኛ ነጻ ያወጣውን ጌታ በታላቅ ፍቅርና አክብሮት የሚያገለግልበት የምስጋና ሕይወት ነው። ይህ ምስጋና በእግዚአብሔር አምሳል ለተፈጠረ የሰው ልጅ ሁሉ አክብሮትና ፍቅርን፣ ለተቸገረ ሁሉ ቅን ርዳታን፣ ለተፈጥሮ ርኅራኄንና የኀላፊነት ስሜትን፣ ለሕዝብ መልካም ኑሮ ተገቢ አስተዋጽኦ ማድረግን ያካትታል።

አንድ ወንጌላዊ ክርስቲያን 'በክርስቶስ አምናለሁ፣ እግዚአብሔርን እወዳለሁ፣ ነገር ግን የማይመስሉኝን ሰዎች የመውደድ ግዴታ የለብኝም' ቢል መጽሐፉ እንዲህ ይለዋል፦ *"ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ እርሱ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን መውደድ አይችልምና" (1ዮሐ. 4፥20)* ተግባራዊ ፍቅር የእውነተኛ እምነት መግለጫ ነው።

ወንጌላዊነት ለወንጌል ቃል መገበር ነው። ወንጌላውያን አማኞች ለአስተምህሮና ለሥነ ምግባር ዋናው የችሎት አደባባይ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ሲሉ፣ ትውፊትና ባሕልን ሁሉ የየግሉ ሰቡም ተሞክሮ በዚሁ ባለሥልጣን ቃል ተፈትሾ የሚጸናው ይጸናል፣ የሚወድቀውም ይወድቃል ማለታቸው ነው። ክርስቲያን የታሪክ ሒደትን፣ የሰዎችን ነባራዊ ሕይወትና የኑሮ መስተጋብራቸውን አይክድም፤ ይሁን እንጂ ይህን ሁሉ በሉዐላዊ እጁ የሚመራ፣ ወደ ዓላማውም የሚያመጣው ኀያል ፈጣሪ አለ ብሎ ያምናል። ስለዚህ ጭንቅ ጥብብ ሲለው፦ *"እግዚአብሔርን ለሚወዱ፣ እንደ ሐሳቡም ለተጠሩ ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን" (ሮሜ 8፥28)* በሚለው የሐዋርያው ጳውሎስ መግለጫ ይጽናናል፤ ተስፋም ያደርጋል።

ይህ ወንጌላዊ አማኝ ግን ነገሩን ለዕውር ዕድል ሰጥቶ ቦዘን የሚቀመጥ ስነፍ አይደለም። የሥነ ፍጥረት መጋረጃ ሲከፈት የሚታየው በዕንቁ በተንቆጠቆጠ ዙፋን ላይ ተቀምጦ፣ ክምችቱ ብዛት የተነሣ እንቅልፍ አሸልቦት የሚያንኮራፋ አምላክ ሳይሆን፣ ሁሉን በሥርዐቱና በጥበቡ እየከሸነ በትጋት የሚፈጥር ብርቱ ሠራተኛ አምላክ በመሆኑ የአራት ዘፍጥረትን የመጀመሪያ ገጽ ያነበበ ወንጌላዊ ክርስቲያን ለስንፍናና ለዋልጌነት ቦታ ሊሰጥ አይችልም። ሥራ ክቡር ነው፤ የዕረፍት ጣዕሙ የሥራ ጣመን ነው። መጽሐፈ ምሳሌም *"የሠራተኛ ዕንቅልፍ ጣፋጭ ናት"*

ይላል፣ *"ትጋትም ለሰው የከበረ ሀብቱ ነው።"*

ወንጌላዊው ክርስቲያን የሚሠራው የራሱን አስፈልጎቶች (Needs) ለማሟላት ብቻ ሊሆን አይገባም። ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ ከመምጣታቸው በፊት ሌቦች የነበሩትን ሲመክር እንዳለው፣ *"ይሰርቅ የነበር ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ፤ ነገር ግን ለተቸገሩት የሚያካፍለው ነገር እንዲኖረው በገዛ እጆቹ በጎ የሆነውን እየሠራ ለማግኘት ይድከም።" (ኤፌ. 4፥28)።*

ክርስቲያንነት ክርስቶሳዊነት ነው ብሎ የሚያምነው ወንጌላዊው አማኝ ማንኛውም የሕይወት እንቅስቃሴው ክርስቶስ መሰልነትን እንዲያሳይ ይሻል። ቢበላ ቢጠጣ፣ ቢማር ቢመራመር፣ ቤተ ሰብ ቢመሠርት ወይም ነጠላውን ቢኖር፣ ቢሠራ ቢከብር፣ ቢታመም ቢፈወስ፣ ቢያገኝ ቢያጣ፣ በሁሉ የሕይወት መስክ ላይ ጌታውንና አዳኙን ለመምሰልና ለማስደሰት ራሱን ያዘጋጃል፣ ያሠለጥናል፤ የሕይወት ግቡም ይኸው ነው። *"አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፤ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ፤ በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ እርሱ ስለ ሁሉ ሞተ" ይለናል ሐዋርያው (2ኛ ቆሮንቶስ 5፥15)*

ወንጌላዊው ክርስትና ታሪክን የሚመለከተው ዞሮ የሚገጥም ክብ አዙሪት አድርጎ ሳይሆን፣ መነሻና መድረሻ ያለው መሥመራዊ ጉዞ አድርጎ ነው። የሰው ልጅ የኑሮ ዑደት ከልደት እስከ ሞት እያለ ቢደጋገምም የጠቅላላው ዓለም አካሔድ ግን በጠቢቡ አምላክ ንድፍ ተጀምሮ ወደ ማለቂያው የሚገሠግሥ በቦታና በጊዜ ዕሳቤ የሚገለጽ ውቅር ነው።

ራሱን በሦስት አንድነት የገለጠው ሥሉስ አምላክ የንድፍና የሥራው ሁሉ ማዕከልና መደምደሚያ ቁንጮ የዓለማውም መካታቻ ያደረገው መምህር ጌታና አዳኝ ሆኖ የተገለጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው። *"በዘመን ፍጻሜ ይሆን ዘንድ ያለው ሐሳቡ በሰማይም በምድርም ያሉትን ነገሮችን ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሥር ለመጠቅለል ነው።" (ኤፌ. 1፥10)።*

እንግዲያው ወንጌላዊ አማኝ ከሆንህ ሁሉ ነገር ሲሽከረከር ይኖራል እንጂ ምንም የሚለውጥ ነገር የለም ልትል አትችልም። ዘመኑ ፍጻሜ አለው። በዚያ ቀን ዘላለማዊው ዳኛ ብይኑን ይሰጣል። የየሰዉ ዕጣፈንታ የሚወስነው ግን ያኔ ሳይሆን



አሁን ለምሥራቹ ጥሪ በሚኖረው ምላሽ ነው። እዚህ ላይ የአጼ ቴዎድሮስ ጸሐፊ የነበሩትን የአለቃ ዘነብን ውብ ቅኔ መጥቀስ አግባብ ነው።

> *ሰማይ ከዚያ ላይ ሆኖ አንጓቦብን የሚኖር ከቶ ምንድን ነው? ቀን ፀሐይን ሌሊት ጨረቃንና ከዋክብትን ተሸልሞ ዘወትር እኔን እዩኝ እዩኝ እያለ ያደክመናል፤ ምነው የናቀን ድኾች ናቸው ብሎ ነው? ረሳው መሰለኝ የወትሮው እንዳይመስለው በላዩ የተቀመጠው ወንድማችን ነውና እርሱም ተመልሶ አሁን ይመጣል፤እንደዚህ የኮራ እንደ ሰም ለመቅለጥ ነው እንጂ ፊቱን እንዴት ያየው ይሆን፤ ኩራቱም ምድር አስለቅቆታል፤ ምን ይሆናል እንደሚያልፍ አያውቅምን። (መጽሐፈ ጨዋታ 47-48)*

ስለ ወንጌላዊው ክርስትና አንዲት ቅንጣት ብቻ ላክልና ዝም ልበል። ወንጌላዊ ክርስትና በመሠረቱ በቀዳሚ ደረጃ የሥነ ምግባር ሒተታ አይደለም፤ የታሪክና የባሕል የቅርስና የትውፊት ጉዳይም አይደለም፤ የተአምርና የድንቃድንቆች ርችትም አይደለም። እነዚህ ሁሉ በየስፍራቸው ተገቢ ሚና ቢኖራቸውም ክርስትና በቀዳሚ ደረጃ የግንኙነት ጉዳይ ነው። ግንኙነቱም ሰውም አምላክም ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው። የዚህ ሰው ተከታይና ተማሪ፣ የጌትነቱ ሎሌ፣ የአምላክነቱ ቀዳሽ አወዳሽ፣ የፍቅሩ ባልንጀራ መሆን ነው። እርሱ ራሱ እንዲህ አለ፦ *"እናንተ ደካሞች፥ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደእኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፥ ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፤ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና" (ማቴ. 11፥28-30)።*

# የሰባኪው ጥሪ

*"የሰባኪው ቀዳሚና እጅግ አስፈላጊው ተግባር ስብከቱን ማዘጋጀት ሳይሆን ራሱን ማዘጋጀት ነው።" ዶ/ር ማርቲን ሉይድ ጆንስ*

ሰባኪነት ታላቅ ጥሪ ነው። ወንጌላዊው ማርቆስ እንደጻፈልን መድኃኒታችን በአገልግሎቱ መጀመሪያ አካባቢ ለዚሁ አገልግሎት ሰዎችን ጠራ። "ወደ እርሱ እንዲመጡ ጠራቸው፤... ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ፣ ለስብከትም ይልካቸው ዘንድ... ሾማቸው ... ሥልጣን ሰጣቸው" (ማር. 3፥12-14)።

አንዳንድ ሰባኪ የንግግር ችሎታው ከፍ ያለ ሆኖ አድማጩን ሊያፈዝ ይችላል፤ ይሁን እንጂ ሰባኪው ዲስኩረኛ አይደለም፤ አንዳንዱ ሰባኪ የንግግሩ ለዛ የሚጣፍጥ ፈገግታ የሚጋብዝ ሊሆን ይችላል፤ ግን ሰባኪው ሕዝብ አጫዋች አይደለም፤ አንዳንድ ሰባኪ መላ አካሉ ይናገር ይሆናል፤ ግን ሰባኪ ተዋናይ አይደለም።

የወንጌል ሰባኪ ቀዳሚ ስምሪቱ የመለኮትን የምሥራች ማሰማት ነው፡፤ የመሰማት ፍላጎት የሌለው ተናጋሪ አንድም ልቡናው የተሳከረበት ብኩን ነው ። አንድም የገዛ ድምፁን የመስማት ፍላጎት ብቻ የጎለሰሰው ደካማ ነው።የሚነገር ሊሰማ ነው፤ በተለይየአንደበትም የጆሮም ፈጣሪ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር



የሚናገረው እንዲሰማ እንዲያሰማም ነው። (ሁለተኛው ሳልቶ ይነበብ) እግዚአብሔር መጀመሪያ ፣ ያኔ ለነበሩት ሕዝብ ተናገረ ። ያንጊዜና እዚያ ቦታ ቃሉ ሲነገር ለወዲያው ጉዳይ መልስ እንዲሆን ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ለዛሬና እዚህ ላለነው ሊተረጎም እንዲችል ተደርጎ ነው። የመንፈሱ አፍላቂነት ብቻ ሳይሆን የመንፈሱ አብሪነትም አለኝታችን ነው።እንግዲያው የእግዚአብሔር ቃል ለዛሬው ሰው የሚደመጥ እንዲሆን ተሰጥቷል። ይህ ሥራ የሕያው መንፈስ ቅዱስ ተግባር እንደሆን እየተገነዘብን እርሱ ደግሞ በሰው በኩል ለመናገር በመፍቀዱ ምክንያት የእኛንም ኃላፊነት እናስተንትናለን።ሀድን ሮቢንሰን የተባሉ የሰባክያን መምህር እንዲህ ብለው ጻፉ። *‹‹መጽሐፍ ቅዱስን አናስተምርም፣ ሰዎችን መጽሐፍ ቅዱስ እናስተምራለን እንጂ››* የተጻፈው ሁሉ ለአድማጩ ለአንባቢው መጻፉን ሊያስገነዝቡን ስለፈለጉ ይመስለኛል።መልዕክት ይዞ እስኪ ሰሚ ልፍጠርለት የሚል አካሔድ ሳይሆን ለእነዚህ ሰዎች ይህ መልዕክት እንዴት ይድረስ የሚለው ጭንቀት ዋጋ ሊሰጠው ይገባል።

ይህ እንግዲህ የመልዕክቱን ሐቀኝነት ፣ የመልዕክት አስተላላፊውን ኀይል ተቀባይነት እንዲሁም የመልዕክት ተቀባዮችን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘብ ባለሦስት አእማድ መዋቅር ነው።

## ሕዝቅኤላዊ ስብከት

ነቢዩ ሕዝቅኤል መጽሐፍ ጎራሽ ነው። እስቲጠረቃ እንዲበላ ተነገረው፤የእግዚአብሔርን መልእክት ተቀባይ ሆነ ‹‹ብላ ሆድህ ይሙላ››መባሉ መልእክትህ አይሳሳ፣ ልብ ብለህ ሰብሰብ፤ ይዘት ይኑርህ ሲለው ነው።መልእክተኛ ተብሎ መልእክት አልባ እንደመሆን አሳዛኝ ነገር የለም። ለዛሬው ሰው እንድንናገር የተጠራነው ሰዎች ሁሉ ይህን የዛሬው ሰው በቅርጽና በዘይቤ በቧልትና በጨዋታ እየሸነገልነው ልናቆየው አንችልም ያደረግነም እንደሆነ ብዙ ሳይቆይ ጠኔ ይጥለዋል። ከእግዚአብሔር ወቀሳና ሙገሳ ፣ የሰማይ ማስጠንቀቂያና ተስፋ እንዳች ይዞታ የማንሰጠው ከሆነ በራብ እንገድለዋለን።

ሕዝቅኤል የበላ ብቻ ሳይሆን፣ መንፈስ የገባበትም ሰው ነበረ። ‹‹መንፈስ አቆመኝ፣ መንፈስ ወደ ላይ አነሣኝ ›› እያለ ይመሰክርልናል። ዘመን የማይሽረውን ቅዱስ ቃል ለየዘመኑ እንዲሰማ የሚያደርገው መንፈስ ቅዱስ ነው ። መልዕክተኛውን

ሌላ ሰው አድርጎ ይለውጠዋል። አተያዩን ሕያውና ዐዲስ ያደርግለታል። በተውሶና በተናኮታዊ መንገድ (mechanicaly) ቃሉን እንዳይናገር ይልቁን በደራሽ ትኩሳትና ውስጥ በሚነካ ጉልበት እንዲያስተላልፍ ያግዘዋል ።

ነቢዩ፣ መጽሐፍ በልቶ ፣ መንፈስ ጠጥቶ ለመልዕክት አድራሽነት ሲንደረደር ይታያል።እንዲያውም እሱ ራሱ ዝግጁነቱን በሚያሳይ ሀረግ «በምሬትና በመንፈሴ ቁጣ ሄድሁ።» እያለ ይነግረናል እንደደረሰ ወዲያው ንግግሩን ግን አልጀመረም «ምርኮኞቹ መካከል በድንጋጤ ፣ ፈዝዤ ከእነርሱ ጋር ሰባት ቀን ተቀመጥሁ» ይለናል ይህ ቆይታ ፣ ይህ ድንጋጤ ፣ ይህ ፍዝነት ያለ ብል ሃቱ አልሆነም። ከመለኮት መልዕክት ይዞ በመለኮት ጉልበት በርትቶ ይምጣ እንጂ የሰሚዎቹን ዓለም በማወቅ ይበለጽጋል። ለዛሬው ሰው እንናገር ከተባለ የዛሬውን ሰው ከበባ ፣ የአስተሳሰብ ዝመት የኑሮ ድሩ የሚሽከረከርበትን የእንዝርት ዐይንት ማወቀው ይጠቅመናል ላም ባልዋለበት ኩበት እንዳንለቅም።

መልእክታችን እንዲሰማ የሚቻለውን ሁሉ እናደርጋለን ስንል፣ ሊሰሙ የማይወዱ፥ እንዲያውም ሌሎች እንኳ እንዳይሰሙ አልፍ ድንጋይ የሚፈነቅሉ ሊኖሩ መቻላቸውን አንዘነጋም። በሰማዕቱ በእስጢፋኖስ ንግግር ላይ እየጮኹ ጆሮአቸውን ደፍነዋል። (ሐዋ 7:57) መድሃኒታችንንም እንኳ ሁሉ ሰው በርጋታ አላዳመጠውም። ልዑል እግዚአብሄር ለነቢዩ ሕዝቅኤል "... ቢሰሙህ ወይም ባይሰሙህ ቃሌን ትነግራቸዋለህ ብሎታል። (ሕዝ2፤7) ያ ብርቱ ሰባኪ ሐዋርያው ጳውሎስም "እውነትን ከመስማት ጆሮአቸውን ይመልሳሉ:... አንተ ግን የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ።" (2ጢሞ 4: 3-4) እያለ ወጣቱን ሰባኪ ይመክራል።

ይህ 'ጆሮን ዳባ የሚያለብስ' ታሪካዊም አሁናዊም ሐቅ ፊታችን ላይ ተደቅኖ ቢኖርም በእኛ በኩል ከሚታይ ዝርክርክነትና ይዘት አልባነት የሚመጣውን አለመደመጥ ግን የትኛውም ሰበብ ዋስትና ሊሆነው አይገባም። 'የማያሳፍር ሠራተኛ' እንድንሆን «የተማረ ምላስ ሰጥቶኛል፤...ጆሮዬን ከፍቶአል።» እንዳለው የእግዚአብሔር ባሪያ ለማስሰማት ብቻ ሳይሆን ለመስማት ጆሮአችን ሊነቃ ያስፈልጋል። (ኢሳ 50:4-5)



እኛ አድማጮቻችንን፣ እንባቢዎቻችን፣ ወጣቶቻችን ልናስገርም አልተጠራንም፤ ልናዝናናም አልተጠራንም ፣ በረቂቅነት ልናስደምም አልተጠራንም የተጠራነው ልንነካ ነው፣ ልናሰማ፣ ነው (IMPACT [አስሚታ] እንዲኖር ነው) ቃለ እግዚአብሔር ለዛሬው ሰው ሊሆን ፣ ሊደርስ፣ ሊነካው ሊጠቅመው ይቻላል ወይ? እኛስ እንዴት ባለ መንገድ እናቅርበው?

1. የሰባኪው ማንነት

በክርስቶስ የተጠራው ሰባኪ ሁነኛ ማንነት አለው። በተለይ ሦስት ማንነቶቹ ጉልተው ይታዩኛል።

## 1.1 ሰባኪው እንደ ካህን:-

ሰባኪው በእግዚአብሔርና በሕዝብ መካከል የሚቆም፣ ለማስታረቅም የተላከ በመሆኑ የክህነት ጥሪው ልዩ ማንነት ይሰጠዋል። አማንያን ሁሉ ካህናት በሆኑበት በአዲስ ኪዳን አስተሳሰብ ሰባኪው የዕርቅ ወንጌልን በይፋ የማቅረብ ጉልሕ ሚና አለው። *"እኛ የክርስቶስ እንደ ራሴዎች ነን፤ እግዚአብሔርም በእኛ አማካይነት ጥሪውን ያቀርባል፤ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን በክርስቶስ እንለምናችኋለን።" (2ኛ ቆሮ. 5፥20፤ አመት)።*

እንደ ካህን ሰባኪው ታላቅ ርኅራኄ ሊያሳይ ይጠበቅበታል። በሚያዳምጡት ሰዎች ቦታ በልቡናው ተቀምጦ የሕይወት ውጣ ውረዳቸውን ሊያገናዝብ፣ ያነከሰው እንዲፈወስ እንጂ እንዳይናጋ በርጋታ ሊያቃና፣ አብሮ ሊያለቅስ፣ አብሮ ሊስቅ፣ የሻከረ ሊያለዝብ፣ የተስለመለመ ሊያነቃ የተሾመ ነው። እንደ ቴክኒክ ባለሙያ የጣራችንን አሸንዳ ለመተከስ ወናፉን ይዞ የሚዞር ሠራተኛ ሳይሆን፣ የሰው ሁለንተናዊ ጉዳይ የሚገደው ቅርብ ባልንጀራ ነው። ከምስባኩ ወዲያ ብቻ የሚኖር ባይተዋር ሳይሆን በአድማጭ ወንበር ላይ አብሮ ተቀማጭ ነው። ይህ የካህን ቅርበት የኢየሱስ ክርስቶስ ፈለግ ነው። ከሰማየ ሰማያት የወረደ፣ ተጨባጭ፣ ተዳሳሽ፣ እንጀራ በል፣ ሠርግ ሒያጅ፣ ሕጻናት አቃፊና ታንኳ ተሳፋሪ፣ የሆነ ጌታ የምንከተል ክርስቲያን ሰባኪዎች በአፀደ ሥጋ እንደማይኖር "ተመላላሽ የሙት መንፈስ" (Ghost) ድንገት መድረክ ላይ የምንከሰት እንዴት እንሆናለን?

*"እናት ልጆዋን እንደምትንከባከብ እኛም በመካከላችሁ በየዋሃነት ተመላለስን። የእግዚአብሔርን ወንጌል ብቻ ሳይሆን ሕይወታችንንም ጭምር ልናካፍላችሁ ደስ እስከሚለን ድረስ ወደድናችሁ።" (1 ተሰ. 2፥7-8)*

### 1.2 ሰባኪው - የእግዚአብሔር ነቢይ

ሰው መውደዳችን፣ ሰው መቅረባችን፣ ርኅራኄአችንና ባልንጀርነታችን ኖሮም መልእክት አልባ ከሆንን ክርስቲያን ሰባክያን አይደለንም። ሰባኪው ቁርጥ ያለ መልእክት ከሰማይ የተቀበለ፣ ዐዋጅ ነጋሪና መንገድ ጠቋሚ ነው። ምልክት የሚያሳይ ጉበኛ ነው። አልቃሻና ርኅሩኅ ጳውሎስ ነበልባላዊ መልእክት ሊያስተላልፍ የሚችል ነቢይነቱን አጣምሮ እናየዋለን። ዕንባንና መልእክትን ማፋታት ተገቢ ነገር አይደለም።

*"ከእናንተ ጋር በኖርኩባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ቀንና ሌሊት ዕንባዬን እያፈሰስኩ የቱን ያህል እንደ መከርኋችሁና እንደ ገሠጽኳችሁ አስታውሳችሁ በጥንቃቄ ኑሩ" (ሐዋ. 20፥31 ሕያው ቃል)*

ያለው ጠማማ ነገር የሚናገሩ ተኩላዎች ባሰፈሰፉበት ቤተ ክርስቲያን ወስጥ ነው። ሰባኪው ከራሱ ኪስ (ልቡና) እያወጣ የሚመነዝረው ረብጣ የለውም፤ ከእግዚአብሔር ቃል ጓዳዎች ወስጥ ያለውን መዝገብ ግን የማቅረብ ጥሪ ደርሶታል። ምንጭ አይደለም እንጂ መንደልደያ ቦይ ነው። ነቢይነትም ውሃው ሳይደፈርስ፣ ጉልበቱም ሳይቀንስ ለሰዎች የማድረስ ኑሮ ነው። የነቢይነት ጥሪ ትሥጉታዊነትን ግድ ይላል። መልእክቱ ሥጋ ነሥቶ የሚታይ ማድረግ አንዱ ሲሆን፣ በምንናገራቸው ሰዎች ኑሮና ሕይወት ውስጥ መግባት ደስታና ጣዕማቸውን መካፈል ሌላው ነው። ሕዝቅኤልም ጌታችን ኢየሱስም ያደረጉት ይህንኑ ነው።

### 1.3 ሰባኪው - ዐቃቤ ወንጌል

ሰባኪው መጋቤ ወንጌል ብቻ ሳይሆን ዐቃቤ ወንጌልም ነው። ዐቀበ፣ ጠበቀ፣ አቆየ፣ ያዘ፣ ተንከባከበ፤ ጥብቅና ቆመ በሚለው ፍቺ ዐቃቤ ሕግ፣ ሕግ ጠባቂ/ አስጠባቂ እንደ መሆኑ ዐይነት። የክርስቶስ ወንጌል በሰጋስነት የሚታወጅ፣ ለሁሉ የሚነገር ታላቅ



መልእክት ነው፤ ደግሞም፣ ሕፀፅ ጉድለት ሳይጠናወተው፣ ጤናው ሳይቃወስ ትኩሳቱ ሳይበረዝ መጠበቅ ያለበት የእውነት ክምችት ነው።

*"ከእኔ የተማርከውን እውነት በክርስቶስ ከሚገኘው እምነትና ፍቅር ጋር አዋሕደህ እንደ መመሪያህ ያዘው፤ በዐደራ የተሰጠህን አገልግሎት [መልካሙን ዐደራ] በውስጥህ ባደረው መንፈስ ቅዱስ ኃይል ደኅና አድርገህ ጠብቀው።" (2ኛ ጢሞ. 1፥2-4 ሕያው ቃል)*

ሐዋርያው ጳውሎስ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ እውነት ሰባኪ፣ እውነት ሰጪ፣ እውነት ናኚ፣ ተንታኝ ነበረ። ይሁን እንጂ የእውነት ጠበቃና ተሟጋችም ነበረ። ለቆሮንቶስ ምዕመናን *"እንደ ንጽሕት ድንግል ለክርስቶስ ለማቅረብ ለአንድ ባል አጭቻችኋለሁና ... ልቡናችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ካላችሁ ቅንነትና ንጽሕና እንዳትወሰዱ እሠጋለሁ። ..." (2ኛ ቆሮ. 11፥2-4 አመት)* እያለ ጭንቀቱንና ተጋድሎውን ይገልጻል።

ቤተ ክርስቲያን ገና ከመወለዷ፣ ወንጌልም ገና ከመታወጁ ጀምሮ የነበረው ይህ ገብግብ እስካሁን እንደተፋፋመ ነው። ሰባኪው በዚህ መንገድ ንቁና ቆፍጣና ሊሆን ግድ ነው። *"ለእነዚህ ሰዎች ለአንድ አፍታ እንኳ አልተገዛንላቸውም፤ ይኸውም የወንጌል እውነት ከእናንተ ጋር ጸንቶ እንዲኖር ነው።"*

እነዚህን መለዮዎች ሰባኪው አመጣጥኖና አዋሕዶ መኖሩ ፈር እንዳይለቅ ይረዳዋል። እንግዲያው ሰባኪው የክህነት፣ የነቢይነትና የዐቃቤ ወንጌልነት ጥሪ አለው።

## II. የሰባኪው ባሕርይ

ጳውሎሳዊ ምክር ለሰባኪዎች - ከ2ኛ ጢሞቴዎስ

ጢሞቴዎስ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሰባኪና መምህር ሆኖ መሪ አገልጋይ ነበረ። በዕድሜና በልምድ የሚበልጠውና የሚወደው ሐዋርያው ጳውሎስ የጻፈለት ደብዳቤ ሁለት ሺህ ዓመታት ቢያስቆጥርም ለዛሬ ዘመን ሰባኪዎችም ሁነኛ መልእክት አለው። የተናገራቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች በጨለፍታ ከየአናቅጹ እየቀዳን እንቅመስ።

ከብዙ ምክሩ መካከል ዐሥር ዋና ዋና ጉዳዮች ባጭሩ እጠቅሳለሁ:-

1. እውነተኛነት/ቅንነት (1፥1-6)

ሰባኪው አንድ ሰው ብቻ ሊሆን ተጠርቷል፤ ሁለት ወይም ዐሥር ዐይነት ባሕርይ፣ የውስጥና የውጭ አልባሳት፣ እንዳመቺነቱ የሚቀያየር አሚላጭ ሰብእና ሊይዝ አልተፈቀደለትም። የልዑል እግዚአብሔር ዐሳብ፣ ተሸካሚ የመልእክቱ አድራሽ ሆኖ በሰዎች መካከል የሚራመደው ሰባኪ አንደበቱ ብቻ ሳይሆን ልቡናውም ቀላማጅ እንዳይሆን መጠንቀቅ አለበት። ሰዎች ከትንግርታዊ የንግግር ችሎታ ይልቅ እውነተኛነታችንን ማወቅ ይፈልጋሉ።

‹‹ግብዝነት የሌለበት›› ንጽሕ ሕሊና፤ መኖር የአገልጋዩ መሠረታዊ አቋም ሊሆን ይገባል ። በዚህ መሠረት ላይ ብቻ ነው ዘላቂ የሰባኪነት አገልግሎት የሚገነባው።

2. ድፍረት/እምነት (1፥7-12)

የሰባኪው ጉልበት የንግግር ችሎታው ወይም ዝነኛነቱ አይደለም ጉልበቱ ነፍስ ጠርጎ የሚወስደውን ቀጥቃጣ ሰው እንደ ሌላ ሰው አድርጐ የሚለውጠው ብርቱው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። የማይነጥፍ የኃይል ምንጩ እርሱ ነው። ደግሞም የትም ቦታ ቢነገር የማያሳፍረው «ሕይወትና ኢመዋቲነትን ወደ ብርሃን የወጡበት ቅዱስ ወንጌል ነው። ስለዚህ ክርስቲያን ሰባኪ ርኅሩኅ፣አዛኝና ታጋሽ ሆኖ የራስ በራስ መግነን ሞቅታ ሳይሆን የሰማይ ኀይል የሚገለጽበት ሰው መሆን እንዳለበት የማይጠያይቅ እውነት ነው። *“የጌታ መንፈስ በኔ ላይ ነው እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛል”* ያለው ሰባኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

3. ትምህርታዊ ጤንነት (1፥13-14)

ሰባኪው የአካሉ ጤና መጠበቁ ለዚህ አገልግሎት የተሰናዳ ያደርገዋል። ከዚህ የበለጠ ግን የትምህርቱን ጤና ማረጋገጥ ዋና ተግባሩ ነው። “ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠ [የተጠናቀቀ]” ትምህርት/እምነት ያለን ሰዎች ነን(ይሁዳ1-3)። ይህ ትምህርት ግልጽ ንድፍ (ቢጋር) አለው። ያንን ተከትሎ እያጸኑ፣ እያፍታቱ መሔድ፣ ከብርዝ ድልዝ መጠበቅ ሥራችን ነው። “የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን” ብለው በግድግዳቸው ላይ ለጥፈው



እያደር ግን በዝናብ ውሽንፍር ፊደሉ ተጠርጎ “እንሰብካለን” የሚለው ብቻ እንደቀረበት ቤተ ክርስቲያን ሰዎች እንዳንሆን ትምህርታችንን ማጥራት ይገባናል።

4. ባልንጀራ ፈላጊነት/ሰብእዊነት (1፥15-18 እና 4፥9-18)

ሰባኪው ሰው ነው። ስሜቱ ከፍ ዝቅ የሚል፣ ኀጢአት በየደጃፉ የሚተናነቀው፣ አንዳንዴ የሚሸነፍ፣ በሰዎች አይዞህታ የሚበረታ፣ በሰዎች ወቀሳ የሚከሳ ሥሥ ፍጡር ነው። አንዳንድ ቀን ከሰማይ የወረደ አዲስ መልአክ ሆኖ ቢያብረቀርቅም፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከመድረኩ ወርዶ መደበቂያ ፍለጋ የሚሸሽበት ሁኔታ ውስጥ ይገባል፤ እና ይህ ፍጡር ሰው ነው። ስለዚህ የሚያጽናኑት፣ የሚገሥጹት፣ የሚያጫውቱት፣ የሚያመራምሩት ወዳጆች ያሻዋል። ሰባኪው ጳውሎስ ምንኛ ፈለገ?! *“ሁሉም ተውኝ … አንተ ቶሎ ናልኝ”* ብሎ ጓደኛ የለመነ ሰው ነው።

5. ትጋት (2፥1-7)

ለሰባኪው ትጋት ሦስት ሞዴሎች ቀርበውለታል። አንድ ብቻ ዓላማ ያለው ወታደር፣ በሥርዐት (ዲሲፕሊን) የታነጸ አትሌት እና በትዕግሥት የሚደክም ታታሪ ገበሬ።

የሰባኪው አንድ ዋና ፈተና ስንፍና፣ ስልቹነት፣ ታካችነት በመሆኑ ይህን ባሕርይ በጊዜ መገንባት የተዋጣ ሥራ እንዲሠራ ያስችለዋል። በጸሎት ሕይወቱ፣ በቃሉ ንባብና በጊዜ አጠቃቀሙ ሁሉ ከፍተኛ ዲሲፕሊን የሚጠበቅበት ሰው ነው።

6. ጽናት (2፥14-19)

የምንኖርበት ዓለም የተናጋ ዓለም ነው፤ ሁሉም ነገር ረጋ ሠራሽ ነው። የዘመኑም ታወቂ መልክ ጽኑ መልክ ማጣት ነው: : ሰባኪው የጽኑነት፣ የብርቱ አቋም ምሳሌ ሊሆን ተጠርቷል። ለራስ ብቻ አይደለም፤ ጳውሎስ እንዳለው “ለተመረጡት” ሲልም መጽናት ይገባዋል። በውስጣዊ ማንነቱ፣ በፍቅሩና በትምህርቱ በፈተና ውስጥ አልፎ የጸና ሲሆን ፍርክርኮች ወደርሱ ይጠጋሉ፤ ልባቸው ያመነታ ይደገፋሉ።

## 7. ልህቀት/ልቅና (2፥14-19)

የብዙዎቻችን ልማደኛ ፈተና ስብከታችንን "እንደ ነገሩ" ማድረግ ነው። በተለይ ለረዥም ጊዜ የሰበኩ ወይም ታዋቂ የሆኑ ሰባኪዎች አንድ በሽታ "ይድረስ ይድረስ" ነው። ጳውሎሳዊው ተግሣጽና ምክር እንዲህ ይላል፡፡ *"እንደሚያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ የተመሠከረለት ሠራተኛ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ።"* ጥንቅቅ ያለ ሥራ፣ ጥንፍፍ ያለ ተግባር ይታይብህ እንደ ማለት ነው።

የልቅና አስተሳሰብ ጥሩነቱ ፉክክሩ ከሌሎች ጋር ሳይሆን ከራስህ ጋር መሆኑ ነው። ለአንተ በተሰጠህ ጸጋ መጠን ተገቢውን ጥረት እስከ መጨረሻው የማድረግ ጥሪ  ነው። እንግዲያው የክርስቶስ ወንጌል ሰባኪ ወደር የሌለውን ክርስቶስን ለሰዎች ያስተዋውቃልና በማንኛውም ረገድ የሚያደናቅፈውን ዝርክርክነት ሲዋጋ ይገባዋል። ስብከቱን በብርቱ ጥናት አዘጋጅቶ አቀራረቡን በግልጥነትና በሳቢነት ሊያበጅ ይጠበቅበታል።

## 8. ሕይወታዊ ዝግጁነት (2፥20-26)

ከስብከት ዝግጅት ይልቅ የሰባኪ ዝግጅት የበለጠ ሥራ እንደ ሆነ ዐውቆ የሕይወት ግንባታ ላይ ማትኰር ለእግዚአብሔር የተመቸ ዕቃ መሆን ነው። ርምጃችንን የሚያሳድፉ ስንት አዋራጅ ነገሮች እንደሚያደቡብን እናውቃለን። ለጐልማሳው ለጢሞቴዎስ የተሰ ጠው ምክር፣ ራሱን በንጽሕና እንዲጠበቅ የሚያሳስብ ነው። ጌታ በፈለገው ጊዜና ቦታ አፈፍ የሚያደርገው ስንዱ ዕቃ እንዲሆን።

## 9. ባለ ልክነት (3፥1-17)

ይህ ዘመን የሥነ ምግባር መለኪያው የተቃወሰበት ነው። እንዲያውም "ልክ የሚባልስ አለ እንዴ?" እያለ እየጠየቀ ነው። በዚህ "ልክ የለሽ" ሞገድ ውስጥ ስንኖር እንደ እግዚአብሔር ሰውና አገልጋይ መለኪያችን ምንድነው? ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የራሱን ሕይወት አካሔድ እያሳየ ጽኑና የማይለወጠውን ሕያው የሆነውን የቅዱስ ቃሉን ልክ ያቀርብለታል። ጎርፉ የቱንም ያህል ዝቃጭ እያግተለተለ ቢያልፍ አንተ ግን ማጥለያ አለህ ይለዋል። እኛስ ቢሆን ሌላ ምን አስተማማኝ ሚዛን አለን?



## 10. ተጠያቂነት (10፥1-2፤ 6-8)

ለመሆኑ ሰባኪው ይጠየቃል ወይ? እንዴታ! ከሁሉ በላይና በፊት እንዲሰብክ በላከው ጌታ ቅጣትም ሽልማትም በሚሰጠው ልዑል ዳኛ መጠየቁ የማይቀር ነው።

*"በእግዚአብሔር ፊት፣... በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ባለው በክርስቶስ ሰዎች ፊት፣ መንግሥቱንና መገለጡን በማሰብ ... ዐደራ እልሃለሁ"* እንዴት ብርቱ መማጠኛ ነው! እንድንሰብክ የላከን እግዚአብሔር በየዕለቱ በመንፈሱ አማካይ በኋለኛው ቀን ደግሞ በይፋ ይጠይቀናል። የጽድቅ አክሊል ተስፋ እየታየን የምናገለግል ቡሩካን ነን።

## III. ምስባካዊ ሥነ ምግባር ·

ሰባኪው በአብዛኛው የሚቀረጸው፣ የሚታነጸው መናገሪያው መድረክ ወይም ምስባኩ ዘንድ ሳይመጣ በፊት ነው። ወደ ምስባኩ ከመጣ በኋላ ግን የሚያደርገው እያንዳንዱ ድርጊት፣ የሚላበሰው ማንኛውም ሰብዕና፣ የሚያንጸባርቀው የስሜትና የዕተያይ ነፀብራቅ ለጸጋ መተላለፍ የተመቸ ጐዳና አለዚያም ማለፊያ ገቺ ደንቃራ ያደርገዋል። ክርስቲያን ሰባኪ የሚጠበቅበትን የሥነ ምግባር ዐይነት ክብዙ በጥቂቱ አናንሣ።

### 1. አክብሮት

"አወቅሁሽ ናቅሁሽ" ያለብልሃቱ አልተተረተም። ብዙ ልምድና የረዥም ጊዜ አገልግሎት የጌታን መድረክ እንዳናከብር እንቅፋት ሆኖብን እንዳይሆን ያሠጋል! ክርስቲያን ሰባኪ ቢያንስ ሁለት ነገሮች ሊያከብር ይገባል፡-          - ቃሉንና ሕዝቡን። ወንጌሉን ልናከብር ይገባል፤ የጌታችን ቃል ነውና፤ ከነ ስሙ "የክብሩ ወንጌል" ነው። "እንዴት እናከብረዋለን?" የተባለ እንደሆነስ? በበቂ በመዘጋጀት፣ በአግባቡ በመተርጐም፣ ለመልእክቱም በመታዘዝ።

-አድማጮችን ማክበር ይገባናል። እግዚአብሔር አክብሮ አስቦ መልእክት የላካቸው ሕዝቡ ናቸውና ልንወቅሳቸው፣ ልንገሥጻቸው የሚያስፈልግ እንኳ ቢሆን በማን አለብኝነት ልንሰድባቸው ግን አልተፈቀደልንም። ለግማሽ ሰዓትም ይሁን ለአንድ ሰዓት እኛን በጥሞና ማዳመጣቸው ራሱ ትሑታን ሊያደርገን ይገባል።

የእኛን ማንነት ፊኛ የሚነፉ ባሮችም እናድርጋቸው፡፡ ምላሻቸው ቃሉ ልባቸውን በነካው መጠን እንጂ እኛ በወተወትናቸው ልክ አይሁን፡፡ ከዚህ ሌላ ደግሞ ከሌላ እምነት ክፍል የመጡ አድማጮችን ገና መልእክቱን ሳይሰሙ ተደናቅፈው እንደይቀሩ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል፡፡

## 2. የእግዚአብሔርን ቦታ ተክቶ ስለመሥራት

እኛ ሰዎች ነን እንጂ አማልክት አይደለንም፡፡ በምስባኩ ላይ እኛ በመውጣታችን አሁን ልዩ ድንቅ እንደሚደረግ ደጋግመን ማወጅ የልዑል ፈጣሪን ቦታ ተክቶ ተዋናይ መሆን ይመስላል፡፡ በሰው ልቡና ውስጥ በጐ ጉጉት መፍጠር ቢያሻም ያለ ልክ የተጋነነ ጥበቃ መጫር በሚፈቅደው መጠንና ጊዜ የሚሠራውን መንፈስ ማሳዘን አይሆንም? ያልነው ነገር ባልተፈጸመ ጊዜ በአድማጮች ላይ መፍረድ ልዩ ልዩ ሰበቦችም መስጠት አገልግሎታችንን ዝቅ ያደርገዋል፡፡ ሕያው እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ይምጣና ያስደንቀን፡፡ እኛ ራሳችን እኮ ከአድማጩ ጋር ምሕረቱን ተጠባባቂዎች ነን፡፡

## 3. ሐሰት ስለመናገር/ስለማጋነን

አንዱ የሰባኪ ፈተና ለተደማጭነት በመጓጓት እውነታን ከመሥመር አስወጥቶ ማጋነንና ያልተጣራ ነገርን እንደርግጠኛ ነገር ማቅረብ ነው፡፡ ማንም ሰው መዋሸት የለበትም፤ ይልቁን የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ የሚናገር የወንጌል አስተማሪ በዚህ ጉዳይ መጠንቀቅ ይገባዋል፡፡ ስለ ራሱ ታሪክ፣ ስለሚጠቅሳቸው ሰዎች፣ አሁን ስለተሰማው ስሜት እቅጩን ብቻ ቢናገር ሕሊናውን ከጸጸት፣ አድማጩቹንም ከስሕተት ያድናል፡፡

## 4. ትርጉማቸው ከወየበ ድግግሞሽ መጠበቅ

ልማድ እያስገደደን በከንቱ የምንላቸው ብዙ ድጋሞች አሉ፡፡ በየራሳቸው በጣም ጥሩ የሆኑ፣ ያለቦታቸው ግን የሚያታክቱና ትርጉም የሌላቸው ቃላት፣ ሐረጎች፣ መፈክሮች በዝተዋል፡፡ ለምሳሌ "ኢየሱስ ጌታ ነው!" የሚል ሰው ማለቱ ቢሆን እን ዴት ጥሩ ነው! አንዳንድ ጊዜ የሚያናግረን ጥልቅ ግንዛቤ ሳይሆን ደመነፍሳዊ ልማድ ነው፡፡ የከንቱ ድግግሞሽ ክፋቱ ክቡራን የሆኑትን አሳቦች ርካሽ የማድረግ አቅሳይነቱ ነው፡፡ "ነብር መጣብኝ" እያለ ሲያታልል የኖረው እረኛ የእውነት ነብር



የመጣበት ቀን የሚደረስለት እንዳጣው ዐይነት ማለት ነው፡፡

## 5. ታይታንና ስንቱታን ከመናፈቅ መሸሽ

የሁልጊዜ ግብግብ የሚሻ፣ የሰባኪ አንድ በሽታ ከመጠን በላይ ስለ ራሱና ሰዎች እርሱን ስለሚመለከቱበት ግምት ያለው መብሰልሰል ነው፡፡ ከስብከቱ በፊት፣ በዚያን ጊዜና በኋላ ዋናው ትኩረት ቃሉና አድማጮቹ የሆኑለት ሰባኪ የታደለ ነው፡፡ ይህን ፈተና በመንፈሱና በቃሉ ድጋፍ ዘወትር ማስገበር አለብን፡፡ "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክም" ብሎ እንዳለ ሐዋርያው ጳውሎስ፡፡ የዚህ ፈተና ዋና መሣሪያ ደካማ ነጥባችን ሳይሆን ብርቱ ጐን የምንለው ዐቅማችን ነው፡፡ ብርታታችንን ያለ ልክ አደባባዩ ላይ የማስጣት፣ የማብረቅረቅ ስበት ያስቸግረናል:: ሆኖም ይኸው ብርቱ የተባለ ነገር መሰናከያችን መሆኑ ያሳዝናል፡፡ ልክ እንደ አቤሴሎም ውብ ፀጉር ከጥሻ ጋር አጣብቆ ያስወጋናልና በንቃት መከታተል ተገቢ ነው፡፡

## 6. የሌሎችን ዘይቤ ሳያስተውሉ ከመቅዳት መቆጠብ

የፈጠራ ችሎታው አስገራሚ የሆነው ፈጣሪ ልዩ ልዩ ሰዎችን ፈጠረ፡፡ ወደ ፊት በላቦራቶሪ እንደምንባዛ የሚያስፈራሩን ሊቃውንት ሁለንተናው ያው የሆነ የሰው ምርት እንደ ፔፕሲ ኮላ ጠርሙስ ባንድ ቅርጽና መልክ እየተፈበረከ ይወጣል ይሉናል፡፡ ያን ለሚሉት ሰዎች ትተን ስጦታውን እርሱ እንደ ወደደ እያካፈለ የሚሰጠውን ቅዱስ መንፈስና የራሱን ልዩ ልዩ አሠራር በሰው ውስጥ የሚገልጠውን ልዑል እግዚአብሔርን እናስብ፡፡ የምንወደውንና የምናደንቀውን ወይም ሰዎች የሚያሞግሱትን ሰው በባሕርይ መምሰል ቢያስፈልገን እንኳ በስብከት ዘዬ ግን የግድ እርሱን መምሰል አለብን አንልም፡፡ በሁሉ የሚሠራ እግዚአብሔር እንደሚቀርጸን መንቀሳቀስ ይሻላል፡፡ በመዝሙርም በስበከትም ኦርጂናሊቲ እየጠፉ ቅጂ እየተበራከተ መሄዱ እያንዳንዱ ሰው ከጌታው ዘንድ ተቀብሎ በራሱ ማንነት ውስጥ የሚፈስሰውን ጸጋ ለማካፈል አለመትጋቱ ይሆናል እላለሁ፡፡

ሌሎችስ ...?

# መፍትሔ ቃላት

ሁነት - የመሆን ነገር ወይም የሆነ ነገር happening, event

መስተጋብር - አብሮ በመኖር የሚመጣ ስጥ-ተቀበል ግንኙነት interaction

መፍረግረግ - መለማመጥ

ሚዲያ ዐበድ - መገናኛ ብዙኃን የሕይወት ማእከሉ የሆነ media mad

ምስፍና - ግዛት - መስፍንነት - አገዛዝ

ምክኑያዊ (አመክንዮ) - ምክንያት ጠያቂ፥ ምክንያት አቅራቢ ያለ ማስረጃ የማይገለጥ - የአሳብ ስሌት reasonable — logical

ሥር አጥባቂ - ሥር ነቀል ለሚለው ተቃራኒ ጥግ - የነበረውን ሥሩን እንዳይለቅ የሚጠብቅ conservative

ስርጥ - አቋራጭ - ውስጥ ውስጥ የሚሄድ መንገድ - ዋናው ጎዳና ሳይሆን ንዑስ መንገድ

ሽረር አለ - ፈቀቅ አለ ፥ በድንገት ፈንጠር ብሎ ሔደ

ሽነቆጠ - ገረፈ ፥ አለንጋ በገላ ላይ አሳረፈ ፥ አነቃ

ቀቢድ - እጦት፥ ቀቢጸ ተስፋ - የተስፋ መሟጠጥ despair



ቃፊር - ዘበኛ ፥ ጠባቂ

ቅንብብ - ዳር ድንበሩ የተለካ ውቅር ፥ ማዕቀፍ - framework

ቤዝዎት - የመቤገርት ተግባር redemption

ትሥጉት - ሥጋ መሆን - መለኮት ሰው የመሆኑ ምስጢር

ተሸበበ - ተለጎመ ፥ ተከፈፈ ፥ ከንፈሩ ተሰበሰበ

ቱማታ - ድብልቅልቅ - የጠብ ሁካታ፥ ጫጫታ

ትምምታ - ሞገዳዊ ጉዞ። ተመመ - አንድ ላይ በብዛት ሆኖ ተጓዘ።

ትወራ - ቲየሪ፥ ሐገነቢብ theory

ንጽረተዓለም - ርእዮተ ዓለም ፥ ዓለምንና አኗኗርን የምናይበት የአመለካከት ዘይቤ (ፍልስፍና) world view

አሟሰሰ - አደከመ ፥ አቅመቢስ አደረገ

አሳር - መከራ ፥ ስቃይ

አስሚታ - የሚያሳድረው ተፅእኖ ፥ምጣዱ አሰማ በሚለው ዘይቤ (Impact)

አስባታሊ - ሥራ የሚያበዛ ነገር ፥ አድካሚ አዙሪት፥ ባተለ-ደከመ፥ ጣረ ከሚለው ቃል የተገኘ

አርበ - ሩብ ፥ ¼ኛ

614763937

አብሪነት - ብርሃን ሰጪነት illuminate

አታሞ - ከበሮ ፣ በተወጠረ ቆዳ የተሰራ የሙዚቃ እቃ

አንጡራ - ዋናው ነገር ፣ የነገሩ እምብርት (essence)

አውስቦ ዐበድ - ለአወስቦን (ወሲብ) እጅግ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጥ ወሲብን የመጫወቻ ስፖርቱ ያደረገ sex mad

አውስቦን - ወሲብ - sex

አዛንቶ - አዝናንቶ - ዘና አድርጎ

አጋፋሪ - አስተናጋጅ ፣ አስተናባሪ

አግቦ - ሽሙጥ ፣ በጎንታ መናገር

እሳቦት - አስተሳሰብ ፣ የነገር አመለካከት

እስተርእዮ - መገለጥ-revelation - እግዚአብሔር ማንነቱን እና እሳቡን የገለጠበት መንገድና ሂደት

እንቶፈንቶ - ዋጋ የሌለው ከንቱ ነገገር፣ ገለመሌ - አርቲቡርቲ

እግረሙቅ - ማሰሪያ ብረት ፣ ካቴና

እግዚእ - ጌታ፣ እግዚእነ - ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

ከሳች - ገላጭ - የሚከስት ፣ የሚያሳይ

ዕቡይ - ትዕቢተኛ



ወሲቦት - የወሲብ ሥርዐት - የሰው የአውስቦን ባህርይ sexuality

ዝርወተ ኢትዮጵያ - ከኢትዮጵያ ወጥተው በያገሩ የሚኖሩ ፣ የተዘሩ የተበተኑ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያውያት Ethiopian diaspora - የሌላ አገር ቢሆን እንደ የአገሩ ስም ሊጠራ ይችላል።

ዝንቅ - ድብልቅ ፣ከየዐይነቱ የተዛነቀበት

የተምኔት እንጀራ - የምኞት እንጀራ ፣ ቢሆን ቢሆን የሚል ያልተጨበጠ አጉል ጉጉት

የት መጣ - ዳራ ፣ የነገሩ መነሻ background

ደቂቅ - ጥቃቅን፣ ንዑሳን

ዲታ - ባለጠጋ ፣ ሃብታም

ድኅረ ንባብ - ማንበብ መጻፍ ካወቁ በኋላ የማያነቡበት ዘመን / ባህል post literate

ድጋም - ሳያስተውሉ መደጋገም ፣ ማነብነብ

ገበረ - እጅ ሰጠ ፣ እሺ አለ ፣ ተገዛ

ገበያ ሰገድ - ሽመታን ፣ የመግዛት ችሎታን አንጉል የሚያከብር ያላግባብ ሸማች ቁስ አምላኪ አካሄድ

ገፈት - አሰር ፣ ላይ ላይ የሚንሳፈፍ ገለባ

ጋት - የአንድ እጅ መዳፍ ዝርግ ልክ - ትንሽ ርቀት

ግልብ - ጥልቀት የሌለው ፣ ላይ ላይ

| | | |
|---|---|---|
| ጎለሰሰ | - | አጋደመ ፥ ጣለ |
| ጎልዳፋ | - | ያልጠራ ፥ ያልተስተካከለ ፥ ኮልታፋ |
| ጎምላላ | - | ጎልቶ የሚታይ ፥ ዘለግ ያለ፥ (በአሉታዊ አገባብ ኩሩ፥ ሰው ጤፉ) |
| ጠረቃ | - | ጠገበ ፥ ሆዱን ሞላ |
| ጣመን | - | ድካም - ውጣ ውረድ |
| ጥልልታ | - | ግልጽነት ፥ ጥልል ያለ መሆን lucidity |



## የጽሑፎቹ ቀዳምያን ተደራስያን እና የቀረቡበት ቦታ

እዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ጽሑፎች በመጀመሪያ የቀረቡባቸውን መድረኮችና የሴሚናር አዘጋጆች መናገር ምናልባት ይጠቅም ከሆነ ብዬ ዘርዝሬአቸዋለሁ። የሁሉንም ጊዜ ማስታወስ ባለመቻሌ ይቅርታ እየጠየቅሁ የሚበዙት ባለፉት ሰባት አመታት ውስጥ የቀረቡ መሆናቸውን አስታውቃለሁ።

ወቅታዊ ዘላለማዊ

ለክርስቲያን ሥነጽሑፍ ባለ ሙያዎች ማኅበር ሴሚናር በETC የቀረበ

የክርስቲያን ሚዲያ ሜዳ

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ለሦስቱ አብያተ ክርስቲያን በግዮን ሆቴል ውስጥ ያዘጋጀው ሲምፖዚየም ላይ የቀረበ

አንጡራ ወንጌል

የክርስቲያን አሳታሚዎችና ጸሐፊዎች ማኅበር ሴሚናር ላይ የቀረበ - ETC

ሥነ ምግባር በሦስተኛው ሺህ ዘመነ ምህረት

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በአፍሪካ አዳራሽ ውስጥ ለአብያተ ክርስቲያን መሪዎች ያዘጋጀው ሲምፖዚየም ላይ የቀረበ

የንባብ እንቅፋት - የንባብ ትጋት

ለክርስቲያን ጸሐፊዎችና አሳታሚዎች ማኅበር

ኢትዮጵያና የተስፋ ጥበቃ

LLT - ለአገልጋይ መሪዎች ያዘጋጀው ሴሚናር - በኢ.አ.መ.ቅ. ኮሌጅ

ካሪዝማዊ ቅርስ

ኤስ አይ ኤም ና ፊንላንድ ሚሲዮን በመተባበር በ EGST (የኢትዮጵያ የድህረ ምረቃ ሥነመለኮት ትምህርት ቤት ውስጥ) ባዘጋጁት የውይይት መድረክ ላይ የቀረበ

የትርጉም ሥራና የወንጌል ተልእኮ

በSIL - ለአብያተ ክርስቲያን አገልጋዮች ተዘጋጅቶ በነበረ ሴሚናር ላይ የቀረበ

ምን አይነት መሪነት

በምስክር መጽሔት ላይ የታተመ

ኩሬት ወይስ ስምሪት

ለመጽሐፍ ቅዱስ ሠራዊት መጽሔት የተላከ

ወንጌላዊ ክርስትና

በዕንቁ መጽሔት ላይ የታተመ

የሰባኪው ጥሪና ሥነምግባር

በላንጋም ፕሪቺንግ ሴሚናር - (ደብረዘይት) - ለሰባክያንና መጋብያን በተዘጋጀ ዐውደ ጥናት ላይ የቀረበ